በሀሰተኛ ሰነድ ለመክበር
የተደረገ ጥረትና መዘዙ
ገጽ 11

ዘወትር በምሥጋና...
ገጽ 16

በተለወጠ ልብ የተለወጠ ሀገር
እንፍጠር
ገጽ 18


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

84ኛ ዓመት ቁጥር 004 መስከረም 4 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!














# ልዩ የኢኮኖሚ ዞን - ለምን?

**አዲሱ ገረመው**

**ዜና ትንታኔ**

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በቅርቡ ባካሄደው ውይይት በሥሩ የሚያስተዳድራቸውን ፓርኮች ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የመቀየር ፍላጎት እንዳለውና ለዚህም በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ እንዳለ መግለጹ ይታወቃል። ለመሆኑ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ለውጥ ያለው ፋይዳ ምንድነው?

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሰሃ ይታገሱ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በሀገሪቱ 13 ፓርኮች የሚያስተዳድር ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥም አንዱ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ነው። ፓርኮቹ መንግሥት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ የተቀናጀ መሠረተ ልማትን ያቀረበባቸው ናቸው። በአሁኑ ወቅትም

ልዩ የኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ

## የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ በያዝነው ዓመት አጋማሽ ይካሄዳል

ገጽ 8

# ሉዓላዊነትን ያለማስነካት ወኔ - የኢትዮጵያውን የጋራ ታሪክ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አባቶቻችን ሉዓላዊነቷ የተጠበቀ፣ የተከበረች ሀገርን አስረክበውናል። "ሉዓላዊነት" በዓለም ሕዝብ ዘንድ የምንታወቅበት፣ የጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት የሆንበት እንቁ ሀብታችንም ነው። ኢትዮጵያውያን በምንም ዓይነት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋት ውስጥ ብናልፍ የሀገራችንን ክብር እና ድንበር ሊጋፉ የመጣን ኃይል ለመመከት በአንድነት በመቆም የጋራ ታሪክን መጻፍ የቻልን ሕዝቦች መሆናችንን የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።

ለመሆኑ ኢትዮጵያውያን ሉዓላዊነታችንን ላለማስደፈር የሄድንበት ርቀት እንዴት ይገለጻል? የዛሬው ትውልድስ የሀገሩን ሉዓላዊነት ላለማስነካት እስከምን ተጉዟል? ሀገራችን ተምሳሌት ሆና የምትጠቀስበትን "ሉዓላዊነት" ወደፊትም ላለማስደፈር ከትውልዱ ምን ይጠበቃል?

ሉዓላዊነትን ያለማስነካት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ሰንደቅ ዓላማ የሉአላዊነት መገለጫ ነው




# «ሽግግራችን ከተስፋ ወደ ብርሃን፣ ከተግዳሮት ወደ ዘላቂ ድል ነው»

- አቶ ጌቱ ገመቹ
የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ኃላፊ

**ተስፋ ፈሩ**

ሞጆ፡- ሽግግራችን ከተስፋ ወደ ብርሃን፣ ከተግዳሮት ወደ ዘላቂ ድል መሆን አለበት ሲሉ የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ገለጹ።

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ የመሻገር ቀንን አስመልክቶ ባለፈው ሳምንት በሞጆ ከተማ በተካሄደው በፓናል ውይይቱ ላይ፤ የጳጉሜን ቀናት ከአሮጌው ዓመት ወደ አዲሱ ዓመት ለመሸጋገር ከፍተኛ ዝግጅት የሚደረግባቸው ናቸው። ሽግግራችንም ከተስፋ ወደ ብርሃን፣ ከተግዳሮት ወደ ዘላቂ ድል መሆን አለበት ብለዋል።

በአንድ በኩል ዘላቂ ደህንነትን ማረጋገጥ በሌላ በኩል ልማትን በማረጋገጥ ዛሬም ለትውልዱ ዐሻራ እያስቀመጥን ነው ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በችግሮች ላይ ድሎችን በማስመዝገብና ስኬቶችን የቀጣይ ግብአቶች በማድረግ የብልጽግና ጉዞ መሠረት ጥለናል ነው ያሉት።

ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚ ለመሸጋገር እየተደረገ ባለው እንቅስቃሴ በሁሉም ዘርፍ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየተመዘገቡ መሆናቸውን ተናግረዋል። በንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ በኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ልማት ዘርፍም አመርቂ ውጤቶች መመዝገባቸውንም አንስተዋል።

የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሀብቶቻችንን በማልማት ህብረተሰባችንን ተጠቃሚ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ባለፉት ዓመታት በተሠሩት



ሥራዎች በሁሉም ዘርፍ በርካታ ድሎች መመዝገብ መጀመራቸውን ተናግረዋል።

መንግሥት ሀገሪቱን ወደ ብልፅግና ለማሸጋገር የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ቀርፆ ተግባራዊ በማድረጉ ትልቅ ለውጥ እየተመዘገበ ነው። ስንዴ ከውጭ መግዛት ቀርቶ ወደ ውጭ መላክ ተጀምሯል። መንግሥት ለምርትና ምርታማነት የሰጠው ትኩረት የውጭ ምንዛሪ ገቢን በማሳደግ ሰፊ የሥራ እድል እየፈጠረ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

መንግሥት ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በሰጠው ትኩረት የውጭ ምንዛሪ ገቢን በማሳደግ ሰፊ የሥራ እድል እየፈጠረ መሆኑንም አንስተዋል።

የጋራ ተግዳሮቶችን በማሸነፍ የተገኘውን ስኬት በማሳደግ ድህነትን ማሸነፍ የመንግሥትና የሕዝብ አጀንዳ መሆኑን ጠቁመው፣ ስኬቶቻችን የነገ ጉዟችን ስንቅ ናቸው። ዛሬ የምናሳርፈው ዐሻራችንም ጉዟችን እና ሽግግራችንን የሚያግዝና የሚያሳካ ነው ብለዋል።

ድሎቻችን፣ ልምዶቻችን፣ የተፈጥሮ ሀብቶቻችን እና የታሪክ ክምችታችን የሽግግራችን ትሩፋቶች ናቸው፤ በሁሉም ዘርፍ የምንሠራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ በመቀጠል በቀጣይ የሚጠበቅብን ሥራ ይሆናል ሲሉም አክለዋል።

የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ አህመድ ኢድሪስ በበኩላቸው፤ ከለውጡ በኋላ መንግሥት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ ሪፎርሞች በማድረግ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረጉን አንስተው፤ ፖሊሲው ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ የሀገሪቱን ኢንዱስትሪዎች ምርትና ምርታማነታቸውን የበለጠ ለማሳደግ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል ብለዋል።

በኢንዱስትሪው ዘርፍ አራት ፖሊሲዎች መዘጋጀታቸውን፣ ከእነዚህ ፖሊሲዎችም 17 ስትራቴጂዎች መሰናዳታቸውን ጠቁመው፣ እነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት፣ የወጪ ምርቶችን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማሳደግና ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንደሚያግዙ ገልጸዋል።


እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ በኦሮሚያ ክልል ባለፈው ዓመት አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ የኢንዱስትሪ ምርቶች የተመረቱ ሲሆን፤ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ 800 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል። የኢንዱስትሪው ዘርፍ ባለፈው ዓመት 500 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠሩንም ጠቁመዋል።

ከለውጡ በፊት በኦሮሚያ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ቁጥር ስምንት ሺህ እንደነበረና ዛሬ ወደ 23 ሺህ ከፍ ብሏል፤ ብዙ ባለሀብቶችን ተቀብለናል ውጤቱ ለኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ያሳያል ብለዋል።

ከስድስት ዓመታት 7 ሺህ ኢንቨስትመንቶች ሥራ ላይ እንደነበሩና በአሁኑ ወቅት ወደ 12 ሺህ 721 ኢንቨስትመንቶች 800 ቢሊዮን ዶላር ካፒታል በማስመዝገብ በተጨባጭ ወደ ሥራ በመግባት ለ800 ሺህ ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠራቸውንም ገልጸዋል።

ባለፈው ዓመት የፋብሪካዎች የማምረት አቅም 48 በመቶ ከነበረው ወደ በአሁኑ ጊዜ 57 በመቶ አድጓል። በቀጣይም ያገኘናቸውን መልካም ተሞክሮዎች በማስፋት ምርትና ምርታማነታችንን በማሳደግ የክልላችንና የሀገራችንን ሁለንተናዊ የብልጽግና ጉዞ ከግብ ለማድረስ እንሠራለን ብለዋል።

የሽግግር ቀኑን ምክንያት በማድረግ በሞጆ ከተማ የሚገኘው የጆርጅ ቆዳና ጫማ ፋብሪካ፣ በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኘው ካኖሪያ አፍሪካ ጨርቃ ፋብሪካ እና በከተማዋ ዙሪያ የሚገኙ የግብርና ልማት ሥራዎች በቢሮ ኃላፊዎቹና ጥሪ በተደረገላቸው እንግዶች ተጎብኝተዋል፤ የፓናል ውይይትም ተካሂዷል።



# በዓባይ ግድብ ግንባታ የላቀ ብቃት ያካበቱ ባለሙያዎችን ማፍራት ተችሏል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በዓባይ ግድብ ግንባታ ሂደት በሲቪልም ሆነ በሃይድሮ ሜካኒካል ሥራዎች የላቀ ብቃት ያካበቱ ባለሙያዎችን ማፍራት መቻሉን የፕሮጀክቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ኤፍሬም ወልደኪዳን ገለጹ።

የግድቡ ግንባታ ፕሮጀክት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ኤፍሬም ወልደኪዳን ከኢዜአ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደገለጹት፤ ለፕሮጀክቱ ስኬት ከዲዛይን ጀምሮ እስከ ግንባታው የኢትዮጵያውያን ሚና የላቀ ነው።

የፕሮጀክቱ ግንባታ ሲጀመር በአንድ ጊዜ እስከ 15 ሺህ ዜጎች በግንባታው ሂደት ላይ በተለያዩ ሙያዎች ይሳተፉ እንደነበር የጠቀሱት ኢንጂነር ኤፍሬም፤ በግንባታው ሌት ከቀን በመትጋት በስኬት መንገድ ዘልቀው ለግድቡ እውን መሆን ዘላለማዊ አሻራቸውን በማሳረፍ የሚያኮራ ተግባር ፈፅመዋል ብለዋል።

በግንባታው የረጅም ዓመት ልምድ በቀን ሠራተኝነት የጀመሩ በርካታ ወጣቶች አሁን ላይ ከፎርማን እስከ ሱፐርቫይዘርነት መድረሳቸውንም ገልጸዋል።

በሲቪልም ሆነ በሃይድሮ ሜካኒካል ሥራዎች የላቀ ብቃት ያካበቱ በርካታ ባለሙያዎችን ማፍራት ስለመቻሉም አንስተዋል።

የዓባይ ግድብ 13 ተርባይኖች እንዳሉት ገልጸው፤ የጀነሬተር አካል እስከ 12 ሜትር ዲያሜትርና ከ460 ቶን በላይ ክብደት ስላለው በትራንስፖርት አጓጉዞ ለማድረስ ፈታኝ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ነገር ግን በፕሮጀክቱ ግንባታ ላይ የተሳተፉ ኢትዮጵያውያን በየጊዜው አቅማቸውን በማጎልበት ዛሬ ላይ ግብዓቶችን በማምጣት ከዚሁ እንዲገጣጠሙ ማድረግ የሚችሉበት አቅም ተፈጥሯል ብለዋል።

በመሆኑም በቀጣይ ኢትዮጵያ ለምትገነባቸው የሀይድሮ ፓወር ፕሮጀክቶች የሙያ ብቃትና ዝግጁነት እንዲኖር አስችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

የኬ.ቲ ኢንዱስትሪያል ሶሉሽን ሥራ አስኪያጅ ሞላ አስማረ፤ የግድቡ ግንባታ ሲጀመር ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበር ገልጸው፤ በሂደት የራሳቸውን ድርጅት ከፍተው የተርባይን ማቀዝቀዝ ክፍል ዋነኛው ክፍል የሆነውን ራዲያተር በራሳቸው መስራት መጀመራቸውን ተናግረዋል።

አብዛኛውን የፕሮጀክቱን ግብአት በራሳቸው መሥራት እንደሚችሉ ገልጸው፤ ከአቅም ግንባታ ባለፈ የውጭ ምንዛሬ ማዳን ያስችላልም ብለዋል።

በህዳሴው ግድብ ላይ በተለያዩ ሙያዎች ላይ የተሳተፉ በርካታ ወጣቶች በየዘርፉ የኤክስፐርት ደረጃ ላይ የደረሱ እንዳሉም አስታውሰዋል።

በህዳሴ ግድብ ግንባታ በቀን ሥራ ይሳተፉ የነበሩ በርካታ ወጣቶች እውቀትንና ክህሎታቸውን በማዳበር ከፍተኛ የሙያ ብቃት ላይ መድረሳቸውንም ገልጸዋል።

በብየዳ ሥራ የተሰማሩት ወጣት ያየህ የሻንበል እና ህይወት አስማረ፣ በግንበኛ ሙያ የተሰማራችው ወጣት ደጌ በዓባይ ግድብ ግንባታ ሂደት በማንኛውም ቦታ በብቃት መሥራት የሚያስችል አቅም መፍጠር ችለናል ሲሉ ተናግረዋል።

ከመጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በዜጎች ገንዘብና ጉልበት ግድብ ሰርቶ ከወንዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የግንባታ መሠረት መቀመጡ ይታወሳል።

ለዚህም ኢትዮጵያውያን ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን ያለምንም ስስት ለግንባታው አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን፤ በርካቶችም የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው በመስራት ላይ ይገኛሉ። የግድቡ ግንባታ በመገባደድ ላይ ያለው በዜጎች እውቀት፣ ገንዘብና ጉልበት ነው።

# ማሻሻያው ለጥራጥሬና ቅባት እህሎች ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

**ማህሌት ብዙነህ**

ኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ተመን በብሄራዊ ባንክ የሚወሰንበት ሥርዓት ትከተል የነበረ ሲሆን፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ መንግሥት ካደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ውስጥ የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ የሚወሰንበት ሥርዓት ወይም ፍሎቲንግ ኤክስቼንጅ ሬት ትግበራ ተጀምሯል።

ታዲያ የተደረገው የውጭ ምንዛሬ ፖሊሲ ማሻሻያ በግብርና ኤክስፖርት ዘርፍ ላይ በተለይም በጥራጥሬ እና በቅባት እህሎች ላይ የሚኖረው እድልና ተግዳሮት ምን ይመስላል?

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር አረጋ ሹመቴ እንደሚሉት፤ በመንግሥት ተግባራዊ የተደረገው የውጭ ምንዛሬ ፖሊሲ ማሻሻያ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ አሁን ያለውን የውጭ ምንዛሬ እጥረት ለመቅረፍ ይረዳል።

የውጭ ምንዛሬ ፖሊሲ ማሻሻያ በተለይም በጥራጥሬ እና በቅባት እህሎች የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንዳለው የገለጹት ተመራማሪው፤ በዘርፉ ላይ የጥቁር ገበያ እና በወጪ ንግድ ዘርፉ ላይ የሚስተዋለውን ህገወጥነትን ለመቀነስ የሚያስችል መሆኑን ማህበሩ በሰራው ዳሰሳ የወጣ ሪፖርት እንደሚያሳይ አስታውቀዋል።

እንዲሁም በዘርፉ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቀነስ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ የዋጋ መቀነስን ተከትሎም የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በመጨመርና የገበያ እድሎችን በማሳደግ ነጋዴው የተሻለ የሀገር ውስጥ ሽያጭን እንዲያከናውን የሚረዳ መሆኑን ገልጸዋል።

የፖሊሲ ማሻሻያ ተግባራዊ የተደረገበት ጊዜ ሀገሪቱ የኢኮኖሚ ችግሮች ውስጥ ባለችበት ወቅት መሆኑ እና ዓለም አቀፍ ወቅታዊ ሁኔታዎች አንጻር ለትግበራው ፈታኝ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰው፤ መህል ሰፋሪ ወይም የህገወጥ ደላሎች መበራከት ሌላው በዘርፉ ሊከሰት የሚችል ተግዳሮች መሆኑን ይናገራሉ።

ዶክተር አረዳ እንደገለጹት፤የሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች 85 በመቶ ግብአታቸውን ከውጭ ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን ተከትሎ ፖሊሲው በአንጻራዊነት ለውጭ ላኪዎች የተሻለ ይሆናል።

በመሆኑም ምርቶች ወደውጭ የሚቀርቡበት ብሎም የሀገር ውስጥ ሂደቱ ህጋዊ በሆነ መንገድ መሆን አለበት። ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የጥራጥና ቅባት እህል ምርቶች ግድ እሴት መጨመር እና የምርቶችን ጥራት ማሳደግ እንዳለበት ተናግረዋል።



የኢትዮጵያ ጥራጥሬ፣ ቅባት እህሎችና ቅመማ ቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ኢዳዖ አብዲ እንደገለጹት፤ የሀገር መለወጥና እድገትን ተከትሎ መሰረታዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተደርጓል። እንደላኪ ድርጅት ማህበርም የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለውጥና መነቃቃት ይፈጥራል ብለዋል።

አብዛኛው የግብርና ምርቶች የሀገሪቱን አጠቃላይ ምርት ከ30 በመቶ በላይ የሚይዙና የወጪ ንግዱን ከ75 በላይ የያዙ ቢሆኑም የግብርና ሲክተሩ በኪሳራ ሲሰራ እንደነበር ጠቅሰው፤ አሁን የተደረገው ማሻሻያ የወጪ ንግዱ ትርፋማና የተሻለ እንዲሆን ያደርገዋል ይላሉ።

እንዲሁም ላኪው በኪሳራ የላከውን የውጭ ምንዛሬ ሌሎች ምርቶችን ወደሀገር ውስጥ ገቢ በማድረግ ኪሳራውን ያካክስ ነበር። ይህም ለማህበረሰቡ ለኑሮ ውድነት ይዳርግ እንደነበር ገልጸው፤ ማሻሻያው የገቢ ንግድና የወጪ ንግድ እንዲለያዩና እራሱን ችሎ እንዲሄድ ያደርጋል ሲሉም ይገልጻሉ።

ፖሊሲ ማሻሻያው ለውጭ ባለሀብቶች በስፋት እንዲሰማሩ እድል የሚሰጥ መሆኑንም አንስተው፤ይህም የግሉ ባለሀብት የተሻለ እንዲሰራ በማድረግ የገበያ ተወዳዳሪነትን የሚጨምር መሆኑንም ያስረዳሉ።

እንዲሁም ይላክ የነበረው ጥሬ ምርት ላይ እሴት ወደመጨመር እንዲገባ የሚያደርግ ፣የገበያ ድርሻ የሚጨምርና ምርታማነትን የሚያሳድግ መሆኑንም አንስተዋል።

ዶክተር ኢዳዖ ከ20 በመቶ በላይ የሚሆን ምርቶች በህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ይወጣ እንደነበር አንስተው፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲው ህገወጥን በመቆጣጠር ህጋዊዎችን የሚያበረታታና ገቢን የሚያሳድግ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የፖሊሲው ማሻሻያ ወደውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎች እንዳይቀንሱ እና የዋጋ መዋዠቅ እንዳይከሰት በማድረግ የውጭ ምንዛሬን ለማስተካከልና ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ለማስገት እንደሚያግዝም ገልጸዋል።

# የቦንጋ ከተማን ለዜጎች ምቹ የመኖሪያና የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በአዲሱ ዓመት የቦንጋ ከተማን ለዜጎች ምቹ የመኖሪያና የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን የከተማው ከንቲባ አስማማው አደመ ገለጹ።

ከንቲባ አስማማው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአዲሱ ዓመት የቦንጋ ከተማን ለዜጎች ምቹ የመኖሪያና የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ስራ በመስራት የህዝብን ጥያቄ መመለስ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው።

እንደ ከንቲባው ገለጻ፤ ከተማው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የአስተዳደርና ፖለቲካ መቀመጫ እንደመሆኑ መጠን ይህንን የሚመጥን መሰረተ ልማት ለማሟላት የመሀል ከተማውን 44 ሄክታር መሬት በመለየት መልሶ የማልማት ተግባር እየተከናወነ ነው።

የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጠናከርና የፋይናንስ ምንጭ እንዲሆን በማድረግ ከ136 ሚሊዮን በላይ ብር ማሰባሰብ መቻሉን የገለጹት አቶ አስማማው፤ በዚህም የልማቱ ተነሽ ዜጎችን እንዲቋቋሙ ድጋፍ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

በተጨማሪም የከተማውን የመንገድ ደረጃን ለማሳደግና ከተማው ልዩ ውበት እንዲኖረው ለማስቻል ከ23 ኪሎ ሜትር በላይ የሚሸፍን የኮሪደር ልማት እየተከናወነ ነው። ይህም በቅርቡ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምር ከንቲባው አመላክተዋል።

በአዲሱ ዓመት በተለይም በመልሶ ማልማት ስራው ህብረተሰቡን በማስተባበርና በጀት በመመደብ የመንገዶችን ደረጃ ማሳደግና ባለፈው ዓመት ተጀምሮ ያልተጠናቀቁ የመንገድ ጥገና ስራዎችን እንደሚሰሩ ተናግረዋል።

በከተማው የሚገኘውን ብሄራዊ የቡና ሙዚየም የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ በኃላፊነት በመቀበል ሙዚየሙንና ዙሪያውን እያለማ መሆኑን የጠቆሙት ከንቲባው፤ በዚህም የመኪና ማቆሚያን ጨምሮ የተለያዩ ልማቶችን ያካተተ ዲዛይን ተዘጋጅቶ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል ነው ያሉት።



ፎቶ - በረሀኑ ታደሰ
አቶ አስማማው አደመ

እንዲሁም ለወጣቶች ቋሚ የስራ ዕድል ለመፍጠር እየተከናወነ ባለው ስራ ለዶሮ ማርቢያ የሚያገለግሉ 10 ሼዶች ተዘጋጅተዋል። በዚህም ወጣቶቹ ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ስራ የሚገቡ ሲሆን፤ ይህ ተግባር የስራ ዕድል ፈጠራን ከማጠናከር በተጨማሪ ገበያን እንደሚያረጋጋ አቶ አስማማው ገልጸዋል።

በከተማው የእግዜር ድልድይ፣ አንድራቻ መድኃኒዓለም፣ ቶንጎላ መስኪድ፣ የባርታ ፏፏቴ፣ የቦንጌ ሻንቤቶ ወይም የጥንት የከፋ ነገስታት መናገሻና ሌሎችም ለቱሪስት መዳረሻ የሆኑ ስፍራዎች እንደሚገኙ ያስታወሱት ከንቲባው፤ ለዚህም የሚሆን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት አስፈላጊ በመሆኑ ለአልሚዎች መሬት የማስተላለፍ ተግባር ተከናውኗል ብለዋል።

አቶ አስማማው፤ እስካሁን በተሰራው ስራ ለአብነትም የሌዊ ሪዞርት ከ60 በላይ ለቪአይፒ የሚሆኑ ማረፊያዎችን ያዘጋጀ ሲሆን፤ ይህም ለካፍቾ ብሄር ዘመን መለወጫ ማሽቃሬ ባሮ ስራ የሚጀምር ይሆናል። እንዲሁም በቅርቡ በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ አማካኝነት የተሰሩ 20ሎጆች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በዚህም ከተማውን የማልማት ስራው በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን አውስተዋል።

በከተማው በጤና፣ ትምህርት፣ ኢንቨስትመንት፣ ስራ ዕድል ፈጠራ በሌሎችም ዘርፎች እየተከናወኑ የሚገኙ የልማት ተግባራት ተጠናክረው የሚቀጥሉ መሆናቸውን ያመላከቱት ከንቲባው፤ አካባቢው ለኢንቨስትመንት ምቹ በመሆኑ ወደ ከተማው ለሚመጡ አልሚዎች ቢሮክራሲዎችን በማሳጠር በፍጥነት ወደ ልማት እንዲገቡ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠራቸውን ተናግረዋል።

# ወደ ግድቦች የሚገባው ከፍተኛ የውሃ መጠን ጉዳት እንዳያስከትል ጥንቃቄ ያስፈልጋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥሉት ቀናት በሚኖረው ዝናብ ምክንያት ወደ ግድቦች የሚገባው የውሃ መጠን ከፍተኛ በመሆኑ ጉዳት እንዳያስከትል ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አሳሰበ።

ከመስከረም አራት እስከ መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም በሚኖሩት ቀናት በሰሜን ምእራብ ፣በደቡብ ምእራብ ፣በምእራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ኢንስቲትዩት ለኢፕድ በላከው መግለጫ አስታውቋል።

በቀጣይ ቀናት በአብዛኛው የዓባይ፣ የባሮ አኮቦ፣የተከዜ ፣የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ ጊቤ ፣የስምጥ ሸለቆ ፣የአዋሽ ፣የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ኢንስቲትዩቱ አመላክቷል። ይህም ለገጸ ምድር እና ለከርሰ ምድር የውሃ ሀብት መጎልበት አዎንታዊ ጎን እንደሚኖረው ገልጿል።

በሌላ በኩል እነዚህ ተፋሰሶች በሚያገኙት እርጥበት ሳቢያ ወደ ግድቦች የሚገባው ውሃ ከፍተኛ በመሆኑ የቆቃ፣ የከሰም ፣ የተንዳሆ፣ ጣና በለስ፣ የርብና የፊንጫ ግድቦች ሞልተው በተፋሰሱ የታችኛው አካባቢዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ጠቁሟል።

በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ እንደሚኖር ያመላከተው ኢንስቲትዩቱ፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ እንደሚሄድና ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አመላክቷል።

ኢንስቲትዩቱ እንዳሳወቀው፤ በምእራብና በደቡብ ምእራብ የኢትዮጵያ ክፍሎች ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል። የደቡብ የሀገሪቱ ስፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ።

በሌላ በኩል በመስከረም ወር የክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በሰሜንና ምሥራቅ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚዳከም በመሆኑ የወቅቱ የዝናብ መጠንም ሆነ ስርጭት በነዚህ አካባቢዎች ላይ እየቀነሰ እንደሚሄድ ኢንስቲትዩቱ ጠቁሟል።

ይህም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ እንዲሁም ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ገልጿል።

በሌላ በኩል የእርጥበት ሁኔታው በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች መስፋፋት የማሳ ዝግጅት ለማድረግ ፣ የበጋ ወቅት ሰብሎችን ለመዝራት ፣ለግጦሽ ሳር እንዲሁም ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ኢንስቲትዩቱ አስታውቋል።

# በሱማሌ ክልል ከመኸር እርሻ 31 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በሶማሌ ክልል በ2016/17 የምርት ዘመን ከመኸር እርሻ 31 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት እየተሰራ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ የሩዝ እርሻም እየተከናወነ ይገኛል።

የሶማሌ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አህመድኑር አብዲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016/17ዓ.ም የምርት ዘመን በክልሉ ሶስት ሺህ ሄክታር መሬትን በሩዝ ሰብል ለመሸፈን ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን፤ እስከ ነሐሴ 30/2016 ድረስም 530 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል፤ የዝናቡ ስርጭት እስከ ጥቅምት ወር ስለሚቆይ ቀሪውን መሬት በሩዝ የመሸፈን ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በክልሉ የሩዝ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የምርምርና ዘሩን የማብዛት እንቅስቃሴ በትኩረት እየተሰራ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

በክልሉ በርካታ የሰብል አይነቶችን ማለትም በቆሎ፣ ማሽላ፤ስንዴ፣ገብስና በተወሰነ ደረጃም ጤፍ እንዲሁም ሩዝ ለመጀመሪያ ጊዜ የማምረት ስራ ተግባራዊ እየተደረገ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በክልሉ የታቀደውን 31 ሚሊዮን ኩንታል ምርት በማግኘት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሰብሎችን በሰው ሀይል የማረም፤ ኬሚካል የመርጨት፣ ፀረ ተባዮችን የመከላከል፤ በሽታ እንዳያጠቃ የመከታተል ስራ በትኩረት እየተሰራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።


አቶ አህመድኑር አብዲ

በክልሉ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለአርሶ አደሮች ከ20 ሺህ በላይ ኩንታል በቆሎና ማሽላ፤ 10 ሺህ ኩንታል የስንዴ ምርጥ ዘሮችን ለአርሶ አደሮች ተደራሽ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፤ እየተሰራም ነው ብለዋል።

በክልሉ በበጋ መስኖ ከሚለመው መሬት በስተቀር የአፈር ማዳበሪያ የሚፈልግ መሬት የለም ያሉት ኃላፊው፤ ያለውን ለም አፈር ተጠቅሞ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከፊል አርብቶ አደሮችን ወደ እርሻ የማስገባት ስራ እየተሰራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በሶማሌ ክልል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የግብርና ቴክኖሎጂውን የመጠቀም ስራ እየተሰራ እንደሆነም አብራርተዋል።

የክልሉ አርሶ አደሮች ምርጥ ዘርን የመጠቀም ፍላጎታቸው እያደገ ነው፤ ክልሉ የሚፈልጉትን ያኽል ምርጥ ዘር ተደራሽ እያደረገ ቢሆንም እጥረት አለ፤ እጥረቱን ለመፍታት እየተሰራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ አህመድኑር አያይዘውም ክልሉ ለም አፈር ያለው ቢሆንም የክልሉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የአፈር ማዳበሪያ የመጠቀም ፍላጎት ከፍተኛ ነው፤ ነገር ግን ፍላጎቱን የሚያሟላ አቅርቦት የለም፤ በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን 70 ሺህ ኩንታል ብቻ የአፈር ማዳበሪያ ነው ማቅረብ የተቻለው ብለዋል።

# የዘመን እንግዳ

# “አዲሱን ዓመት መቀበል ያለብን በአዲስ እይታ እና በአዲስ ተነሳሽነት ነው”

**ዘሪሁን ገብሬ (ዶ/ር)**
**የሊድስታር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት**



አስቴር ኤልያስ

የዛሬው የዘመን እንግዳችን ዘሪሁን ገብሬ (ዶ/ር) ይባላሉ:: ዘሪሁን (ዶ/ር) የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው:: በሊድስታር ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በማኅበረሰብ ልማት ‘Community Development’ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሰርተዋል:: ትምህርታቸውን በአገር ቤት ብቻ ሳይወሰኑ ባህር ማዶ በመሻገር በዳላስ ዩኒቨርሲቲ በትራንስፎርሜሽናል ሊደርሺ (Transformational Leadership) ሦስተኛ ዲግሪያቸውን መስራት ችለዋል::

ዘሪሁን (ዶ/ር) የሊድስታር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ናቸው:: በትምህርት ደረጃ በኤች. አይ.ቪ. ኤድስ ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ፣ ሥነ-መለኮት (‘Theology’)፣ ሰላም እና ግጭት አፈታት እና የፕሮጀክት አስተዳደርም ተምረዋል፣ አራት የተለያዩ መጻሕፍትንም ጽፈው ለንባብ አብቅተዋል:: አዲስ ዘመንም እኝህን ምሁር አዲስ ዓመትን አስመልክቶ የዛሬው የዘመን እንግዳው አድርጎ አቅርቧቸዋል:: መልካም ንባብ ይሁንልዎ::

**አዲስ ዘመን፡- አዲሱን ዓመት እንዴት ልንቀበለው ይገባል? በአዲሱ ዓመት ያቀደው ዕቅድ እንዴት ሲሳካልን ይችላል?**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** አዲሱን ዓመት መቀበል ያለብን በአዲስ እይታ እና በአዲስ ተነሳሽነት ነው ብዬ አምናለሁ። አዲሱን ዓመት በአዲስ ሂደት፣ በአዲስ ግብ እና በአዲስ መርሃግብር መቀበል አለብን። ይህ አንድ ብለን የጀመርነው አዲስ ዓመት በእኔ አተያይ ሁለት ትልልቅ ነገሮች ይዞ ይመጣል። ይኸውም አንዱ እድል ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ፈተና ነው።

እንደሚታወቀው በዓመቱ ውስጥ ያሉት 365 ቀናት ናቸው። እነዚህ 365 ቀናት በሙሉ መሥራት የምንችልባቸው ናቸው የሚል እምነት አለኝ፤ ቀናቱ የተሰጡት ደግሞ ለተመረጡ ሰዎች አሊያም ውስን ለሆኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ለሁሉም እኩል የሚሰጡ ናቸው። ነገር ግን ዋናው ልዩነቱ የሚፈጠረው በተሰጡን ቀናት ያለን አጠቃቀም ላይ ነው። እነዚህን ቀናት በትክክል የምንጠቀምባቸው ከሆነ ፊታችን ያለው የስኬት ጊዜ ይሆናል። ቀናቱን በአግባቡ ካልተጠቀምንበት ግን በኪሳራ የምንኖርበት ጊዜ ይሆናል። እንዲያም ሆኖ ምርጫው በእጃችን በመሆኑ የእኛው ነው።

ሰዎች አሮጌው ዘመን አልፈው ወደ አዲስ ዘመን ሲሸጋገሩ አንድ ማስተዋል የሚጠበቅባቸው ነገር እንዳለ ማጤን አለባቸው። ይኸውም ወደፊት ያሉትን አማራጮች ማየት መቻል ነው። ምንም እንኳ ያሳለፍነው ዓመት የከፋ ቢሆንም፤ አዲሱን ዓመት በአዲስ ስኬት እና በአዲስ ርዕይ መጀመር እንችላለን።

ሁሌም ቢሆን ከአዲሱ ዓመት ጋር የሚመጣ አዲስ ጥንካሬ እና አዲስ ሀሳብ ይኖራል። ይህም በአዲሱ ዓመት ውስጥ ያሉትን ቀናት ሁሉ በጥበብ መጠቀም የስኬት መንገድ ነው። ቀናቱን በትክክል በተሰጠን አግባብ አለመጠቀም ግን ኪሳራ ነው። ስለዚህ አዲሱ ዓመት ይዞ የመጣውን አዳዲስ እድሎችን በአግባቡ መጠቀም የኛ ድርሻ ነው።

በሌላ በኩል አዲሱ ዓመት የራሱን ትግል እና ውጣ ውረድ ይዞ ይመጣል። ትናንት ከነበርንበት ሕይወት መውጣት ራሱን የቻለ ትግል ነው፤ ከትናንቱ ስህተቶቻችን ለመታረም መሞከር ይህም ትግል ነው፤ ከትናንት ውድቀት ለመውጣት መጣርም እንዲሁ ከባድ ትግል ነው። ስለሆነም ካለንበት ውድቀት እና ጥላቻ ወጥተን ፍቅርን ለማዳበር ጠንካራ ትግል ይጠይቃል።

በአዲሱ ዓመት ትግሉን ለማሸነፍ ከትናንት ተምረን ለሚመጣው ነገር መዘጋጀት አለብን። በአዲሱ ዓመት የትናንቱ ውስብስብ የሆኑ ችግሮቻችን እንደገና እንዳይዙን የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። እንደ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ አመራር እና ሀገር ከችግሮቻችን ለመውጣት የምናደርገው ጥረት ጠንካራ ትግል ይጠይቃል። ስለዚህ በአዲሱ ዓመት ራሳችንን ለቀጣይ እድሎች እና ትግሎች ማዘጋጀት የግድ የሚለን ይሆናል።

በአዲሱ ዓመት የትናንትናን ያልተሳካ ኑሮ እንደገና ላለመኖር መወሰን አለብን። በአዲሱ ዓመት እንደ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ እና ሀገር ከፊታችን ላሉ እድሎች እና ትግሎች ራሳችንን ማዘጋጀት ትልቁ ጉዳይ ነው።

ወደ አዲሱ ዓመት ከመሸጋገራችን በፊት የባለፈው ዓመት ዕቅድ እና አፈፃፀም መገምገም ይጠበቅብናል። እንዲሁም የአዲሱን ዓመት ዕቅዳችን እና ርዕያችንን በጥልቀት መመልከት እና መገምገም አለብን። በምናደርገው ግምገማ ጠንካራ እና ደካማ ጎናችን በመለየት በአዲሱ ዓመት ክፍተቶቻችንን በመሙላት ወደ ላቀ ደረጃ ለመሸጋገር እራሳችንን ማዘጋጀት አለብን። የጳጉሜን ቀናት የባለፈው ዓመት አፈፃፀማችን የምንገመግመው እና ለአዲሱ ዓመት በአዲስ እቅድ እራሳችንን የምናዘጋጅበት ጊዜ ነው።

አዲሱ ዓመት ችግሮቻችንን ለመፍታት ከፍተኛ ትግል የምናደርግበት ጊዜ ይመስለኛል። በአመቱ አዲስ ሕይወት መኖር መጀመር አለብን። ባለፈው አመቱ ያልተሳካልንን ጉዳይ በማስታወስ ያ እንዲህ መሆን ነበረበት እያልን የምንተክዝበት ሳይሆን፤ በቀጣዩ ዓመት ምን መሆን አለበት የሚለው ላይ ማተኮር የተሻለ ነው ባይ ነኝ።

አዲሱን ዓመት አዲስ የሚያደርገው ዓለምን እንዴት እንደምንመለከተው እና በአዲስ መልኩም ውሳኔ የምናሳልፍበት ነው። ይህንን እንደ ማኅበረሰብ እና መንግስት ማሰብ በጣም አስፈላጊ ነው:: አዲሱ ዓመት ለችግሮቻችን መፍትሄ የምንፈልግበት እንጂ በትናንትናው መሰናክል የምንያዝበት ዘመን መሆን የለበትም።

በአጠቃላይ ይህ የተያያዝነው አዲስ ዓመት ብዙ እድሎችን እና ፈተናዎችን ይዞ ወደ እኛ እየመጣ ነው። ዕድሎቹን ተጠቅመን ትግሉን ለማሸነፍ እራሳችንን ማዘጋጀት አለብን። በአመቱ ከስህታችን በመማር በሚቀጥለው ጊዜ የተሻለ ሥራ ለመስራት ማዘጋጀት አለብን።

መዘንጋት የሌለበት ነገር ያለፈውን መለወጥ ባንችልም ዛሬን ልንጠቀምበት እና ለነገ እራሳችንን ማዘጋጀት እንደምንችል ነው። የእኛ አመለካከት ለዚህ ወሳኝ ነው። አንድ ሰው አመለካከቱ ከተቀየረ ሕይወቱ እና የወደፊት ዕጣ ፈንታው ይለወጣል።

ጠንካራ ሰዎች እድሎችን ሲመለከቱ፣ ደካማ ሰዎች ደግሞ መሰናክሎችን በማሰብ ተስፋ ይቆርጣሉ። ጠንካራ ሰዎች ስለወደፊቱ ስኬት እና እድገትን ያስባሉ። ደካማ ሰዎች ደግሞ ስለ ውድቀት ያስባሉ። ደካማ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ብቻ ላይ ያተኩራሉ። ጠንካራ ሰው ለመሆን በአመለካከታችን ላይ መሥራት አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ከፊታችን ያሉትን እድሎች ለመጠቀም እና ትግሉን ደግሞ በድል ለመሻገር እና ስህተታችንን ለማረም እንደ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ እና ሀገር ምን ማድረግ አለብን?**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** ሰው ከውድቀቱ፣ ከድክመቱ እና ከስህተቱ የበለጠ ይማራል። የማይታበለው ሀቅ ቢኖር ለዓመታት እንደ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ እና ሀገር የሰራናቸው ብዙ ስህተቶች አሉ። ስህተቶቹ ከአሮጌው ዓመት ጋር አልፈዋል። በአዲሱ ዓመት ውስጥ ያሉ 365 ቀናት በትክክል ለመጠቀም አዲስ እቅድ እና መርሃ ግብር በማውጣት በርትተን መሥራት ይጠበቅብናል። የዓመቱን ቀናት በሙሉ በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው በዓመቱ ብዙ ነገሮችን ማከናወን እንችላለን። ዕቅዳችንን ተግባራዊ ካላደረግን ግን ባለንበት እንቆያለን። ስለዚህ ካለፈው ተምረን ከፊታችን ለሚመጡት አዳዲስ ነገሮች እራሳችንን ማዘጋጀት ብቁ ማድረግ ከእኛ የሚጠበቅ የቤት ስራ ነው።

> **በአዲሱ ዓመት የትናንትናን ያልተሳካ ኑሮ እንደገና ላለመኖር መወሰን አለብን። በአዲሱ ዓመት እንደ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ እና ሀገር ከፊታችን ላሉ እድሎች እና ትግሎች ራሳችንን ማዘጋጀት ትልቁ ጉዳይ ነው**

ከፊታችን ባሉት ቀናት ውስጥ ጠንክረን የምንሠራበት ጊዜ መሆን አለበት። ቁጭ ብለን ስለ ትናንት ድክመታችን ከማሰብ ተግተን በመስራት ከችግር እና ከድህነት መውጣት የእኛ ድርሻ ነው ባይ ነኝ። የሚያጋጥሙን ችግሮች እንቅፋት ሳይሆን ጠንክረን እንድንሠራ እንደ መልካም አጋጣሚ ልንጠቀምበት ይገባል። ስላለፈው ነገር መጨናነቅ ትተን የወደፊቱ ላይ አተኩረን መሥራት ከአንድ ብልህ ሰው የሚጠበቅ ነው።

ቀናት በራሳቸው ጥሩም መጥፎም አይደሉም:: ቀናትን ጥሩ እና መጥፎ ናቸው ብለን ባንፈርጃቸው መልካም ነው። ምክንያቱም መልካሙን እና ክፉውን ቀን የሚወስኑት የምንኖርበት ሁኔታ ነው። በፊታችን ያሉትን ቀናት በትክክል ከተጠቀምንበት ይሳካልናል፤ ካልተጠቀምንበት ግን ስኬት የለም። በመጪዎቹ ቀናት በትክክል ለመጠቀም አዳዲስ አመለካከቶች፣ አዳዲስ እቅዶች እንዲሁም መርሃ ግብሮች እና ግቦች ሊኖረን ይገባል:: ያለፉት ቀናት ተመልሰው አይመጡም። ስለዚህ ከፊታችን ያሉትን ቀናት በተሻለ ሁኔታ መጠቀም የግድ ይለናል። ሁሉን ቀናት በአዲስ አእምሮ እና ፕሮግራም መቀበል አለብን። ለመጪው አዲስ ዓመት ያቀድነውን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ መዘጋጀትም ቁርጠኛ መሆንም ከእኛ የሚጠበቅ የቤት ስራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአዲሱ ዓመት ዕቅዳችንን በትክክል ለማሳካት ምን ማድረግ አለብን?**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፡-** ዕቅድ የስኬት አንድ በመቶኛ ሲሆን፣ 99 በመቶው የእቅዱ አፈፃፀም ነው። ስኬታማ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “አዲሱን ዓመት መቀበል...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ሰዎች የዕቅድ ጥቅምን ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው:: የተለያዩ ፕሮጀክቶች ላይ የሚሰሩ ሰዎችም የዕቅድ ጥቅም በደንብ የገባቸው ናቸው:: ዕቅዳችን ተግባራዊ ካልሆነ ግን በወረቀት ላይ የሚቀር ይሆናል። ስለዚህ የዓመቱን ዕቅዳችን በግማሽ ዓመት፣ በሩብ ዓመት፣ በወራት፣ በሳምንታት፣ በቀናት እና በሰዓታት ከፍለን ተግባራዊ ማድረግ አለብን። የእለት ተእለት ሥራዎቻችንን እየገመገምን መሄድም ይጠበቅብናል። ተግባራዊ ያልሆነ ዕቅድ ከነምክንያቱ መቀመጥ አለበት።

እቅድ ሲባል አሁን ባለንበት እና መድረስ በምንፈልግበት መካከል ያለ ድልድይ ነው። የምንፈልገው ቦታ ለመድረስ ድልድዩን እየገነባን መሄድ አለብን። ርዕያችን የሚሳካው በዕቅዳችን አፈፃፀም ነው። ስለዚህ ለነገ ዛሬ ማቀድ አለብን:: ዕቅድ አቅደን አለመተግበር ግን ጊዜ ማባከን ነው። ስለዚህ ያቀድነውን እቅድ ተግባራዊ ማድረግ አለብን። የዕቅድ አፈፃፀማችን በየጊዜው እየገመገምን ካልሄድን በመጨረሻ እንዳሰብነው አይሆንም። ዕቅዳችንን ተግባራዊ ማድረግ ካልቻልን በየዓመቱ ማቀድ ብቻ ሆኖ ይቀራል።

**አዲስ ዘመን፦ ባለፈው ዓመት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተስተውለው የቆዩትን የጸጥታ ችግሮችን በአዲሱ ዓመት እንዳይደገሙ ለማድረግ መፍትሄው ምንድን ነው ይላሉ?**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፦** የአገራችን የጸጥታ ችግር ብዙ ነገሮችን የሚያካትት ነው፤ ቢሆንም በሚከተሉት ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። በመጀመሪያ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ለወጣቶች ተጨማሪ የስራ እድል መፍጠር ላይ ነው ባይ ነኝ። ስራ አጥነት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ችግር ሲሆን፣ ድህነት ደግሞ የታዳጊ ሀገራት ትልቁ ፈተና ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በተደረገ አንድ ጥናት መሰረት ከስድስት ወጣቶች መካከል ስራ የሚያገኘው አንዱ ወጣት ብቻ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጣቶች ስራ አጥነት 50 በመቶ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 89 በመቶ የሚሆነው በታዳጊ ሀገራት ነው። በወጣቶች ላይ መስራት ማለት ሀገሪቱን የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ እንደመስራት የሚቆጠር ነው።

ሳይሠራ የሚበላ ሰው ችግር ለመፍጠር ዝግጁ ነው:: “ሥራ ፈት አእምሮ የሰይጣን መመሪያ ነው” ይላሉ ፈረንጆች። ስለዚህ ለወጣቶች ተጨማሪ የስራ እድል ቢፈጠር ግጭቶች እና የጸጥታ ችግሮች በዚህ አይቀጥሉም ብዬ አምናለሁ። በሁለተኛ ደረጃ መልካም አስተዳደርን እስከ መንደር ድረስ ማስፈን ነው፤ መንግስት በዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ሕብረተሰቡ የሚፈልገውን አገልግሎት እንዲያገኝ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፈታት አለባቸው።

ሦስተኛው የሀገሪቱን የጸጥታ ችግሮች ለመፍታት ለጸጥታ ችግር መንስኤ ወይም ምንጭ ናቸው የተባሉትን ነገሮች በአግባቡ መመርመር አስፈላጊ ነው ባይ ነኝ። የጸጥታ ችግርን ለመፍታት የሀገሪቱ ሕብረተሰብ ካለፈው በመማር በሠላም ግንባታ ላይ በጋራ መሥራት አለበት። በጸጥታ ችግር ከደረሰብን ጉዳት ተምረን ሠላም እና ጸጥታን ለማስጠበቅ በጋራ መስራት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፦ የአገራችን እና ያደጉት አገራት የስራ ባሕል እንዲሁም የጊዜ አጠቃቀምን እንዴት ይገልፃሉ?**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፦** ያደጉ አገሮች የሥራን እና የጊዜን ጥቅም ጠንቅቀው ያውቃሉ:: ሳይሠሩ መኖር እንደማይችሉ አሳምረው የተረዱ ናቸው። ለአብነት ያህል መጥቀስ ካስፈለገ በአገራችን ቡናን አንድ ጊዜ በመትከል በየዓመቱ ምርት እናገኛለን። በአገራችን ትንሽ በመስራት መኖር ስለሚቻል የስራ ባህላችን ደካማ ነው።

በሀገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የዋጋ ንረት ለመፍታት የስራ ባህላችን ሙሉ ለሙሉ መቀየር አለበት እላለሁ። ለውጥ ለማምጣት እንደ ግለሰብም ሆነ በምንሰራበት ድርጅት ውስጥ የስራ ባህላችን ሙሉ ለሙሉ መለወጥ ብሎም በአፋጣኝ መሻሻል አለበት። አለበለዚያ ዛሬ ላለው ትውልድ ነገ ቀላል የሚባል ጊዜ አይሆንም።

የተያያዝነው አዲሱ ዓመት የውድድር ዘመን ነው፤ በመሆኑም ጊዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም እማ



በአዲሱ ዓመት (2017 ዓ.ም) ሁሉም የሀገሪቱ ሕዝቦች በሰላም ወጥተው የሚገቡበት፣ በፍቅር እና በደስታ አብረው የሚኖሩበት፣ ሰዎች በነፃነት ወደ ፈለጉት ቦታ ተንቀሳቅሰው የሚሰሩበት ወቅት እንዲሆን ትልቁ ምኞቴ ነው

ጠንክረን በመስራት ብርቱ ተፎካካሪ መሆን አለብን። ሠርተን ከምናገኘው ገቢ መቆጠብ እና ከቆጠብነው ገንዘብ ኢንቨስት ማድረግ አለብን። ጊዜው የውድድር ነው፤ ስለሆነም ይህ ትውልድ በውድድር ዘመኑ ጠንካራ እና ተፎካካሪ ለመሆን ጠንክሮ መስራት አለበት።

ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን ያልቻሉ መተዳደሪያ እስኪያጡ ድረስ ሊሰቃዩ ይችላሉ። ዘመኑ የዲጂታል ስለሆነ ወደፊት በመዝረፍ ወይም መስረቅ አይቻልም። ስለዚህ የሚያወጣን ጠንክረን ለመስራት ዝግጁ መሆን ብቻ ነው።

ያልተዘጋጀ ሰው ራሱን ላዘጋጀ ሰው ሠራተኛ ይሆናል። ራስን ማዘጋጀት ማለት እግዚአብሔር የሰጠን ጊዜ እና ስጦታ በደንብ ለመጠቀም መዘጋጀት ማለት ነው። አንድ ቀን 24 ሰዓት አለው። እግዚአብሔር የሰጠንን ጊዜ እና አእምሯችንን ለመጠቀም እራሳችንን ማዘጋጀት አለብን። ስኬታማ ለመሆን አእምሮአችንንና ጊዜያችንን በጥበብ መጠቀም ይኖርብናል።

ጊዜን መበደር፣ ማበደር፣ መውሰድ፣ ማቆም፣ ማራዘም፣ ማሳጠር አንችልም። በጊዜ መጠቀም ስኬታማ እንደሚያደርግም ሁሉ በትክክል አለመጠቀም ደግሞ የውድቀት መንስኤ ነው። ስለዚህ ጊዜን በትክክል የመጠቀም ጥቅም በደንብ መረዳት አለብን።

ብዙ ወጣቶቻችን በማኅበራዊ ድህረ ገጽ ላይ የሚለቀቁትን ቀልዶች በማየት ጊዜያቸውን እያጠፉ ነው። አሁን ካሉበት ኑሮ ለመውጣት ራሳቸውን በትምህርት ማዘጋጀት አለባቸው። ማኅበራዊ ሚዲያን ለበጎ ነገር መጠቀም መቻል አለባቸው።

ማኅበራዊ ሚዲያን ሕይወታችንን ለመቀየርና ለማሻሻል መጠቀም አለብን። ስለ አንተ የሚያስብ የመጀመሪያው ሰው ራስህ ነው። ሌላው ቀጥሎ ይመጣል። አሁን ያለው ትውልድ ራሱን ለመለወጥ ዝግጁ ካልሆነ ራሱን ለመለወጥ ለተዘጋጀ ሰው ሠራተኛ ወይም ይመስላል ይሆናል። ትክክለኛ ራዕይ ለስኬታችን ወሳኝ ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ወጣቶች የራሳቸውና የቤተሰቦቻቸው ሕይወት እንዲቀይሩና በሀገሪቱ ልማት እና የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፦** ኢትዮጵያን ጨምሮ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ብዙ ወጣቶች አሏቸው። በቀድሞው መረጃ መሰረት 87 በመቶ ወጣቶች በታዳጊ ሀገራት ይገኛሉ። እንደ ሀገርም ሆነ ዓለም አቀፍ በወጣቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው። ምሁራንም በዚህ ጉዳይ ላይ ሊሰሩ ይገባል። በትውልዱ ወይም ወጣቱ ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ በሀገሪቱ የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ እንደመስራት የሚቆጠር ተግባር ነው።

ብዙ ሀገሮች ያደጉት በወጣቶች ላይ በመሥራት ነው። ስለዚህ እንደ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት እና ሀገር በወጣቶች ላይ መስራት አስፈላጊ ነው። የሀገራችን የትምህርት ስርዓትም የወጣቶችን የወደፊት እጣ ፈንታ በደንብ የሚያመለክት መሆን አለበት። ወጣቶች ላይ ብንሠራ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው እና ለአገራቸው ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ:: እንደ መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተሰብ እና ማኅበረሰብ የሚሠሩ ሥራዎች ሁሉ ወጣቶችን የሚያበቃ እና መንገድ የሚያሳይ መሆን አለበት።

ወጣቶች ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን ተጠቅመው የራሳቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን ሕይወት ለማሻሻልና የወደፊት ሕይወታቸውን ስኬታማ ለማድረግ በንቃት መሥራት አለባቸው። ተሠርተው ከሚያገኙት ገቢም መቆጠብ አለባቸው።

ብዙ ወጣቶች ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው ሥራ በመፈለግ ሰፊ ጊዜያቸውን ያጠፋሉ። የስራ እድል መፈለግ ብዙ ፈተናዎች አሉት:: የስራ የማግኘት ዕድልም ጠባብ ነው:: ስለሆነም ወጣቶች ተቀጥረው ከመሥራት የራሳቸውን ስራ መፍጠር ላይ ማተኮር አለባቸው ባይ ነኝ። ተቀጥሮ መሥራት እና የራስን ሥራ ፈጥሮ በግል መሥራት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ተቀጥሮ የሚሠሩ ሰው ገቢው በወር አንድ ጊዜ ብቻ ነው። የራሱ የግል ሥራ የሚሠራ ሰው ግን በየቀኑ ገቢ ያገኛል። የራሱን ስራ ፈጥሮ የሚሠራ ሰው ከራሱ አልፎ ለሌሎች ሰዎች የስራ እድል ይፈጥራል። በዚህም እንቅስቃሴው ለአገርም ይተርፋል።

ወጣትነት የሚሮጡበት እና የሚሠሩበት ጊዜ ነው፤ ስለሆነም ወጣቶች ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን በጥበብ መጠቀም አለባቸው። ወጣቶች አልባሌ ቦታ መዋልና ከመጥፎ ጓደኞቻቸው ጋር ከመዋል ራሳቸውን መቆጠብ አለባቸው። ይህ ትውልድ ስለራሱ እና ለቀጣይ ትውልድ መልካም ነገርን ለማስተላለፍ ተግቶ መስራት ይጠበቅበታል።

**አዲስ ዘመን፦ የጳጉሜን ቀናት በተለያዩ ስያሜዎች ተሰይመው በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ በተለያዩ መርሀ ግብሮች ተከብረው አልፈዋል። በዚህም መሰረት ጳጉሜ 1 ”የሽግግር ቀን‘ ተብሎ ተከብሯል። ሽግግር ከአሮጌው ዓመት ወደ አዲሱ ዓመት መሻገርም ጭምር ነውና ከዚህ በመነሳት ”ሽግግር‘ የሚለውን ቃል እንዴት ይገልጹታል?**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፦** በዚህ አገላለጽ ሽግግር የሚለው ቃል ከአሮጌው ዘመን ወደ አዲስ ዘመን መሸጋገርን ያመለክታል። ወደ አዲሱ ዓመት ከመሻገራችን በፊት ጠራርገን ማስወገድ ያለብን ብዙ አሮጌ ነገሮች አሉን። ከአሮጌው አመለካከታችን ወጥተን በአዲስ እይታ ወደ አዲሱ ዓመት መሄድ አለብን። አመለካከታችን የወደፊት ሕይወታችንን ይወስናል። በአዲሱ ዓመት እንደ ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ እና ሀገር በአዲስ አስተሳሰብ፣ ሂደት እና ራዕይ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገር አለብን።

**አዲስ ዘመን፦ አዲሱን ዓመት በማስመልከት ለሕዝብ እና ለሀገሪቱ የሚያስተላልፉት መልዕክት ይኖርዎ ይሆን?**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፦** በአዲሱ ዓመት (2017 ዓ.ም) ሁሉም የሀገሪቱ ሕዝቦች በሰላም ወጥተው የሚገቡበት፣ በፍቅር እና በደስታ አብረው የሚኖሩበት፣ ሰዎች በነፃነት ወደ ፈለጉት ቦታ ተንቀሳቅሰው የሚሰሩበት ወቅት እንዲሆን ትልቁ ምኞቴ ነው። ሰዎች ወደፈለጉበት አቅጣጫ ተንቀሳቅሰው የሚነግዱበት፣ የሚማሩበት እና በሁሉም መንገድ የተሳካ ዓመት እንዲሆንላቸውም እመኛለሁ።

በአዲሱ ዓመት ሰዎች በነገሮች የሚጣሉበት ሳይሆን፣ ያለው ሰው የሌለውን የሚረዳበት፣ የሚመራው አመራር ለሚመራው ሕዝብ የሚያስብበት፣ ሰዎች እርስ በእርሳቸው የሚከባበሩበት ዓመት እንዲሆን መሻቴ ነው። ያለፈው ነገር ለሕዝባችን እንደ ሕልም ሆኖ የሚደነቁበት ጊዜ እንዲሆን እመኛለሁ።

**አዲስ ዘመን፦ ስለሰጡን ጊዜ ከልብ እናመሰግናለን።**

**ዘሪሁን (ዶ/ር)፦** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ በያዝነው ዓመት አጋማሽ ይካሄዳል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ዋናው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ጉባዔ በያዝነው የ2017 ዓ.ም አጋማሽ እንደሚካሄድ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ። የትግራይና አማራ ክልሎችን ሳይጨምር በሁሉም ክልሎችና ሁለቱ የከተማ መስተዳድሮች አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቱ እስከ ጥቀምት ወር 2017 ዓ.ም መጨረሻ ይጠናቀቃል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ ላለፉት ሁለት ዓመታት ከአምስት ወራት ክልሎችንና ወረዳዎችን በሚገባ የመለየት ሥራዎች መከናወናቸውን ጠቅሰው፤ አዲሱ ዓመት መሠረታዊ የሆኑና ማግባባት ያልቻሉ ምክንያቶችን ነቅሶ በማውጣት የጋራ ውይይት የሚያደርጉበት እንደሆነ አስታውቀዋል። ለዚህም 2017 ዓ.ም ለኮሚሽኑ ወሳኝ ጊዜ መሆኑን ተናግረዋል።

ኮሚሽኑ እስከ ጥቅምት ወር 2017ዓ.ም መጨረሻ ድረስ የፌዴራልን ጨምሮ በ10 ክልሎችና ሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቱን እንደሚያጠናቅቅም ገልጸዋል።

በልየታው ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሕዝቡ አጀንዳውን ሰብስቦ የሚሰጥበትን ሂደት በማመቻቸት ሰፊ ሥራዎች መሰራታቸውን ኮሚሽነሩ ጠቅሰው፤ በአሁኑ ወቅትም ከአንድ ሺህ በላይ ከሚሆኑ ወረዳዎች አጀንዳ እየተሰበሰበ ይገኛል ብለዋል።

የተሰባሰቡ አጀንዳዎች ከክልልና ከፌዴራል ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በ2017 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ዋናው ሀገራዊ የምክክር ጉባዔ ይካሄዳል በማለት፤ በዚህ ሂደት ውስጥ በቅርቡ ለሀገራዊ ምክክር ጉባዔው ተሳታፊዎችን በመለየት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በሲዳማ፣ በማዕካላዊ ኢትዮጵያ፣ በሀረሪና ሌሎች ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የአጀንዳ አሰባሰብ ሥራ መከናወኑን ጠቅሰዋል። ከሚቀጥሉት ቀናት ጀምሮ በአፋርና ሱማሌ ክልሎች ተመሳሳይ ሥራዎች እንደሚሰሩም አስታውቀዋል።



ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ

እስከ ጥቅምት ወር 2017ዓ.ም መጨረሻ ድረስ የፌዴራልን ጨምሮ በ10 ክልሎችና ሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቱ ይጠናቀቃልም ነው ያሉት።

በትግራይና አማራ ክልሎች ያሉ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ሲሄዱ በቀጣይነት በእነዚህ አካባቢዎችም ተመሳሳይ ሥራዎች እንደሚከናወኑ ኮሚሽነሩ ተናግረዋል። እነዚህ ተግባራት ሲፈጸሙ በ2017 ዓ.ም አጋማሽ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ጉባዔ ይካሄዳል ሲሉ ገልጸዋል። ይህም ለኮሚሽኑ በተሰጠው የሥራ ጊዜ ገደብ ውስጥ የሚፈጸም እንደሆነ ነው ያመላከቱት። ከምክክር ጉባዔው በኋላ የሚሠሩ ሥራዎችም ሕዝብና መንግሥት የሚወስኑበት ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል።

ኮሚሽነሩ፤ "ዓመቱ ለኢትዮጵያውያን የሰላም፣ የጤና፣ ከሁሉም በላይ ያለፉ ችግሮቻችንን ተገንዝበን ተጸጽተን፣ እርስበርሳችን ታርቀን ወደ ሀገራዊ እድገት የምንሄድበት ጊዜና ዘመን እንዲሆንልን እመኛለሁ" በማለትም የአዲሱን ዓመት የመልካም ምኞት መግለጫ መልዕክታቸውን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተላልፈዋል።

# ሉዓላዊነትን ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የታሪክ ምሁርና የህገር ሽማግሌ ፕሮፌሰር አደም ካሚል እንደሚሉት፣ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ የኖረች ሀገር ናት። ኢትጵያውያን ከዳማት ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የሀገራችንን ሉዓላዊነት በጋራ መጠበቅ የቻልን ሕዝቦች ነን። በየትኛውም ዘመን የነበሩና ያሉ ኢትዮጵያውያን የሀገራቸውን ሉዓላዊነት የማስጠበቅ ጠንካራ አቋም ያላቸው በመሆናቸው በተለያየ ጊዜ ሀገራችንን ለመድፈር የመጡ ወራሪዎች ተሳክቶላቸው ሀገራችንን የተቆጣጠሩበት አጋጣሚ የለም።

በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት ሥርዓትን ለማበጀት ብዙ ጦርነቶች ተካሂደዋል ያሉት የታሪክ ምሁሩ፤ ባዕድ ሲመጣ ግን ሕዝቧ ምንጊዜም ሉዓላዊነቷን ለማስከበር በአንድነት ዘብ የሚቆም መሆኑን ተናግረዋል። በዚህም ምክንያት በታሪካችን ኢትዮጵያ አንድም ጊዜ ሉዓላዊነቷ ጥያቄ ውስጥ ገብቶ እንደማያውቅ ይናገራሉ።

ሉዓላዊነት የአንድ ሕዝብ የክብር ምልክት ነው ያሉት ደግሞ የፖሊሲና የሕዝብ አስተዳደር ምሁሩ ዶ/ር ገመቹ አራርሳ ናቸው።

ዶክተር ገመቹ እንዳሉት፤ የጥንት አባቶች የሕዝብ ክብር ምንነትን፤ የሉዓላዊነትን ዋጋ ጠንቅቀው የተረዱ በመሆናቸው ሀገራቸውን ከጠላትና ሊደፍራት ከቃጣው ጠላት ሁሉ ጠብቀው አስረክበውናል። የዛሬዋ ሉዓላዊት ኢትዮጵያ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎባታል።

የመረጃ መለዋወጫ መሳሪያዎች፣ የቴክኖሎጂ እውቀት ባልነበረበትና በርካታ ምቹ ባልሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ሀገሬን ለማንም አሳልፌ አልሰጥም ብለው ታግለው ዛሬ ያደረሷትን ሀገር የዛሬው ትውልድም ይህን ክብር አስጠብቆ ለመጪው ትውልድ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት ያሉት ዶክተር ገመቹ፤ የዜጎች ክብር ሊጠበቅ፣ የፖለቲካ ልዩነቶቻችንን ወደ አንድ ማምጣት የምንችለው ሀገር ሉዓላዊ ሆና ስትኖር ብቻ ነው ይላሉ።

ሌላው የፖለቲካ ምሁር ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር) እንዲሁ ኢትዮጵያውን ሉዓላዊነታችንን ለማስከበር የሄድንበት ርቀት ልዩ የሚያደርገን መሆኑን ይናገራሉ።

እርሳቸው እንዳሉት የውስጥ አለመግባባቶችና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ቢኖሩብንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጠላት ወራሪ ጋር ባደረጋቸው ፍልሚያዎች ሁሉ በሉዓላዊነቱ ላይ የማይደራደር መሆኑን አሳይቷል። ያልተግባባ፣ የተጋጨ፣ እርስ በእርሱ የተዋጋ ሕዝብ ጠላት ሲመጣበት አብሮ ተሰልፎ የሚወጋ፣ ለጠላት እጁን የማይሰጥ ሕዝብ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን የጋራ ታሪካችንም ትርክታችንም ነው ብለን የምንጠቅሰው ትልቁ ነገር ሉዓላዊነታችንን ለማስከበር የሄድንበት ርቀት፤ በሉዓላዊነታችን የማንደራደር መሆናችንን ነው።

ዶክተር ሙሉጌታ፤ ጠቅላላ ዓለም በኢትዮጵያ ላይ በተነሳበት ጊዜ ለምሳሌ፣ አውሮፓና አሜሪካ ኢትዮጵያ ላይ ሲዘምቱ ሳንንበጥና ወደ ኋላ ሳንል ተቋቁመን ዛሬ ያለንበት አደባባይ ላይ መሆናችንን አሳይተናል። ባዕድ ባሴረ እና በጻፈ ቁጥር የምንወድቅ ቢሆን ኖሮ ሉዓዊነታችንን ማስከበር የማንችል፣ በአካባቢያችንም የተናቅን እንሆን ነበር ብለዋል።

ሉዓላዊነት በየፈርጁ ይገለጻል ያሉት ገመቹ (ዶ/ር)፣ ሌላ የውጪ አካል ጫና ሳይፈጥርበት የስልጣን ምንጭ ሕዝብ ሲሆን፤ የሕዝብ ሉዓላዊነት በዚህ ይገለጻል፤ የአንድ ሀገር መንግሥት የሕዝብን ፍላጎት መሠረት አድርጎ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን ያለ ምንም ጫና፣ የውጪ አካል ጣልቃ ገብነት እና ግፊት በራሱ መወሰን ሲችል ሉዓላዊነት በዚህም ይገለጻል ብለዋል።

ሉዓላዊነት ታላቅ ዋጋ ያለው ፅንሠ ሐሳብ ነው ያሉት ዶክተር ገመቹ ፤ እንደ ሕዝብ ሀገራችንን ከውጪ ጠላት መጠበቅ አለብን ብለዋል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ሌላ ሀገር ወርራ አታውቅም ያሉት ምሁሩ፤ ወራሪ ጠላት ሲመጣባት ግን ትልቁ ፈተና የነበረው ከሌላው ጋር የሚያብሩ ጥቂት ባንዳዎች መኖራቸው ነበር፤ በመሆኑም ከውስጥም ሆነ ከውጪ ጠላት ጋር አብሮ የሀገራችንን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ አካላትና ግለሰቦችንም ጭምር መታገል እንደሚያሻም አበክረው ይናገራሉ።

ዶክተር ገመቹ እንዳሉት፣ ኢትዮጵያ በታሪኳ ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሉዓላዊት ሀገር ሆና የቆየች ሀገር ናት፣ ይህ ትውልድም የዚህ የታሪክ ኃላፊነት አለበት። የሀገራችን ሉዓላዊነት ጥያቄ ውስጥ ሊከት የሚችል ምንም አይነት ክፍተት መፍጠር የለብንም፤ በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ዘንድ ተከብረን መኖር የምንችለው ሀገር ስትከበር ነው። ትውልዱም በሀገሩ አንድነት፣ በብሔራዊ ጥቅሙና በሉዓላዊነቱ የማይደራደር መሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

# ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጠት በሚያስችል መልኩ የሚተዳደሩ ሲሆን የአምራች ዘርፉን በሚገባ እየደገፉ ይገኛሉ።

አጠቃላይ እነዚህን ፓርኮች ለማልማት የወጣው ገንዘብ ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር እንደሚሆን የሚጠቅሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ መንግሥት ካለው ቁርጠኝነት ፓርኮቹን በርካታ ገንዘብ አውጥቶ መደገፉን ይናገራሉ።

እስካሁንም በፓርኮቹ ውስጥ 85 በመቶ የሚሆኑ ሼዶችና የለማ መሬትም መያዙንም አስታውቀዋል። 15 በመቶ ያህሉን እስካሁን ባለሀብቶች ገብተው እየተጠቀሙበት እንዳልሆነም ጠቁመዋል። በተለያዩ ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ሁኔታዎችም ሼዶችን የመልቀቅ ሁኔታ እንዳለ አመላክተዋል። ለወደፊት የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ሰፊ ቦታ መኖሩንም ገልጸዋል።

በፓርኮቹ ውስጥ ካሉት 147 የሚሆኑ ኢንቨስተሮች 51 በመቶ ያህሉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እንደሆኑ በመጥቀስ፤ ከዚህ ቀደም ፓርኮቹ ሲሠሩ በዋናነት ታሳቢ ተደርጎ የነበረው የኤክስፖርት ምርቶች የሚመረቱበት እንዲሆን ነበር ብለዋል። በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በስፋት እየገቡና ከውጪ ባለሀብቶች ጋር እየሰሩ መሆናቸውን አብራርተዋል። 70ሺህ የሚሆኑ ሠራተኞችም በእነዚህ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተቀጥረው እንደሚሰሩ ጠቁመዋል። አብዛኞቹም ሴቶችና ወጣቶች መሆናቸውን ተናግረዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደሚሉት፤ በፓርኮቹ አማካኝነት ኤክስፖርት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ኤክስፖርት ማድረግ ተችሏል። ይህ ቁጥር ብዙ የሚባል አይደለም። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ፓርኮቹ የወጪና ገቢ ምርት ሚዛን ላይ እንዲያተኩሩ ተደርጓል።

የኤክስፖርት አፈጻጸም ደካማነት፣ የሀገሪቱ የጸጥታ ችግሮች፣ የመሠረተ ልማት እጥረት ለፓርኮቹ ተግዳሮት የፈጠሩ ጉዳዮች መሆናቸውን፤ ከዚህም ባሻገር በኢንቨስተሮች በኩል የሚነሱ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ ቢሮክራሲ፣ መሠረተ ልማት፣ የቁጥጥር ሥርዓትና የህጎች በፍጥነት መቀያየር ቅሬታዎች መኖራቸውን ዋና ሥራ አስፈጻሚው አንስተዋል። እነዚህንና መሰል ችግሮችን በመቅረፍ በልዩ ትኩረት ፓርኮቹን ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለመቀየር እየተሠራ እንዳለም ነው የገለጹት።

"ስናለማ የቆየነው በተለይም ኤክስፖርትን መሰረት ያደረገ ፓርክ ነበር። አሁን ላይ ተጨማሪ ሥራዎችን በማካተት ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን መቀየር አለብን" ብለዋል። ይህም በቀጣዮች ከአምስት እስከ አስር ዓመታት ውስጥ ተፈጻሚ እንደሚሆን ነው የገለጹት። ለዚህም የህግ ጉዳዮችን ጨምሮ በርካታ ሂደቶች መጠናቀቃቸውን አብራርተዋል።

ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ፍላጎቱ በሀገሪቱ ተግባራዊ የተደረጉ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ተከትሎ ሲሆን፤ ፓርኮቹ አሁን ካሉበት አፈጻጸም የላቀ የኢኮኖሚ አበርክቶ እንደሚኖራቸው ጠቅሰዋል። ኢንዱስትሪን መሰረት ያደረጉ የንግድ ሥርዓቶችን ለመዘርጋትና ኤክስፖርትን በማብዛት የወጪ ገቢ ንግድ ሚዛኑንም ይበልጥ ለማስጠበቅ ይረዳል ብለዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ፓርኮቹ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ሲቀየሩ ማኑፋክቸሪንግ ብቻ ሳይሆን የንግድና ሎጀስቲክስ እንዲሁም የፋይናንሺያል አገልግሎት በፓርኮች ውስጥ እንዲኖሩ ያስችላል። በተለይም ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የውጭ ባንኮች ገብተው የምንዛሪ አገልግሎት እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህም የዘመናዊነት ማዕከልነታቸውን ያስጠብቃል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ፤ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገር ኬንያ ብልጫ ያለው ኢኮኖሚ ገንብታለች። ሆኖም የኢትዮጵያ ውድድር በዓለም አቀፍ ደረጃ በመሆኑ አዳዲስ የማክሮ ኢኮኖሚ ለውጦችን ተግባራዊ ማድረጓ የግድ ነበር ይላሉ። ከዚህ ውስጥም ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እሳቤን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆን ይጠቅሳሉ።

አቶ ዘመዴነህ፤ ለማኑፋክቸሪንግ ተብለው የተከፈቱ ፓርኮች የአገልግሎት ዘርፉን ጨምሮ ተጨማሪ አገልግሎት እንዲሰጡ ታስበው ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የሚያደርጉትን ግስጋሴ በመደገፍ የዶክተር ፍሰሃን ሃሳብ ይጋራሉ። ዘመናዊ የሆኑ በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ የኢኮኖሚ ዞኖች ስኬት የተገኘው በአምራች ዘርፉ ብቻ ሳይሆን የአገልግሎት ሴክተሩንም በመያዛቸው ጭምር ነው ብለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በዋጋም በጥራትም ተወዳዳሪ መሆን የሚቻለው ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ሲኖር ነው በማለት፤ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ሲኖር ታላላቅ ኩንያዎች ገብተው ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪ የማድረግ እድሉ እንዳለቸው ያብራራሉ።

ልዩ ኢኮኖሚ ዞን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን ስላለበት የውጭ ኢንቨስትተሮችን ጨምሮ የግል ሴክተሩን በብዛት ማሳተፍ እንደሚቻልና፤ ለዚህ ደግሞ በቴሌኮም፣ በትራንስፖርትና በባንኪንግ ሲስተም የታዩ ለውጦች አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥሩ ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት ዱባይን ጨምሮ በርካታ ልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች በዓለም አቀፍ ደረጃ መኖራቸውን ጠቅሰው፤ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነትም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊታወቁ በሚችሉ ነጻ የንግድ ቀጣናና ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ ባሉት ኢንዱስትሪዎች አማካኝነት እንደሚሆን አስገንዝበዋል።

በሚቀጥሉት 25 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እስከ አንድ ነጥብ 7 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሊደርስ እንደሚችል፤ በሚቀጥሉት 40 ዓመታት ውስጥ ደግሞ በዓለም ውስጥ ካሉት 20 ትላልቅ የኢኮኖሚ ባለቤቶች ከሚባሉት ኢትዮጵያ አንዷ እንደምትሆን፤ ምናልባትም ከነ ሳውዱ አረቢያና ቱርክ ልትበልጥ እንደምትችል ዓለም አቀፍ ትንበያዎችንና ጥናቶችን መነሻ አድርገው የሚገልጹት አቶ ዘመዴነህ፤ እዚህ ላይ ለመድረስ ከቀጣናዊ የንግድ ውድድር ወደ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት መግባት እንደሚያስፈለግ እና ለዚህ ደግሞ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ወሳኝ ሚናን እንደሚጫወቱ ይገልጻሉ።

# ጥራትና ምላሽ ሰጪ የጤና ስርዓት ለወጣቶችና አፍላ ወጣቶች

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ በቁጥር የበዙ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ይገኛሉ። እነዚህ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የጤናና በሌሎችም ሴክተሮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አላቸው። ይህንኑ መብታቸውን ለማስከበር ታዲያ ጤና ሚኒስቴርና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ለወጣቶች ቅድሚያ በመስጠት የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ስራዎችን ሲያከናውኑ ቆይተዋል። ይሁንና ለወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የሚሰጠው አገልግሎት ወጣቱን የሚያረካና በሕይወቱ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጣ እንዲሆን በጥራት ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራት እናዳለበት ታምኖበታል። ለዛም ነው አምስተኛው የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና ጉባኤ «ተደራሽነትና ጥራት፤ ምላሽ ሰጪ የጤና ስርዓት ለሁሉም አፍላ ወጣቶች» በሚል መሪ ቃል ሰሞኑን የተካሄደው።

የጤና ሚኒስቴር ሚንስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ እንደሚናገሩት፣ ከዚህ በፊት የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት በአብዛኛው ትኩረቱ ተደራሽነት ላይ ነበር። ነገር ግን ተደራሽነት ብቻውን በቂ ባለመሆኑ ከተደራሽነት ቀጥሎ ጥራት ላይ፣ ከጥራት በኋላ ደግሞ ምላሽ መስጠት የሚችል የጤና አገልግሎት ለወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። የጤና አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ወጣቶች በሁሉም አቅጣጫ ለሚፈልጉት ነገር ሁሉንም ያማከለ እንዲሆን ታሳቢ ባደረገ መልኩ አምስተኛው ጉባኤ ተካሂዷል። ስራው የአንድ ሴክተር ባለመሆኑም ነው በጉባኤው ላይ ትምህርት ሚንስቴርና የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ተሳታፊ የሆኑት።

የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ ተቀይሮ የተለያዩ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። ከነዚህ ስራዎች ውስጥ አንዱ መስተካከል፣ መታደስና መቀየር ያለባቸው ነገሮችን ማከናወን ነው። ፖሊሲው መከላከል ላይ ያተኮረ ቢሆንም አክሞ ማዳንንም ያካተተ ነበር። ከዚህ አንፃር ወጣቶች ብዙ ነገር በመያዛቸው አሁንም መከላከል ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል። ወጣቶች በተለያዩ ነገሮች ሲያዙ፣ ሲቸገሩና ሲታመሙ፣ ከአእምሮ ሕመም ጀምሮ ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ ሕመሞች ሲጠቁ እንደ ሀገር አክሞ የማዳን አቅም ያስፈልጋል።

ይህንንም ለማድረግ መንግስት ስትራቴጂ በመቅረፅ ከሰነድ አንስቶ የሚተገበሩ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። በተጨማሪም በሁለተኛው የጤና ትራንስፎርሜሽን እቅድና በመካከለኛ ዘመን የጤና እድገትና ኢንቨስትመንት እቅድ ውስጥ የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤና ስትራቴጂ የስነ ተዋልዶ ጤና ስትራቴጂዎች ተካተዋል። ስትራቴጂዎች የሚተገበሩት ደግሞ በራሳቸው በወጣቶች፣ በሴክተሮች የበለጠ ደግሞ በማኅበረሰቡ ነው። አሁን ደግሞ አፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤናቸውን ለመጠበቅ ወደራሳቸው የሚመለከቱበት ግዜ ነው።

ሚንስትሯ እንደሚናገሩት፣ ጤና ሚኒስቴር የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶችን የጤና አገልግሎት ተደራሽነትና ጥራትን ለማሻሻል በርካታ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። የ2017 ዓመት ደግሞ የአገልግሎት ዓመት እንዲሆን በመሰየሙ በየትኞቹ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት ዙሪያ መስራት እንደሚያስፈልግ መነጋገር ያሻል። ከአመጋገብ ስርዓት አንስቶ የጤና መረጃዎችን እስከመጠቀም ድረስ ያለውን ሁኔታ በቅጡ ተረድቶ ስራዎችን ማከናወን ይገባል። ምክንያቱም ከጤና መረጃዎች በላይ የሆኑ መረጃዎችን የሚቀበል ትውልድ በመሆኑ ነው። ስለዚህ የሚወሰደውም የሚሰጠውም መረጃ ምን ያህል ራስን፣ ቤተሰብንና ትውልድን የሚጠቅም እንደሆነ ወጣቱ ማየት አለበት።

ብዙ ወጣቶች በዓለም ላይ ለሳይበር ሴኪዩሪቲ ከዛም በበለጠ ደግሞ በማኅበራዊ ሚዲያ በሚመጡ ነገሮች ጥቃት የሚደርስባቸው ናቸው። በኢትዮጵያም ቴክኖሎጂው እያደገ በመጣ ቁጥር የኢንፎርሜሽን ወረርሽኝ እየጨመረ ይመጣል። ስለዚህ ቴክኖሎጂውን ተከትሎ የሚመጣውን መረጃ በተገቢው መንገድ




መጠቀም ካልተቻለ ወጣቱን ስለሚጎዳ በትብብር መስራት ያስፈልጋል። ለዚህም ጤና ሚኒስቴር በአየር ሰዓት ፕሮግራሙ፣ በማኅበራዊ ሚዲያው ወጣቱን የሚጠቅሙና መረጃዎችን የሚያገኝበትን ስራዎች ከአጋር ድርጅቶችና ከሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን እያከናወነ ይገኛል።

ጤና ሚኒስቴር አካል ጉዳተኛ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶችን ያማከሉ ስራዎችን ሲያከናውን የቆየ ቢሆንም የተሰራው ስራ ግን በቂ ነው ማለት አይቻልም። ስለዚህ ሁሉንም ወጣቶችን ያማከለ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል። አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን በጤናው መስክ ተጠቃሚ ሚሆኑባቸውን ስራዎች መስራት ይገባል። በተለይ ደግሞ አፍላ ወጣቶችና ወጣቶች የሚያገኙት መረጃ ሙሉ እንዲሆን ማድረግ ትምህርት ሚኒስቴርና የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ጨምሮ የሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች ድርሻ ነው። አጋር ድርጅቶችም ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን መደገፍ ይኖርባቸዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ፣ በወጣቶች ላይ እየተከናወኑ ካሉ ስራዎች መካከል አምና የተጀመረው «የብልህ ጅምር» የተሰኘው መርሃ ግብር አንዱ ሲሆን ከዚህ በበለጠ ደግሞ ሌሎች ፕሮግራሞችን በመቅረፅ በወጣቶች ላይ ስራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል። አፍላ ወጣትነት ደግሞ በብዙ መልኩ ተጋላጭነት የሚታይበት፣ ካልታሰበ እርግዝና አንስቶ ለበርካታ የጤና እክል የሚጋለጡበት ነው። ከዚህ አንፃር የስነ ተዋልዶ ጤና ስራ የሁሉም ስራ ሊሆን ይገባል። በስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት የሚከናወኑ ትላልቅ ስራዎች ወጣቱን ያማከሉ፣ ወጣቱን መድረስ የሚችሉ ከትምህርት ቤት እስከ እያንዳንዱ መኖሪያ ቤት ድረስ ማንም ሰው በየትኛውም ግዜ ማግኘት የሚገባውን አገልግሎት እንዲያገኝ ከተሰራ ከተደራሽነት በለጠ ጥራት ያለው መረጃ አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል። ከዚህ አንፃርም በርካታ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

በዩኒቨርሲቲዎች፣ በወጣት ማእከላት፣ በስራ ቦታዎች፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች በስነ ተዋልዶ ጤና ወጣቶችንና አፍላ ወጣቶችን ያማከሉ ስራዎች ተጠናክረው ይሰራሉ። ነገር ግን ስራው በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ብቻ የሚሸፈን ሳይሆን ወጣቶችን ይበልጥ የሚያሳትፍ የአቻ ለአቻ የጤና ትምህርት በጤና ተቋማት ውስጥና በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

የጤና ሚንስትር ዲኤታ ዶክተር ደረጄ ዱጉማ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፣ የዘንድሮውን አምስተኛው የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና ጉባኤ ከባለፈው ጉባኤ በብዙ መልኩ ለየት ያደርገዋል። የዘንድሮው ጉባኤ መሪ ቃል «ተደራሽነትና ጥራት፤ ምላሽ ሰጪ የጤና ስርዓት ለአፍላ ወታቶችና ወጣቶች» የተባለውም በቀጣይ የሚከናወኑ ስራዎች በዚህ ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው ነው። ተደራሽነት ሲባል ደግሞ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚገኙ እንደመሆናቸው በነዚህ ቦታዎች ላይ አስፈላጊ የሚባሉ የጤናና በሌሎች ሴክተሮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አላቸው። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግስትና

> **«የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ ተቀይሮ የተለያዩ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። ከነዚህ ስራዎች ውስጥ አንዱ መስተካከል፣ መታደስና መቀየር ያለባቸው ነገሮችን ማከናወን ነው። ፖሊሲው መከላከል ላይ ያተኮረ ቢሆንም አክሞ ማዳንንም ያካተተ ነበር። ከዚህ አንፃር ወጣቶች ብዙ ነገር በመያዛቸው አሁንም መከላከል ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል። ወጣቶች በተለያዩ ነገሮች ሲያዙ፣ ሲቸገሩና ሲታመሙ፣ ከአእምሮ ሕመም ጀምሮ ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ ሕመሞች ሲጠቁ እንደ ሀገር አክሞ የማዳን አቅም ያስፈልጋል።»**

ሌሎች አጋር አካላት ለወጣቶች ቅድሚያ በመስጠት አገልግሎቱን እንዲያገኙ ሲሰራ ቆይቷል።

ጥራት ሲባል ደግሞ የሚሰጡ አገልግሎቶች የወጣቶችና የአፍላ ወጣቶችን ፍላጎት የሚያረካ፣ በሕይወታቸው ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጣ መሆን አለበት። አዲሱ አራተኛው የኢትዮጵያ የጤና ፖሊሲ ለአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል። ይህም በተለያዩ ምላሽ ሰጪ የጤና ስርዓቶች ውስጥ የሚካተት ስለሆነ የሚገነባው የጤና ስርዓት ለአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች የቅድሚያ ቅድሚያ እንደሚሰጥ የሚሰጥ ነው።

ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ ስራዎች ለወጣቶችና አፍላ ወጣቶች በጤና ሚኒስቴር በኩል ተከናውነዋል። በተለይ ደግሞ የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እቅዶች ወጣቶችና አፍላ ወጣቶችን መአከል ያደረጉ እንዲሆኑ ተደርጓል። በእቅድና በዶክመንት ብቻ ሳይሆን በስራዎችም እንዲገለጥ ጥረት ተደርጓል። በዋናነት በየደረጃው መዋቅር እንዲኖርና ካውንስል በየደረጃው ተቋቁሞ ወጣቶች በተለያዩ ደረጃዎች እርስ በርሳቸው እንዲማማሩ ማድረግና ድምፃቸው እንዲሰማ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ወጣቶች ለጤና መረጃ ያላቸው ተደራሽነት እንዲሻሻል ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል።

የወጣቶችና አፍላ ወጣቶችን ፍላጎት ማሳካት የሚቻለው ሁሉም ሲረባረብ ነው። ስለዚህ ስራው የጤና ሚኒስቴር ብቻ ባለመሆኑና ዘርፈ ብዙ ስራ የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሁሉንም ሴክተር መስሪያ ቤቶች ርብርብ ይጠይቃል። በተለይ ወጣቶች እርስ በርሳቸው ተደራጅተው የበለጠ ለጤናቸውና ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳያቸው የሚጠቅሙ ስራዎችን ማከናወን ይኖርባቸዋል። በቀጣይም በሀገሪቱ ያሉ ርካታ ጎጂ ባህላዊ ደርጊቶችን ለመቀነስ ጠና ሚኒስቴር ከሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን እቅድ አስቀምጦ ይሰራል።

ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በአብዛኛው ወጣቶችን እያጠቁ እንደመሆናቸው በነዚህም ላይ ትርጉም ያለው ስራ ለመስራት በአስርና በሶስት ዓመት የጤና እቅድ ውስጥ በተለየ መንገድ ተቀምጦ የሚሰራበት ይሆናል።

ከዚህ ውጪ ወጣቶች በአብዛኛው የሚገኙት በትምህርት ተቋማት ውስጥ እንደመሆኑ በዩኒቨርሲቲ፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮችና በሌሎችም የተለያዩ የልማት አካባቢዎች ላይ በወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ላይ ያተኮሩ ስራዎችን ለመስራት ጥረት እየተደረገ ነው። ኢትዮጵያ ከእዳ ወደ ምንዳ በምታደርገው ሽግግር ፈጠራና ፍጥነት በጣም ወሳኝ ናቸው። ስለዚህ ወጣቶች ለፈጠራና የተጀመሩ ስራዎችን በፍጥነት ለመጨረስ ዋነኛና በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከታቸው በመሆኑ ኢትዮጵያን በሁለንተናዊ መልኩ ለመቀየር የራሳቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል።

የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ እንደሚሉት የአፍላ ወጣትነት እድሜ የኅብረተሰቡን የቀጣይ ትውልድ ማፍራት ሁኔታ የሚወስን ነው። በተለይ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የወጣት ቁጥራቸው ከጠቅላላው ሕዝብ አንፃር ከፍተኛ የሆኑባቸው ሀገራት ለወጣቶች አስቻይ ሁኔታዎች ካልተፈጠሩ፣ ተሳታፊነታቸውና ተጠቃሚነታቸው ካልተረጋገጠ ለሚታሰበው ብልፅግና እንቅፋት ይሆናል። ስለዚህ በአፍላ ወጣቶችና በወጣቶች ዙሪያ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

ወጣቶች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሯዊ፣ ማኅበራዊ ለውጦች የሚከሰትበት የእድሜ ክልል ላይ የሚገኙ በመሆናቸው የሕይወታቸው ሂደትና ኡደት ልዩ ትኩረት የሚሻ ነው። ምክንያቱም በዚህ እድሜ ክልል በሚፈጠሩ ስሜታዊነት፣ የአቻ ግፊቶች፣ የመረጃ እጥረት የተነሳ አፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ለጤናና ለተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ይሆናሉ። የስነ ተዋልዶ ጤና ችግር ደግሞ ለኤች አይ ቪ ኤድስ ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች፣ ላልተፈለገ እርግዝና፣ ለጽንስ ማቋረጥ፣ ለአደንዛዥ እፆች፣ ለአልኮል መጠጦች፣ ለአእምሮ ጤና እክል፣ ለአካል ጉዳትና ለሌሎችም ችግሮች ተጋላጭ ያደርጋቸዋል።

ስለዚህ አፍላ እድሜ ላይ ያሉ ታዳጊዎችና ወጣቶች ጤናቸው በተሟላ መልኩ እንዲጠበቅ ሁሉም ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል። ጤናቸው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ እርስ በርሳቸው ተቀራርበው የሚወያዩበትና ራሳቸው የመፍትሄ አካል የሚሆኑበት መንገድ መዘጋጀት ይኖርበታል። ወጣቶች በራሳቸው የእድሜ ክልል ውስጥ የራሳቸውን ችግር ሲነጋገሩ ይበልጥ ግንዛቤ ይኖራቸዋል።

ሚኒስትሯ እንደሚያብራሩት እንደ ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ደረጃ ባሉ ከ3 ሺ በላይ በሚሆኑ ወጣት ስብዕና መገንቢያ ማእከላት ውስጥ የጤና አገልግሎቶች ይሰጣሉ። ነገር ግን በሚፈለገው ልክ አገልግሎቱ እየተሰጠ ባለመሆኑ በላይ የስነ ተዋልዶ ጤናን በሚመለከት ንግግር የሚያስፈልገው ጉዳይ በመሆኑ ለዚህ አፅንኦት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል።

ከዩኒሴፍ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር «ዩ ሪፖርት» የተሰኘ የዲጂታል ስርአት ተጀምሯል። እስካሁንም ከ20 ሺ በላይ ወጣቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። በሌላ በኩል የአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚነት በተለይ ደግሞ በግጭት በተፈናቀሉ አካባቢዎች ላይ እየጨመረ መጥቷል። ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከጤናና ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በተለይም የሕግ አካላትን በማሳተፍ የአደንዛዥ እፅ ግብረ ኃይል እዲቋቋም ተደርጓል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከቤት ውስጥ የእጅ ሥራ እስከ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው ተወልዳ ያደገችው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን አባድር ኢንስቲትዩት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ ፓስተር አካባቢ በሚገኘው አሜሪካን ሚሽን ትምህርት ቤት ተከታትላለች።

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷ ቀጥላም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ካምፓስ /አራት ኪሎ ግቢ/ በስታትስቲክ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በጥሩ ውጤት ማጠናቀቋን ትገልጻለች። የዕለቱ የስኬት ገጽ እንግዳችን ወይዘሮ አዲላ እስማኤል የአዲላስ ማኑፋክቸሪንግ መስራችና ባለቤት ናት።

ሥራ ወዳድ፣ ታታሪና አዲስ ነገር የመፍጠር ውስጣዊ ፍላጎት ያላት አዲላ፤ ከወላጅ እናቷ የተማረችውን የእጅ ሥራ ትጠበብበታለች። ክርን ከኪሮሽ በማዋደድ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ የእጅ ሥራዎችን መስራት ከልጅነት እስከ ዕውቀት አብሯት የኖረ ሙያዋ አርጋዋለች። የእጅ ሥራ ሙያዋን የበለጠ ያዳበረችው ደግሞ ወደ ትዳር በገባችበት አጋጣሚ ነው።

ሴት ልጅ በቶሎ ትዳር መያዝ አንዳለባት ጽኑ ዕምነት ባለው ማኅበረሰብ ውስጥ የተገኘችው አዲላ፤ ትምህርቷን ባጠናቀቀች በሳምንቱ የትዳሩን ዓለም መቀላቀሏንም ታስታውሳለች። ‹‹በወቅቱ ገና ልጅ በመሆኔ ወደ ትዳር መግባቱን ብዙ ባልወደውም ወላጅ የሚለውን መቀበል ደግሞ የግድ በመሆኑ አሜን ብዬ ተቀብያለሁ። ያም ቢሆን ታድያ ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው ወላጆቼ የሚጠቅመኝን እንዳደረጉልኝና በትልቁም እንደዋሉልኝ ተረድቻለሁ፤ ስለዚህ ወላጆቼን ሁልጊዜም አመሰግናቸዋለሁ›› ትላለች። ገና በለጋ ዕድሜዋ የጀመረችው ትዳር በልጆች ተባርኮ ዛሬ ላይ እኩዮቿን ማድረስ መቻሏንም ትናገራለች።

በትዳር ዓለም ልጅ ወልዶ በማሳደግ ሂደት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ በቤት ውስጥ ታሳልፍ የነበረችው ወይዘሮ አዲላ፤ የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን በቤት ውስጥ ትሰራ ነበር። ከወላጅ እናቷ የተማረችውን የእጅ ሥራ በተለይም የኪሮሽ ሥራን በመስራት ውጤታማ መሆን ችላለች። የተለያዩ ዲዛይኖችን በማዘጋጀት ውስጣዊ ፍላጎቷና የነብሷ ጥሪ የሆነውን የእጅ ሥራ ልጆቿን ከማሳደግ ጎን ለጎን ደስ እያላት ከውስጥ በመነጨ ፍቅር ስትሰራ ቆይታለች።

ታታሪ፣ ሥራ ወዳድና ብርቱዋ አዲላ፤ በቤት ውስጥ ደስ እያላት እንደቀልድ የምትሰራቸው የእጅ ሥራዎች በብዙዎች ዘንድ ይወደዱላትም እንደነበር ታስታውሳለች። አንድ ሁለት እያለች ቀስ በቀስ የምትሰራቸው የእጅ ስራዎች ልጆች ከማሳደግ ጋር አንድ ላይ ተደምረው የሙሉ ጊዜ ሰራተኛ ቢያርደርጓትም ደስተኛ ነበረች። የእጅ ሥራዎቿ ከልጆቿ እኩል እየተወለዱና እያደጉ ቤቷን መሙላት ጀመሩ። ይህን ጊዜ ወይዘሮ አዲላ፤ ከልጆቿ እኩል እያሳደገች ያመጣችውን የእጅ ሥራ ወደ ገበያ ማውጣት እንዳለበት በማመን እንቅስቃሴ ጀመረች።

የእጅ ሥራዎቿ ገበያ ላይ ይወጣሉ ብላ ሳታስብ ውስጣዊ ፍላጎቷን በማዳመጥ የፈጠራ ችሎታዋን በሥራ ያሳየችው አዲላ፤ ከዓመታት በኋላ ቤት ውስጥ የተከማቹትን የእጅ ስራዎች ወደ ገበያ ይዛ ወጥታለች። በወቅቱ ገበያ ላይ ስታቀርበው በዙሪያዋ የነበሩ ሰዎች ከሚያደንቁት በብዙ እጥፍ ብዙዎች የእጅ ሥራዎቿን አድንቀው ሲደነቁ አስተውላለች። ክርና ኪሮሽን አስማምታ ከሰራቻቸው የእጅ ሥራዎች መካከልም የልጆችና የአዋቂ ቦርሳ፣ ሹራብ፣ ቀሚስ፣ የአንገት ልብስ፣ ካልሲ፣ ኮፍያ ይገኙበታል። ከአልባሳቱ በተጨማሪም የእጅና የእግር ብራስሌቶችን በክርና በጨሌ ትሰራለች።

እነዚህን ምርቶች ማኅበረሰቡ ዘንድ ለማድረስና ስራውን ወደ ቢዝነስ መቀየርን ስታስብ መሸጫ ሱቅ መከራየት የግድ ነውና መኖሪያ ቤቷ ውስጥ ያመረተችውን በክራይ ሱቅ ለገበያ በማቅረብ ብዙዎች ዘንድ መድረስ ችላለች። በወቅቱ ብዙዎች ሥራዋን ወደው ሲገዙላት የበለጠ ትበረታታለች።

በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ኋላ የሚጎትቷት በርካታ ደንቃራዎች ይገጥሟት እንደነበር የምታስታውሰው አዲላ፤ እሷ ግን ከሚያበረታቷት ጋር በርትታ ሥራዋን በጥራት መስራቷን ቀጥላለች። በወቅቱ ስምንት ለሚደርሱ ሠራተኞች የሥራ ዕድል ፈጥራለች።

የእጅ ሥራ በባህሪው በፍጥነትና በብዛት የሚሰራ ባለመሆኑ ፍላጎት ያላቸውንና ቤት ውስጥ የቀሩ ስምንት አካል ጉዳተኞችን በማሰልጠን ወደ ሥራ አስገብታለች።

‹‹አካል ጉዳተኞቹ በቤታቸው ሆነው በሰለጠኑት መሰረት ይሰሩ ነበር›› የምትለው አዲላ፤ የሚያስፈልጓቸውን ክርና ሌሎች ግብዓቶችን በማቅረብ ታሰራቸው እንደነበር አጫውታናለች። በወቅቱ ከሰራተኞቿ ጋር በመሆን የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን ሰርታ ወደ ገበያ መውጣት ጀምራለች።

ይህን ጊዜ ታድያ ሥራዋን ማሻሻልና ማስፋፋት የሚያስችላት አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ። እሷ እንዳለቸው በወቅቱ ደጃፏን ያንኳኳው አጋጣሚ የጀርመን ፕሮጀክት ነበር። ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያውያን ዲዛይነሮችን በተለያየ ዘርፍ አወዳድሮ ማሰልጠን ነው። የሰራቻቸውን የእጅ ሥራዎች የተመለከተው የውጭ ዜጋም በእጅ ሥራዎቹ በጣም ተደንቆ የሚፈልገውን አይነት ሥራ እንድትሰራ ትዕዛዝ ይሰጣታል። ትዕዛዙ የተለያዩ ቀሚሶችን በእጅ መስራት ሲሆን እሷም ቀሚሶቹን በተባለው ጊዜና ጥራት አደረሰች። የውጭ ዜጋውም አዲላን ጨምሮ ሌሎች ዲዛይነሮችን ከምርቶቻቸው ጋር ይዞ ወደ ጀርመን አገር በመጓዝ በጀርመን በተለያዩ ዘርፎች የፋሽን ትርዒቱ ማሳየት ችለዋል።

‹‹ይህ ለእኔ ትልቅ አጋጣሚ ነበር›› የምትለው አዲላ፤ በወቅቱ የውጭው ዓለም ለእጅ ሥራ የሚሰጠውን ትልቅ ቦታ መረዳት እንዳስቻላት ተናግራለች። በመሆኑም ሥራውን የበለጠ አጠናክራ ለመቀጠል ትልቅ ሞራል ሰንቃ ተመልሳለች።

በተለያዩ ምክንያቶች ከፕሮጀክቱ ጋር መቀጠል ባትችልም በቤት ውስጥ አምርታ በክራይ ሱቅ የምትሸጣቸውን የእጅ ሥራዎች በተለያዩ ባዛርና ኤግዚቢሽኖች ይዛ በመቅረብ ሥራዋን አስፋፋች። በዚህ ጊዜ በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅታ የማምረቻ ቦታ ማግኘት ችላለች።

በወቅቱ ስምንት አካል ጉዳተኞችን ይዛ ስትሰራ የነበረችው አዲላ፤ ከወረዳው ባገኘችው የመስሪያ ቦታ ሥራዋን ለማስፋፋት በር ከፍቶላታል። በመሆኑም ሁለት የስፌት ማሽኖችን በማስገባት ከእጅ ሥራው ጎን ለጎን ቦርሳዎችን በማምረት ለገበያ አቅርባለች። በተለይም ዕቃ መያዣ ቦርሳዎችን ለሱፐርማርኬቶች ታቀርብ እንደነበር ታስታውሳለች።

ሥራው ራሱን እየመራ ሲሰፋ የትራስና የመጅሊስ አልባሳትን ጭምር በማምረት ይበልጥ ስራዎቿን ማውጣት ቻለች። በዚህ ጊዜ ከተማ አስተዳደሩ የተማሪዎች ዩኒፎርም ለማዘጋጀት ባወጣው ጨረታ ተወዳድራ የመጀመሪያውን የተማሪ ዩኒፎርም በጊዜና በጥራት አምርታ አቅርባለች።

የዩኒፎርም ሥራ ትልቅ መነቃቃትን የፈጠረላት አዲላ፤ ከእጅ ሥራ ይልቅ ወደ ዩኒፎርም ሥራ በማድላት ሙሉ ለሙሉ ዩኒፎርም ወደማምረት ገብታለች። የተለያዩ አይነቶች ዩኒፎርሞች እንዳሉም ጠቅሳ፣ ባደረገችው የገበያ ጥናት ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ዩኒፎርሞች እጥረት መኖሩን ትረዳለች። ያለው ፍላጎትና አቅርቦት ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ለሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ ዩኒፎርሞችን ለማምረት አቅዳ ወደ ሥራው ገብታለች።

ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ዩኒፎርሞችን በጥንቃቄና በጥራት ማምረትና መጠቀም የግድ ነው የምትለው አዲላ፤ አልባሳቱን በከፍተኛ ጥራት በጥንቃቄ እንደምታመርት አጫውታናለች። እሷ እንዳለችው፤ ለኦፕራሲዮን ክፍል ብቻ የሚያስፈልጉ አልባሳት አሉ። እነሱን በማጥናት የተለያዩ ፓኬጆች ይዘጋጃሉ። አንድ ባለሙያ የሚለብሰው ዩኒፎርም ከሌላኛው ባለሙያ ይለያል። እያንዳንዱ የሕክምና ባለሙያ የሚለብሰው ዩኒፎርም በቀለምና በአይነት የተለያየ በመሆኑ ታካሚው ሀኪሙን በዩኒፎርሙ ቀለም ለይቶ ያውቀዋል። ስለዚህ ታካሚው በተለምዶ ነጭ ገዋን የለበሰውን ሁሉ ዶክተር ብሎ አይጠራም። አዲላም ይህን በጥናት በመለየት በጥንቃቄና በጥራት እያመረተች ለሆስፒታሎች ታቀርባለች።

በቤት ውስጥ በክርና በኪሮሽ የተጀመረው የእጅ ሥራ ዛሬ የሕክምና ባለሙያዎች የሚለብሷቸውን የተለያዩ አይነት ዩኒፎርሞችን እያመረተ የሚገኘው አዲላስ ማኑፋክቸሪንግ፤ የታካሚዎችን ዩኒፎርም ጭምር እያመረተ ይገኛል።

‹‹ጤና ሲባል ሁልጊዜ ከጽዳት ጋር የተያያዘ ነው›› የምትለው ወይዘሮ አዲላ፤ ሥራው ሰፋ ያለ ቦታና ጥንቃቄን እንደሚፈልግም ትናገረለች። ድርጅቷ አሁን ላይ ወደ መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ የተሸጋገረ ቢሆንም፣ ስራውን 126 ካሬ ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ ነው የሚያመርተው። በቀጣይም ሥራውን የማስፋ ዕቅድ



እንዳላት ጠቅሳለች።

በቤት ውስጥ በእጅ ሥራ ስትጀምር ለስምንት ሴቶች የሥራ ዕድል የፈጠረችው ወይዘሮ አዲላ፤ በአሁኑ ወቅት 30 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥራለች። በቀጣይም የሥራ ዕድል ለማስፋት ዕቅድ ያላት ሲሆን፤ ለዚህም ሥራውን የበለጠ ማስፋፋትና በጥንቃቄና በጥራት መሥራት የግድ ነው ትላለች። በአሁኑ ወቅትም የማስፋፊያ ጥያቄ አቅርባ ምላሹን በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች። ከመንግሥትም አጥጋቢ ምላሽ እያገኘች እንደሆነ ነው የተናገረችው።

ከዚህ ቀደም የሆስፒታል ባለቤቶች ሆስፒታል ሲገነቡ የሕክምና አልባሳቱን ጨምሮ ቁሳቁሱን ከውጭ ያስገቡ እንደነበር ያነሳችው ወይዘሮ አዲላ፤ አሁን ግን በአገር ውስጥ እየተመረቱ ያሉ የሕክምና ባለሙያዎች አልባሳት በመኖራቸው እረፍት ሰጥቷቸዋል ትላለች። በመሆኑም አሁን ላይ አብዛኞቹ የሕክምና ተቋማት ሆስፒታሎችን ጨምሮ በአገር ውስጥ የተመረቱትን የሕክምና ባለሙያዎች አልባሳት እየተጠቀሙ ይገኛሉ። አልባሳቱ አላቂ እንደመሆናቸው ገበያ ውስጥ በስፋት እንደሚፈለጉም አመላክታለች።

የሰውን ሕይወት እያዳኑ ያሉ የሕክምና ባለሙያዎች ፍጹም ምቹ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሆነው መሥራት እንዳለባቸው አምናለሁ የምትለው ወይዘሮ አዲላ፤ ለዚህም ‹‹እኔ በሙያዬ ምቾት የሚሰጥ ዩኒፎርም እንዲለብሱ ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ›› ትላለች። እሷ እንዳለችው፤ ምቾት የሚሰጥ ዩኒፎርም ለማምረት የጨርቁ አይነት ይወስነዋል። ፖሊስተር የሚባለው ጨርቅ የሚያቃጥል ባህሪ አለው። ይህም ምቾት አይሰጥም። ስለዚህ ኮተን የሆኑ ጨርቆች ተመራጭ ናቸው። አዲላስ ማኑፋክቸሪንግ ይህንኑ ከግምት በማስገባት ኮተን እና ፖሊስተር በመቀላቀል አልባሳቱን ያመርታል።

አንድ ክር በሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም፤ አራት ክር በአስር ብር ገዝታ በቤት ውስጥ ጀመረችው የእጅ ሥራ በአሁኑ ወቅት አምራች ኢንዱስትሪውን በመቀላቀል ገበያ ውስጥ በስፋት መግባት ችሏል። የድርጅቱ የገበያ መዳረሻዎች በአብዛኛው ሆስፒታሎች ሲሆኑ፤ እሷም እነሱን ለማግኘት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ገበያ የማፈላለግና የማስተዋቅ ሥራ ሰርታለች። በመሆኑም ድርጅቱን ፈልገው የሚመጡ በርካታ ደንበኞችን በማፍራት የተለያዩ ሆስፒታሎች ጋር መድረስ ችላለች።

የማምረት አቅሙን በሚመለከትም እንዳብራራችው፤ አዲላስ ማኑፋክቸሪንግ ባሉት 30 የመስፊያ ማሽኖች በቀን 150 ሙሉ ልብስ እያመረተ ይገኛል። ይሁንና ድርጅቱ ከዚህ በበለጠ ለማምረት የማምረቻ ቦታ ውስንነት አለበት። በቀጣይ በሚያደርገው ማስፋፊያ ሥራውን የበለጠ በማስፋት በቀን የማምረት አቅሙን ከ150 ወደ 1000 ከፍ የማድረግ እንዲሁም የሥራ ዕድል የመጨመር ዕቅድ አለው። ምርቶቿንም ከአዲስ አበባ ውጭ በአገሪቱ በሚገኙ ክልሎች እንዲሁም በአፍሪካ አገራት ጭምር የመድረስ ትልቅ ዕቅድ እንዳላት ወይዘሮ አዲላ ተናግራለች።

በአስር ብር መነሻ ካፒታል በቤት ውስጥ የተጀመረው እጅ ሥራ አሁን ላይ ከፍ ያለ ካፒታል ማስመዝገብ እንደቻለና ወደፊትም እያደገ እንደሚሄድ የገለጸችው አዲላ፤ በአሁኑ ወቅት አዲላስ ማኑፋክቸሪንግን እየመራች ያለችው እኩያ ከሆኑ ልጆቿ ጋር በጋራ እንደሆነና ልጆቿ በብዙ እያገዟት መሆኑን አጫውታናለች።

ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ የተለያዩ ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች ድጋፍ እያደረገች እንደሆነ የጠቀሰችው አዲላ፤ በተለይም ወላጅ አልባ ልጆችን ከሚረዱ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር እንደምትሰራ ተናግራለች። ለልጆቹ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን በየጊዜው ታደርጋለች። ወላጅ አልባ ሕጻናት መታየትና መደገፍ እንዳለባቸውም ታምናለች። በዚህ ተግባሯም የተለያዩ የምስጋናና የምስክር ወረቀቶችን ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅት አግኝታለች። በአካባቢዋም እንዲሁ አቅመ ደካሞችን በመርዳት ማኅበራዊ ኃላፊነቷን እየተወጣች መሆኗን አስታውቃለች።

‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የሚሰሩ የሥራ ዘርፎች እና መስራት የሚችሉ እጆች አሉ›› የምትለው አዲላ፤ ይህንን አስማምቶ መጠቀም የሚቻልበት ጊዜ አሁን መሆኑን አስታውቃለች፤ በተለይም መንግሥት አምራች ኢንዱስትሪውን እየደገፈ ያለበት መንገድ አበረታች እንደሆነም አመልክታ፣ ይኸው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግራለች። መስራት የሚችሉ እጆች ሰርተው መለወጥ እንዲችሉ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ እየተሰራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥል ብላለች።

# ተናጋሪው ዶሴ

# በሀሰተኛ ሰነድ ለመክበር የተደረገ ጥረትና መዘዙ

አስመረት ብስራት

ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል የሀገርን ኢኮኖሚ እንዲሁም የዜጎችን መብትና ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ የወንጀል ተግባር ነው። ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀቱ በመንግስታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሰነዶች ላይ የሚፈፀም ከሆነ በሙስና ወንጀል የሚያስጠይቅ ነው።

መንግስታዊ ሰነድ ሲባል ከሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ከክልል ቢሮዎችና በየደረጃው ካሉ አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የወጡ በማስመሰል የሚዘጋጅ ሲሆን ለምሳሌ የንግድ ወይም ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወረቀቶች፣ የይለፍ ወረቀቶች፣ የብቃት ማረጋገጫዎች፣ የስራ ፈቃድ ወረቀቶች፣ የስራ ልምድ፣ የክፍያ ማዘዣዎች፣ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ወይም ሊብሬዎች፣ ወዘተ የሚያካትት ነው።

የሕዝባዊ ድርጅቶች ሰነድ ደግሞ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም ተቋማት ሰነዶች ለምሳሌ የመጋዘን ደረሰኝ፣ የእቃ ማውጫ ፈቃድ፣ የትምህርት ማስረጃ፣ የባንክ ክፍያ ሰነዶች እና መሰል በእነዚህ ተቋሟት የሚሰጡ ሰነዶችን የሚመለከት ነው።

ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት፣ መገልገል እና የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነት እነዚህን ይመስላሉ። ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውም መብት ወይም ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውም ሰነድ የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ፤ በመንግስት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት መዝገብ፣ ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛውን ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሀሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ስልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሀሰተኛ ሰነድ የፈጠረ እንደሆነ፤ አንድን የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነድ በተለይ የፈራሚውን ስም ወይም ፊርማ ወይም የሰነዱን ይዘት፣ አሃዝ፣ ፍሬ ነገር ወይም ዝርዝር መግለጫ በሙሉ ወይም በከፊል በመለወጥ፣ በማሻሻል፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም በማጥፋት ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ ወይም ማናቸውንም ሀሰተኛ ፍሬ ነገር ያስገባ ወይም እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 23 መሰረት ከሶስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ያስቀጣል።

በተጨማሪም የዚህ ወንጀል አፈፃፀም በሚከተለው ሁኔታ ሊከብድ የሚችል ሲሆን ይኸውም ሰነዶቹን እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ እንዲጠብቅ ወይም ከነዚሁ ውስጥ ቅጂዎችን እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ እንደሆነ ወይም ሰነዱን በመገልገል የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ወይም በሕዝብ ጥቅም ላይ ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ አምስት ዓመት የሚደርስ እስራት ያስቀጣል።

ሌላው መገንዘብ የሚገባን ጉዳይ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 23 (4) መሰረት በወንጀል የሚያስጠይቀው ሀሰተኛ ሰነዶችን ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ይዞ መገኘትና መገልገል ጭምር ሲሆን በዚህም መሰረት ወደ ሀሰት የተለወጠ ወይም በሀሰት የተዘጋጀ ሰነድ በቤቱ፣ በተሽከርካሪው፣ በኪሱ ወይም በማንኛውም አግባብ በቁጥጥሩ ስር የተገኘ እንደሆነ ከላይ በተጠቀሰው ቅጣት ጋር ተመሳሳይ በሆነ ይቀጣል። በተጨማሪም ማንኛውም ሰው ወደ ሀሰት በተለወጠ ወይም በሀሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በተመሳሳይ ይቀጣል።

ከጉምሩክ መንግስታዊ ስራዎች ጋር በተያያዘ ማንኛውም ሰው በጉምሩክ ኮሚሽን ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ኮሚሽኑ የሚጠቀምበትን ቅፅ፣ ማህተም፣ መታወቂያ፣ ዓርማ፣ የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ማናቸውም ሰነድ ወይም ምልክት ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሰራ ወይም ይህንኑ ያከፋፈለ፣ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ ወይም ለጉምሩክ ስነ ስርዓት የሚቀርቡ ሰነዶችን የሰረዘ፣ የደለዘ፣ የፋቀ ወይም አስመስሎ የሰራ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 167 እና በጉምሩክ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ 1160/2011 አንቀፅ 169(4) መሰረት ከአምስት እስከ አስር ዓመት እስራት ይቀጣል።

ከላይ የተመለከትነውን የሕግ ድንጋጌ ልናነሳ የወደድነው ሀሰተኛ መንግስታዊ ሰነዶችን በመገልገል ከ 1 ሚሊዮን 697 ሺ ብር በላይ ጉዳት ያደረሱ ተከሳሾች ታሪክ ልናካፍላችሁ ስለወድድን ነው።

ተከሳሾቹ የሱፍ ሰይድ መሀመድና ካሊድ ተስፋዬ ዓለሙ ይባላሉ። ባለፉበት ገንዘብ የመክበር ሕልም ያነገቡት እነዚህ ተከሳሾች አይደረስብንም በማለት ሀሰተኛ መንግስታዊ ሰነዶችን በማዘጋጀት ከሕዝብ ሀብትና ንብረት ላይ የማይገባቸውን ጥቅም ሲያጋብሱ መቆየታቸው ይደረስበታል። እነዚህ አጭበርባሪዎች እኩይ ተግባራቸው ስር ሳይሰድ ለማስቆም ፖሊስ ስራውን ጀምሯል።

### አጭበርባሪዎቹ

የሱፍ ሰይድ መሀመድና ካሊድ ተስፋዬ ዓለሙ ይባላሉ። አጭበርብሮ መብላትን የእለት ከእለት ተግባራቸው ያደረጉት እነዚህ ሰዎች በጥቂት በጥቂቱ የለመዱትን የማጭበርበር ተግባር ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ በሙሉ አቅማቸው የገቡበት የቀደመ ስርቆታቸው ሳይታወቅባቸው በመቆየቱ የተነሳ ነው።

ታዲያ በቀላል በቀላሉ የለመዱትን ሌብነት ከፍ በማደረግ ሀብታም ለመሆን ተግተው መስራት ጀመሩ። ይህን ስራ ሰርተው ለመክበር ደግሞ ትክክለኛው አማራጭ ያለ ቀረጥ መኪና ማስገባት እንደሆነ ተስማሙበት። ታክስ ያልተከፈለባቸው መኪኖች ወደሀገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉበትን አካሄድ በተገቢው በማጥናት ወደስራው ገቡ።

አንደኛው መኪናውን ከውጭ ለማስገባት ሲጣጣር ሌላኛው ደግሞ ሀሰተኛ ሰነዶችን የማዘጋጀት ስራ ላይ ተጠመዱ። መኪኖቹ ለቱሪስት አገልግሎት በሚል ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ቀረጥ የተከፈለባቸው በማስመሰል ወደ ግል ንብረትነት ያዘዋውሯቸዋል።

በዚህ ስራቸው ለተወሰነ ጊዜ ሳይያዙ መቆየታቸው ጉልበት ፈጠረላቸው። ሳይነቃባቸው መቆየቱ የልብ ልብ የሰጣቸው እነዚህ ሰዎች በተደጋጋሚ ይህን የሰነድ ማጭበርበር ስራ ጠንክረው ተያያዙት። መያዝ አይቀርምና በለመደ አገራቸው የለመዱትን ስራ ለመስራት በሚጣደፉበት ወቅት የሕግ አካላት እጅ ይወድቃሉ።

ፖሊሶች የመረጃውን ሀሰተኝነት ካረጋገጡ በኋላ የያዟቸውን ሰነዶች በሙሉ በማጠናቀር ለዐቃቤ ሕግ አቀረቡ።

### የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ

በዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ ላይ 1ኛ የሱፍ ሰይድ መሀመድ፣ 2ኛ ካሊድ ተስፋዬ ዓለሙ የተባሉ ሁለት ተከሳሾች በተለያዩ 2 ክሶች ተከሰዋል።

1ኛ ክስ በአንደኛ ተከሳሽ ላይ ሲሆን ተከሳሽ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሞዴሉ 2012 ቶዮታ ራቫ ፎር የሆነ ተሽከርካሪ በአንድ ግለሰብ ስም ለቱሪስት አገልግሎት በጊዜያዊነት ተመዝግቦ ምንም አይነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ከሳዑዲ አረቢያ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ እያለ መደበኛ የጉሙሩክ ስነስርዓት ተፈጽሞበት ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት እና በግዢ የተላለፈለት በማስመሰል የተሽከርካሪ ምዝገባ በማካሄድና በተሽከርካሪው ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ እና ሰሌዳ ለማውጣት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን አቅርቦ በመገልገል በቀን 04/05/2011 በቁጥር 006516 የተዘጋጀ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ እና ሰሌዳ በመውሰድ ተሽከርካሪው በህጋዊ መንገድ የጉሙሩክ ስርአት ተፈጽሞበት ቢሆን ለመንግስት ሊከፍል የሚገባውን 1,697,113 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ አንድ መቶ አስራ ሶስት) ብር በማሳጣት ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ በፈጸመው ሀሰተኛ መንግስታዊ ሰነዶችን የመገልገል ከባድ ሙስና ወንጀል ተከሷል።

በተመሳሳይ በ2ኛ ክስ በሁለቱም ተከሳሾች ላይ ሲሆን ተከሳሾች ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቁ ከላይ በ1ኛ ክስ በተጠቀሰው ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ለቱሪስት አገልግሎት በጊዜያዊነት ከሳዑዲ አረቢያ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የገባውን ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት በማስመሰል ሀሰተኛ የጉምሩክ ሰነዶች እና ሀሰተኛ መንግስታዊ ሰነዶችን በመገልገል የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ በ1ኛ ተከሳሽ ስም ከወጣበት በኋላ በወንጀል ምክንያት የተገኘውን ንብረት ምንጩ እንዲደበቅና ሕጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ በማሰብ፣ 2ኛ ተከሳሽ ተሽከርካሪው የተገኘው በወንጀል ምክንያት መሆኑን እያወቀ ይህን በመደበቅ ተሽከርካሪው የራሱ እንደሆነ ሊብሬውም ወንድሙ በሆነው 1ኛ ተከሳሽ ስም እንደተመዘገበ ለ1ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ገልጾ በማግባባት የዋጋ ድርድር ሲያደርግ ቆይቶ 1 ሚሊዮን 697 ሺ 113 ብር ለመሸጥ በመስማማት ከዚህ ገንዘብ ላይ 200 ሺ ብር በቅድመ ክፍያነት የተቀበለ እንዲሁም ሽያጭ ከተከናወነ በኋላም ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ላይ 1 ሚሊዮን 20 ሺ ብር 1ኛ ተከሳሽ በባንክ ሒሳብ ቁጥር ያስተላልፍለታል።

1ኛ ተከሳሽም ንብረቱን ያገኘው በወንጀል ምክንያት ሆኖ እያለ ይህን በመደበቅ ድርድሩን በ2ኛ ተከሳሽ አማካኝነት ሲያከናውን ከቆየ በኋላ የንብረቱ ሕጋዊ ባለቤት መስሎ በመቅረብ ከላይ በ1ኛ ክስ የተጠቀሰውን ተሽከርካሪ በቀን 22/05/2011 ዓ.ም በቁጥር ቅ4/0002093/2A/2014 ዓ.ም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ቅ/ጽ/ቤት በተመዘገበ የመኪና ሽያጭ ውል ስምምነት ለ1ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር 1,287,85 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት ሺ ሰማኒያ አምስት) ብር በሽያጭ ያስተላለፈ እና ከሽያጩ ያገኘውን ገንዘብ ይበልጥ ምንጩን ለመደበቅና ከተደራሽነት ለማራቅ በማሰብ ለ2ኛ ተከሳሽ ያስተላለፈ ሲሆን፣ ተከሳሾች በተፈጸመው ወንጀል ምክንያት የተገኘውን ንብረት ምንጩ እንዲደበቅና እንዳይታወቅ ለማድረግ ለ3ኛ ሰው አስተላልፈው የሸጡ በመሆኑ በፈጸሙት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በወንጀል ድርጊት የተገኘውን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ተከሰው በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦባቸው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ ወንጀል ችሎት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል።



### ውሳኔ

በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦባቸው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ ወንጀል ችሎት ክርክር ሲደረግ የቆየው ጉዳይ ወደ እልባት ደረሰ።

በክርክሩ ሂደትም ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾች ላይ ማስረጃ አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ተከሳሾችም በዐቃቤ ሕግ የቀረበባቸውን ክስ መከላከል ባለመቻላቸው ምክንያት ፍርድ ቤቱ በተከሳሾች ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት የቅጣት ውሳኔ ያሳለፈ ሲሆን በዚህም በ1ኛ ተከሳሽ በ13 ዓመት ጽኑ እስራትና በ7 ሺ. ብር የገንዘብ መቀጮ፣ በ2ኛ ተከሳሽ ደግሞ በ8 ዓመት ጽኑ እስራትና በ8 ሺ. ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል።

## ማረፊያ/ ትዝብት

# የኛ አቆጣጠር ይረሳ ይሆን?

**ዋለልኝ አየለ**

እነሆ አሮጌ ዓመትን ጨርሰን አዲስ ዓመት ተቀበልን። አዲስ ዓመት ሲገባ (ስንቀበል) ደግሞ የለመድነውን የዓመተ ምህረት አጻጻፍ ትተን ሌላ አዲስ ቁጥር እንጽፋለን። በእርግጥ ልዩነቱ ያን ያህልም ነው። ከአራት ዲጂት ውስጥ አንዲት ዲጂት ናት የምትቀየረው። ይሄ አጻጻፍ ለአሥር ዓመታት ያህል ይቀጥላል። ለምሳሌ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ሁለተኛ ላይ ያለችዋ (የአሥር ቤት ማለት ነው) 9 ቁጥር ለ10 ዓመታት ያህል ትቀጥላለች፤ 1991፣ 1992፣ 1993 ... እያልን ማለት ነው። ከ2001 እስከ 2009 ድረስ ደግሞ 0 ቀጥላለች። እነሆ ከ2010 ጀምሮ ደግሞ ሁለተኛ ላይ ያለችዋ 1 ቁጥር እስከ 2020 ዓ.ም ድረስ ትቀጥላለች። ሦስተኛና አራተኛ ላይ ያሉት (ከቀኝ ወደ ግራ ነው የምንሄደው) ለመቀየር መቶ እና ሺህ ዓመታት ይቆያሉ። የመቶ ቤት የሆነችዋን ‹‹0›› ለመቀየር 83 ዓመታት ይቀሩናል። የአንድ ሺህ ቤት የሆነችውን ‹‹2›› ለመቀየር 983 ዓመታት ይቀራሉ።

አሁን ያለነው ትውልድ የመቶ ቤት የሆነችው ‹‹0›› አብራን ትቆያለች፤ ዕድሜና ጤና ይስጠንና 2100 ዓ.ም ለማየት ያብቃን እያልን ከቁጥር ጨዋታ እንውጣና ወደ ዋናው ትዝብት እንግባ።

እንግዲህ አዲስ ዓመተ ምህረት ሲገባ የመጨረሻዋን ዲጂት መቀየር የተለመደ ነው። እዚህ ላይ ታዲያ አንድ በተደጋጋሚ የሚስተዋል ስህተት አለ። ዓመቱን ሙሉ ስንጽፈው በቆየነው ቁጥር ከመላመድ የተነሳ መርሳት ያጋጥማል። የለመደ እጅ የተቀየረችዋን ቁጥር በመርሳት ያለፈውን ይጽፋል። አሁን አሁን የስብሰባ ማስታወሻዎች ሁሉ ሳይቀር የሚጻፉት በኮምፒተር ስለሆነ እንጂ የእጅ ጽሑፍ በነበረ ጊዜ ደጋግሞ ያጋጥማል። ስህተቱ በኮምፒተር አያጋጥምም ማለት ሳይሆን ቶሎ ለማጥፋት ቀላል ስለሆነ ችግሩን ያቀለዋል። የእጅ ጽሑፍ ሲሆን ግን ስርዝ ድልዝ ይበዛዋል። ለምሳሌ፤ ዓመቱን ሙሉ 2016 እያለ ሲጽፍ የቆየ እጅ 2017 በማለት ፋንታ 2016 ብሎ ሊጽፍ ይችላል።

እነሆ አዲስ ዓመት ተቀበልን። ‹‹2017 ዓ.ም›› ብለን አዲስ ቁጥር ጻፍን። እዚህ ላይ ታዲያ አንድ የምንታዘበው ነገር አለ። ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን የራሳችን የዘመን አቆጣጠር ያለን...›› እያልን እንፎክራለን። የዘመን አቆጣጠራችንን የኮራንበትን ያህል ግን አንጠቀምበትም፤ የውጭው ናፋቂ ነን። በቀላሉ የጓደኞቻችሁን (የራሳችሁንም ቢሆን) ስልክ ተመልከቱ! ሰዓቱ የሚሞላው በፈረንጅኛው አቆጣጠር ነው። ቀኑ እና ዓመተ ምህረቱ የሚሞላው በፈረንጅኛው አቆጣጠር ነው። ስልኩ የኢትዮጵያን አቆጣጠር አይሰራም ይሆን?

በተለይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት ውስጥ በሚሰሩ ጓደኞቼ ደግሞ ከዚህም በላይ የታዘብኩት ነገር አለ። የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ጭራሹንም ይጠፋባቸዋል። ‹‹ዛሬ ቀን ስንት ነው?›› ተብለው ቢጠየቁ ‹‹መስከረም 4›› ከማለት ይልቅ ‹‹ሴፕቴምበር 14›› የሚለው ቶሎ ትዝ ይላቸዋል። ምክንያቱም የሥራ እንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ከፈረንጅኛው አቆጣጠር ጋር ነው የሚቀራረቡት። ደብዳቤዎችና ሌሎች የሥራ ሰነዶች የሚጻፉት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነው። የወር ደመወዛቸውን የሚቀበሉት በውጭው አቆጣጠር ነው። በእነዚህ ተፅዕኖዎች ምክንያት ከኢትዮጵያው አቆጣጠር ይልቅ ለውጭው ይቀርባሉ።

የመንግስት ተቋማት ሆነውም የውጭው አቆጣጠር ተፅዕኖ ያለባቸው አሉ። እንዲያውም ከመገናኛ ብዙኃን በስተቀር አብዛኞቹ በውጭው አቆጣጠር የሚጠቀሙ ናቸው። ለምሳሌ ባንኮች ደረሰኝ ላይ ቀን የሚጽፉት በውጭው አቆጣጠር ነው። ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቀንና ዓመተ ምህረት የሚጻፈው በውጭው አቆጣጠር ነው። በተለይም ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚለጠፉ ማስታወቂያዎች ሁሉ በውጭው አቆጣጠር ነው። በእርግጥ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የማስተማሪያ ቋንቋውም እንግሊዘኛ ስለሆነ ከተፅዕኖው ነፃ መሆን አይቻልም፤ ቢሆንም ግን ቢያንስ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚወጡና በአገር ውስጥ ቋንቋ በሚጻፉ ማስታወቂያዎች የኢትዮጵያን መጠቀም ይቻል ነበር።

ይሄ የዘመን አቆጣጠርን እያደበላለቁ መጠቀም ለመረጃ ስህተትም ይዳርጋል። አንድ በተደጋጋሚ የሚስተዋል ስህተት ላስታውሳችሁ። እንደሚታወቀው በእንግሊዘኛ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኝ ዓመተ ምህረት በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ነው። በእንግሊዘኛ ስንጽፍም ይህንኑ ዓመተ ምህረት ነው መጠቀም ያለብን። ምናልባት የኢትዮጵያን ዓመተ ምህረት መጥቀሱ አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ E.C የሚለው የተለመደ አገላለጽ አለ። ልብ ብላችሁ ከሆነ ግን ይሄን ሳይጠቀሙ በኢትዮጵያ ዓመተ ምህረት በእንግሊዘኛ የሚጽፉ አሉ። ይሄ ነገር ለስህተት ይዳርጋል። ምክንያቱም ጽሑፉ የእንግሊዘኛ ከሆነ ሰዎች የሚረዱት በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ነው፤ አማርኛ ከሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው።

ለምሳሌ ዓመተ ምህረቱ ያለፈ ከሆነ የሰባት ወይም የስምንት ዓመት ልዩነት ተሳስተናል ማለት ነው። ምናልባት ዓመተ ምህረቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ገና ወደፊት ከሆነ ግን ከጽሑፉ ዓውድ ልንረዳው እንችላለን። ለምሳሌ ‹‹በ2018 በተደረገው...›› የሚል የሆነ ሁነት ብናነብ የኢትዮጵያ 2018 ገና ወደፊት ስለሆነ በአውሮፓውያኑ ነው ማለት ነው። ‹‹በ2008 በተደረገው... ›› ቢል ግን የአውሮፓውያኑም የኢትዮጵያም 2008 ስላለፈ አንጠረጥርም፤ ምናልባትም ጉዳዩ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቅ ሆኖ ከነ ዓመተ ምህረቱ ካላስታወስነው በስተቀር!

እንደዚሁም በአማርኛ ጽሑፍ ውስጥ አቆጣጠሩ የውጭ ከሆነ እ.ኤ.አ ብሎ መግለጽ የተለመደ ነው። አንዳንድ ጊዜ ግን ይህን ሳይጠቀሙ በውጭው አቆጣጠር ይጽፋሉ። ይሄም ከላይ የገለጽኩትን አይነት ስህተት ያስከትላል። አንድ እንደ ምልክት የሚያገለግል ነገር ደግሞ አለ። ‹‹ዓ.ም›› የሚል ካለው አቆጣጠሩ በኢትዮጵያ ነው፤ ከሌለው በአውሮፓውያኑ ነው የሚባል ነገር አለ። ይሄ አከራካሪ ስለሆነ አስተማማኝ አይሆንም! የውጭውም ‹‹ዓ.ም›› ይባላል የሚሉ አሉ። ምክንያቱም በእንግሊዘኛ B.C እና A.D የሚባል ነገር ስላለ A.D ‹‹ዓ.ም›› እንደማለት ነው ብለው የሚከራከሩም አሉ፤ ለማንኛውም ይሄኛው ዘዴ የማሳሳት ዕድሉ ሰፊ ነው።

በነገራችን ላይ ጉዳዩ የሀገር ውስጥ ሆኖ የውጭውን አቆጣጠር እንዲንጠቀም የሚያስገድዱን ነገሮች አሉ። ይሄውም በራሳችን መዘናጋት የመጣ ነው። ብዙ ነገሮቻችን በውጭዎች የተጻፉ ናቸው። ስለዚያ ጉዳይ መረጃ ፈልገን ወደ በይነ መረብ (ኢንተርኔት) ስንገባ በእንግሊዘኛ የተጻፈ ታሪክ እናገኛለን። በሀገር ውስጥ ቋንቋ ስንፈልገው ግን ዘረኝነትና የፖለቲካ ብሽሽቅ ነው የሚያመጣልን። ለምሳሌ የአንድ ታዋቂ ሰው ስም አስገብታችሁ ብትፈልጉ፤ ‹‹የእገሌ ስውር ሴራ፣ የእገሌ ገመና ሲጋለጥ...›› የሚሉ አሉቧልታዎችን ነው የሚያመጣልን። በእንግሊዘኛ ስትፈልጉ ደግሞ የሕይወት ታሪኩን፣ የሰራቸውን ሥራዎች፣ የትምህርት ደረጃውን... ይነግረናል። በእነዚህ ምክንያቶች እንግሊዘኛውን ለመጠቀም እንገደዳለን።

እንዲህ የውጭውን አቆጣጠር የመለማመዳችንን ያህል ግን ለምን ወደ አገርኛ መተርጎም አልቻልንም? ቀኑ እና ወሩ ከተጠቀሰ በውጭ አቆጣጠር የተጻፈን ጽሑፍ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ማስቀመጥ በጣም ቀላል ነው። በእያንዳንዱ ወር ውስጥ ያለን የቀን ልዩነት ይታወቃል። ያለን የዓመተ ምህረት ልዩነት ይታወቃል። ለምሳሌ ከመስከረም እስከ ጥር ባሉት ወራት ውስጥ የሰባት ዓመት ልዩነት ነው ያለን። በእንግሊዘኛ ጽሑፍ የተገለጸው ወር ከመስከረም እስከ ጥር ባሉት ከሆነ ከዓመተ ምህረቱ ላይ ሰባት መቀነስ ነው። ከጥር በኋላ የፈረንጆች ዓመት ስለሚታደስ ከጥር እስከ ነሐሴ ባሉት ወራት ደግሞ ልዩነታችን ስምንት ስለሆነ ስምንት መቀነስ ነው። ቀኑም ልክ እንደዚሁ! ለምሳሌ ባለፈው ነሐሴ ወር የነበረው ልዩነት ስድስት ሲሆን አሁን በመስከረም ወር ደግሞ 10 ነው።

ይሄኛው አቆጣጠር ወሰብሰብ ስለሚል ሁሉም ይጠቀመው ማለት አይቻልም፤ ቢያንስ በምርምር ላይ ያሉ ሰዎች ግን እንዴት ይሄ ይጠፋቸዋል? እሺ ይሄም ይቅር! አገራዊ ሁነትን በራስ አቆጣጠር ቢጻፍ ምን ችግር አለው? ምናልባት መሰልጠን እየመሰለን ወይም ስንፍና ነው። ሰው እንዴት የራሱ አኩሪ ታሪክ እያለው የሌላው ይናፍቀዋል? ደግሞ እኮ ባለፉት ዓመታት ‹‹የኩራት ቀን›› እያልን ስናከብር ነበር።

በዚህ መዘናጋታችን የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር የመረሳት ዕጣ ፋንታ እንዳይገጥመው ያስፈራል። በራሳችን እንኩራ!

መልካም አዲስ ዓመት!

## ዓለም አቀፍ

# ምዕራባውያን ዩክሬን የረጅም ርቀት ሚሳይሎችን እንድትጠቀም ከፈቀዱ በቀጥታ ከሩሲያ ጋር እንደሚዋጉ ፑቲን አስጠነቀቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ምዕራባውያን ዩክሬን የረጅም ርቀት ሚሳይሎችን እንድትጠቀም ፈቃድ የሚሰጡ ከሆነ ከሩሲያ ጋር በቀጥታ እንደሚዋጉ ይወቁት ሲሉ የሩሲያው ፕሬዚዳንት ተናገሩ፡፡

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ምዕራባውያን ይህን ውሳኔ የሚወስኑ ከሆነ የጦርነቱ መዳረሻ የት ድረስ ሊሆን እንደሚችል መገመት ከባድ ነው ብለዋል፡፡

አሜሪካ ለዩክሬን የሰጠችው የረጅም ርቀት ሚሳይል በሩሲያ ውስጥ የሚገኙ ኢላማዎች ላይ ጥቃት ለመፈጸም እንዲውሉ ፈቃድ ለመስጠት እያጤነች እንደምትገኝ ከሰሞኑ ማስታወቋ ይታወሳል፡፡



ቭላድሚር ፑቲን

ከአሜሪካ በተጨማሪ ብሪታንያም ይህን የዋሽንግተን ውሳኔ ልትከተል እንደምትችል ተነግሯል፡፡ ይህን ተከትሎ ነው ፑቲን ምዕራባውያን ጦርነቱን ቀጣናዊ ከሚያደርግ ድርጊት እንዲቆጠቡ ያስጠነቀቁት፡፡

በተጨማሪም ሞስኮ ተገቢ ነው ያለችውን እርምጃ ሁሉ እንደምትወስድ ዝተዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ ለኪዬቭ የረዥም ርቀት ሚሳኤሎችን የሚያቀርቡ ሀገራትን በቀጥታ ወደ ጦርነቱ ይጎትታል ነው ያሉት፡፡

ምክንያቱም ዩክሬን የሳተላይት ኢላማ መረጃ እና የሚሳይሎቹ አካሄድ የሚከታተል መሰረተ ልማት ስለሌላት በኔቶ አባል ሀገራት የሚከወን ይሆናል፤ ይህም በቀጥታ መሳተፋቸውን የሚያረገግጥ ነው ብለዋል፡፡

ስለሆነም ጉዳዩ ለዩክሬን የረጅም ርቀት ሚሳይል የመፍቀድ እና ያለመፍቀድ ሳይሆን የኔቶ አባል ሀገራት በቀጥታ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የሚወስን ነው ሲሉ ዝተዋል፡፡

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮልደሚር ዘለንስኪ የሞስኮን የማጥቃት አቅም ይቀንሳሉ ያሏቸውን በሩሲያ ውስጥ የሚገኙ ኢላማዎችን ለማጥቃት ፈቃድ እንዲሰጣቸው ለወራት ሲወተውቱ ቆይተዋል፡፡

ዩክሬን የምዕራባውያን የጦር መሳሪያ ድጋፍ መዘግየትና ረጅም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳይሎችን እንዳትጠቀም የተጣሉባት ማዕቀቦች ለመልሶ ማጥቃቱ አለመሳካት በምክንያትነት ስታቀርብ መቆየቷ ይታወሳል።

የምዕራባውያን ሚሳይሎች በሩሲያ ግዛት ውስጥ ጥቃት ከተፈጸመባቸው የጦርነቱን አድማስ እንደሚያሰፋውና “የኒዩክሌር ጦርነት” ሊጀምር እንደሚችልም ፑቲን ከዚህ ቀደም ገልጸው ነበር።

በአሁኑ ማስጠንቀቂያቸውም ሀገራቸው ጠላቶቿ በዚህ ልክ ሲተባበሩባት ከዳር ቆማ እንደማትመለከት እና ሉአላዊነታቸውን ለማስጠበቅ መውሰድ የሚጠበቅባቸውን እርምጃ ያለማመንታት እንደሚወስዱ ተናግረዋል፡፡

# ስዊድን ሀገሪቷን ለቀው ለሚወጡ ስደተኞች 34 ሺህ ዶላር እከፍላለሁ አለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ስዊድን ሀገሪቷን ለቀው ለሚወጡ ስደተኞች 34 ሺህ ዶላር ልትከፍል ነው።

የሀገሪቷ የኢሚግሬሽን ሚኒስትር ጆን ፎርሲል ከ2026 ጀምሮ ሀገሪቷን ለቀው ለሚወጡ ስደተኞች እስከ 34 ሺህ ዶላር ድረስ ለመክፈል ተዘጋጅተናል፤ ይህ የሆነው አዲስ በተዘጋጀው የስደተኞች ፖሊሲ ለውጥ ነው ብለዋል።

በ2015 ላይ ከተለያዩ የአለም ክፍሎች ለሚመጡ ጥገኝነት ጥያቄዎች ድንበሯን ክፍት አድርጋ የነበረችው ሀገር በዚሁ አመት ከ160 ሺህ በላይ ስደተኞችን ተቀብላለች። አብዛኞቹ ስደተኞች ከመካከለኛው ምሥራቅ እና ሰሜን አፍሪካ መነሻቸውን ያደረጉ ናቸው።

በርካታ ስደተኞችን ከመቀበል ጋር በተያያዘ በሀገሪቱ እየጨመሩ የሚገኙት ከባባድ ወንጀሎች መንግስት እዚህ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ እንዳስገደደው ተነግሯል።

ከ2012 እስከ 2023 በሀገሪቱ የሚፈጸሙ የግድያ ወንጀሎች በእጥፍ ጨምረዋል በተመሳሳይ ወሲባዊ ትንኮሳዎች በ56 በመቶ ሲጨምሩ ወንጀሎቹ 90 በመቶ የሚፈጸሙት በስደተኞች መሆኑን መንግሥት አስታውቋል።

የሀገሪቷ ጠቅላይ ሚኒስትር ኦልፍ ክሪስተርሰን ባለፈው አመት በ12 ሰአታት ልዩነት ውስጥ 3 ሰዎች መገደላቸውን ተከትሎ እየጨመረ የመጣውን የስደተኞች ወንጀል ለመከላከል አዲስ አሰራር እንደሚከተሉ ቃል ገብተው ነበር።

ከዚህ ባለፈም በአደንዛዥ እጽ ሽያጭ፣ በተደራጁ ወንጀሎች እና በሌሎችም ህገ ወጥ እንቅስቃሴዎች ላይ ሲሳተፉ የተገኙ ስደተኞችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ መጡበት እንደሚመልሱ ዝተዋል።

በሀገሪቷ የሚንቀሳቀሱ የቀኝ ዘመም ፓርቲዎች የስደተኞችን ቁጥር ለመቀነስ መንግስት እሰጣለሁ ያለው ገንዘብ ላይ ጭማሪ እንዲያደርግ በመጠየቅ ላይ ናቸው።




የስዊድንን እሴቶች ስደተኞች እያጠፉ ይገኛሉ በሚል በጥብቅ እየሞገቱ የሚገኙት እነኚህ ፓርቲዎች የገንዘብ መጠኑ ከፍ ቢደረግ ጥያቄውን ተቀብለው ከሀገር ለመውጣት ፈቃደኛ የሚሆኑ በርካታ ስደተኞች ይኖራሉ ብለዋል።

ዴንማርክ በተመሳሳይ ምክንያት ጥብቅ የስደተኞች ፖሊስ በመከተል ላይ ከሚገኙ የአካባቢው ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ሀገሪቷን ለቀው ለሚወጡ ስደተኞችም እስከ 22ሺ ዶላር ድረስ በመክፈል ላይ ትገኛለች።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# አገልጋይነት ክብር ነው!

**አስቀ ፀጋዬ**



አገልጋይነት ክብርን፣ ሞገስን፣ የራስ ፍላጎትንና ጥቅምን ወደ ጎን ትቶ ለሌሎች መስራት ነው። አገልጋይነት ከአንገት በላይ ሳይሆን ከልብ በመነጨ መልኩ ሌሎችን ማገዝ ነው። አገልጋይነት ራስን ዝቅ አድርጎ ሌሎችን ከፍ ማድረግ ነው። አገልጋይነት በራስ ሳይሆን በሌሎች ደስታ መርካት ነው። በበጎ ፍቃደኝነት ሌሎችን ለመርዳት ራስን ማዘጋጀት ነው። የሰዎችን ችግር መረዳትና መጋራት ብሎም መፍትሄ መፈለግ ነው። አገልጋይነት ክብር ነው!

አገልጋይነት ሲባል ታዲያ በግለሰብ ደረጃ ብቻ ተገድቦ የሚቆይ ሳይሆን ከቤተሰብ አንስቶ እስከ ሀገር የሚዘልቅ ነው። በቤተሰብ ውስጥ አገልግሎት አለ። አንዱ አካባቢ ሌላውን አካባቢ ያገለግላል። ወረዳዎች ሕዝብን በልዩ ልዩ መልኩ ያገለግላሉ። ከተሞችም እንደዛው። ሀገርም ሕዝቧን በሕዝቧ ታገለግላለች። አዲሱ 2017 ዓ.ም የአገልጋይነት ዓመት እንዲሆን ተሰይሟል።

አገልጋይነት የሚለው ፅንሰ ሀሳብ መልከ ብዙ ገጽታዎች ያሉት ሲሆን ስጋዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሕሊናዊና ስብዕናዊ እርካታዎችን የሚያጎናጽፍ እሴት ወይም የማንነት መገለጫ እንደሆነ በሰዎች ዘንድ ሲነገር ይሰማል። በአሁኑ ዘመን ደግሞ የአገልጋይነት ትርጉም ለአንድ ተቋም ወይም ግለሰብ ተቀጥሮ መስራትና ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት የሚል ጥቅል ትርጉም ተሰጥቶታል። ይሁን እንጂ አገልጋይነት በውልና በስምምነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን ከራስ በጎ የማድረግ ሀሳብ የሚመነጭ በመሆኑ ገደብ የሌለው ጽንሰ ሀሳብ መሆኑን የሚገልጹም አልጠፉም።

ሕዝብ የሰጠው አደራና ኃላፊነት ላለበት መንግስት ደግሞ አገልጋይነት ዋንኛ እና መሰረታዊ አልፎም ዘላቂነቱን ማረጋገጫ ነው ቢባል ማጋነን አይደለም። ምክንያቱም መንግስት ወደ ስልጣን የሚመጣው በሕዝብ ይሁንታ ነውና። በሕዝብ ይሁንታ ማለትም በምርጫ ወደ ስልጣን የመጣ መንግስት ደግሞ ቃል በገባው መሰረት ሕዝብ የማገልገል ትልቅ ኃላፊነት አለበት። የአገልጋይነት ምሳሌ ሆኖ መታየትም ይጠበቅበታል።

ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መረጃ መሰረት መንግስት ሲቪል ሰርቪስ እያለ በሚጠራው የስራ አወቃቀር ውስጥ 2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሰራተኞች እንዳሉ ይነገራል። እነዚህ በመንግስት የስራ መዋቅር ውስጥ ያሉና ሕዝብን ለማገልገል የተሾሙ አልያም የተቀጠሩ ናቸው። ስለዚህ የነዚህ ሰራተኞች ተቀዳሚና ዋነኛ ተግባራቸው በቅንነትና ታማኝነት ሌላ ነገር ሳይጠብቁ ሕዝባቸውን ማገልገል ነው።

‹‹ሲቪል ሰርቪስ›› የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል ወደ አማርኛ ተወስዶ ሲተረጎም የመንግስት ስራ/አገልግሎት የሚለውን ትርጉም ይሰጣል። በ1940ዎቹ መጀመሪያ የእንግሊዝ ቢሮክራሲ የሆኑ አንዳንድ አሰራሮች በሕንዶች ተለምደው ከዛም በሂደት እነዚሁ አሰራሮች ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ‹‹ሲቪል ሰርቪስ›› የሚለው ቃል የመንግስት ስራንና ሰራተኛን እየተካ የሄደበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

በጥቅሉ ሲታይ ‹‹ሲቪል ሰርቪስ›› በጥሬ ትርጉሙ የመንግስት ፖሊሲን መፈፀም ወይም መንግስትን ማገልገል ትርጉም እንዳለው ‹‹ዲፈረንስ ቢትዊን ኔት›› የተሰኘ ድረ ገጽ "Difference Between Civil Service and Public Service" በሚል ርዕስ ያሰፈረው ጽሁፍ ያትታል። ‹‹ሲቪል ሰርቫንት›› ደግሞ የመንግስትን ፖሊሲዎች የሚፈጽም ሰራተኛ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። በመዝገበ ቃላት ትርጉሙም ቢሆን ሲቪል የሆነ ሰራተኛ ማለት ሰላማዊ የሆነና ስራን የሚሰራ ከጦር ሰራዊት ወይም የመከላከያ ኃይሎች ስራ የተለየ ባህሪ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ሲቪል ሰርቪስ ሲነሳ አብረው የሚነሱ ሁለት ምሰሶዎች አሉ። አንደኛው ከገንዘብና ሀብት ጋር የሚያያዝ ሲሆን ሁለተኛው የሰው ሀብትን፣ ፖሊሲንና ተቋምን የሚያመልከት ነው። በመሆኑም በሁለንተናዊ የአገር ዕድገት ላይ እነዚህ ምሰሶዎች የሚጫወቱት ሚና ሁሉ ከሲቪል ሰርቪስ ዘርፉ የሚጠበቅ እንደሆነ ይታመናል።

አንድ አገር ሚዛናዊ የሆነ የሕዝብ አስተዳደር ስርዓት አለው ለመባል ከፖለቲካዊ የአገረ መንግስት ምስረታ ጎን ለጎን ለገንዘብና ለሰው ሃብት እንዲሁም ለፖሊሲና ለተቋም ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል። ይህ ከሆነ ሲቪል ሰርቪስ በእርግጥም ለመንግስትና ዜጎች ጤናማ የሆነ ግንኙነት ብሎም ለአገር ዕድገት መሰረታዊ ሚና የሚጫወት ዘርፍ መሆኑ ይረጋገጣል።

ሲቪል ሰርቪስ ለዘላቂ ልማትና መልካም አስተዳደር የማይተካ ሚና እንዳለው ይነገራል። በሕዝብ የተመረጠን መንግስት ገለልተኛ የአስተዳደር መዋቅር የሚሸከመው ሲቪል ሰርቪስ በመሆኑ የዴሞክራሲ ሁነኛ አካል እንደሆነ ይቆጠራል።

በዚህ ሚናውም ሲቪል ሰርቪስ ከፍ ያለ የሙያዊና የስነ ምግባር ደረጃዎች ሊኖረው እንደሚገባ ይመከራል። እናም ሲቪል ሰርቪሱ ፖሊሲውን፣ ሕጎችን፣ አሰራር ሂደቶችን፣ ስርዓቶችን፣ ድርጅታዊ አወቃቅርንና ሰዎችን ያካትታል።

ሲቪል ሰርቫንት በመንግስት ተቋማት ውስጥ የተቀጠረ ሰው ማለት ነው። ይህ ሰው አስተዳደራዊ መሳሪያዎችን የሚያንቀሳቅስ፣ መንግስታዊ ውሳኔዎችን የሚያስፈጽም በመሆኑ ሲቪል ሰረቫንቱ የማይተካ ሚና አለው። ይህ ሚናውን ጥግ ድረስ እንዲወጣ ከተፈለገ ደግሞ የአገልጋይነት ባህሪ መላበስ ይኖርበታል።

ዓለም የሄደበትና ጠንካራ ሲቪል ሰርቪስ የገነባበት መንገድ ዓለም አቀፋዊ እሳቤን የያዘ ነው። ጠንካራ ሲቪል ሰርቪስ የሚገነባው አቅምን፣ ችሎታን፣ ቁርጠኝነትን፣ ለሕዝብ ተቆርቋሪነትን መሰረት አድርጎ ሲዋቀር ነው። ሲቪል ሰርቫንቱ ወይም የመንግስት ሰራተኛው በአቅሙና በችሎታው እንዲወዳደርና እንዲመደብ ይጠበቃል። ሲቪል ሰርቪስ ከፖለቲካና ከዳኝነት ስራዎች ውጭ የሲቪል ተግባራትን ለመከወን የተቀጠሩ መንግስት አካላትን ያጠቃልላል የሚባለውም ለዚሁ ነው።

ወደ አገልጋይነት ሀሳብ ስንመለስ ፅንሰ-ሀሳቡ በዘመናት በብዙ ባህሎችና ሃይማኖቶችም ተቀባይነት ያለው ነው። በመሰረቱ፣ አገልጋይነት የሌሎችን ፍላጎት ከራስ ማስቀደምና ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ መንገድ በትህትና ማገልገል መሆኑ ይገለጻል። ከመቀበል ይልቅ በመስጠት ላይ ያተኮረና በማኅበረሰብ ዘንድ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ባህሪይ ነው አገልጋይነት።

የአገልጋይነት አላባውያን ተብለው ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ ትህትና ነው። አገልጋይ ለስራው ትኩረትን ወይም እውቅናን ሳይፈልግ ማገልገልን ብቻ ቀዳሚ ተግባሩ ያደረገ ነው። ትህትና የአገልጋይነት አስፈላጊ አካል በመሆኑ ከራስ ፍላጎት ይልቅ የሌሎችን ፍላጎት ማስቀደምና በምላሹ ምንም ሳይጠብቁ ማገልገልን ይጠይቃል።

ሌላኛው የአገልጋይነት ገጽታ ራስን መስጠት ነው። ይህ ማለት ሌላ ሰውን ለመርዳት ጊዜን፣ ሃብትን ወይም የራስን ምቾት መተውን ያካትታል። ከራስ በላይ ሌሎችን ለማስቀደም ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል። አገልጋይነት ርህራሄና መተሳሰብ ነው። እውነተኛ አገልጋይ የሌሎችን ፍላጎት የሚረዳና ችግራቸውን ለማቃለል የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው።

በዘመናዊው ሕብረተሰብ ውስጥ አገልጋይነት በተለያየ መልኩ ይታያል። ሌሎችን ለመርዳት ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን በሚሰጡ በጎ ፈቃደኞች፣ የታመሙትን ለመንከባከብ ራሳቸውን ለአደጋ በሚያጋልጡ የጤና ባለሙያዎች፣ የሀገር ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ የፀጥታ ባለሙያዎች እና ነገን በቀጣይ ትውልድ ላይ የሚሰሩ መምህራኖች እንዲሁም በየደረጃው ባለው የመንግስት ሰራተኛ ውስጥ ሊገኝ ይችላል።

በስራ ቦታ ያለ ሁሉም ሰው በአገልጋይነት መንፈስ ከሰራ ከሌሎች ጋር የተሻለ ግንኙነትና ትብብር ለመፍጠር አይቸገርም። ይህ ደግሞ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ትልቅ ዕድል ይሰጣል። ምርታማነትና የደንበኞችን እርካታ እንዲጨምር ያደርጋል። አገልጋይነት የአንድነት ስሜትና የቡድን ስራን ያጎለብታል። ሁሉም ሰው ሌሎችን ለማገልገል የጋራ ግብ ላይ እንዲሰራ ያደርጋል። የአገልጋይነት ባህል ለሁሉም ሰው የተሻለና ፍትሐዊ የሆነ አገር ለመፍጠር ይረዳል።

የዜጎች ግልጋሎት ጉዳይ ታዲያ ዘመናዊነትን እንዲላበስ ይጠበቃል። ወጥ በሆነ መንገድ ደረጃውን ጠብቆ በስራ መዋቅር ውስጥ ሊዘረጋ ይገባዋል። እዚህ ጋር የመንግሥት አገልግሎት ጉዳይ የመንግሥት አቋምን የማገልገል ጉዳይ ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ይልቁኑም የሕዝብና የአገር አገልግሎት ነው። ስኬታማ ልማት የሚመጣውና አገር የሚገነባው በስኬታማ ሲቪል ሰርቪስ ስርዓት ነውና።

አሁን ላይ መንግሥት የጀመረውን ሲቪል ሰርቪሱን በሙያተኛ የማደራጀት ተግባርን አጠናክሮ መቀጠል አለበት። ጅምሮቹ ተጠናክረው ከቀጠሉ ጥሩ የሲቪል ሰርቪስ መገንባት ይቻላል። የሲቪል ሰርቪስ ዘመን ተሻጋሪና በመንግስት መለዋወጥ የማይዛባ መዋቅር እንዲሆን ትኩረት ተደርጎ እንደሚሰራ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከዚህ ቀደም ተናግረዋል።

በ2013 ዓ.ም የተዘጋጀው የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ ፍኖተ-ካርታ (2013) እንደሚጠቁመው አዲስ የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲ ከሚገዛባቸው መርሆዎች ዋናው ከስትራቴጂዎችና ከአደረጃጀት፣ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና መሳሪያዎች በላይ ለሰዎች ዕውቀትና የአስተሳሰብ ልህቀት አብልጦ ትኩረት አድርጓል።

ከሰው ሀብት ልማት መስኮች መካከልም በመንግሥት ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲ ለሰዎች የፈጠራ ችሎታ፣ ምጡቅ አስተሳሰብና ሐሳብ የማመንጨት ችሎታ ከእውቀትና ክህሎት በላይ ዋጋ የሚሰጠው "ቅድሚያ ችሎታ ላላቸው" የሚል መርህ አንዱ ነው።

ለሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛነት የሚመለመሉ ሰዎች 'ምሉዕ ስብእና'ን ተላብሰው ዘርፉን እንዲቀላቀሉ፣ ለዜጎች የላቀ ውጤት ሊያስመዘግቡ የሚችሉ፣ ፈጠራን የሚያመነጭ ብሩህ አዕምሮ፣ ምጡቅ አስተሳሰብና የአዳዲስ ሀሳብ ባለቤቶች ሊሆኑ ይገባል።

ስለሆነም የቅጥር ሂደቱን በጥንቃቄ መምራት፤ ጥፋትን ፈጥኖ ማረም፣ ሰንሰለትን ማሳጠር፣ አሰራርን ማቅለል ተገቢ ነው። በተጨማሪም ችግር-ፈቺዎች፣ ለሰራተኞች ግልጽ እቅድ የሚሰጡ፣ አዳዲስ የስራ ሂደቶችን የሚቀርጹና በተግባር ደግፈው ለሰራተኛው የሚያስተዋውቁ ብቁ የስራ መሪዎችን ማፍራት ያስፈልጋል።

ማገልገል ክብር የሆነበት ስርዓት መገንባት በተለይም የመንግሥት ሰራተኞች አገልግሎታቸው በገንዘብና በንብረት ጥቅም የሚለካ ሳይሆን ዜጎችን አክብሮ ከሚሰጥ የላቀ አገልግሎትና ከተገልጋይ ዜጎች እርካታ በሚመነጭ አንጸባራቂ ክብር መሆኑን በተግባር እንዲያረጋግጡ ማድረግ ያሻል።

የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ ፍኖተ-ካርታ ላይ በግልጽ እንደተመላከተው ነጻ፣ ገለልተኛና ሙያዊ ብቃት ያለው የመንግስትና የሕዝብ አገልጋይነትን እውን ለማድረግ የአደረጃጀቶችን ምክንያታዊነት ማረጋገጥ፣ የሕግ የበላይነትን ማስከበር፣ ለውጤት ተኮር አፈጻጸም ትኩረት መስጠት፣ ግልጽነት፣ ተደራሽነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ላይ በትኩረት ይሰራል።

የመንግስት ዘርፍ የሰው ሀብት ልማቱ በተለዋዋጭ ሁኔታዎችና ለውጦች የሚያልፍ በመሆኑ ከሌሎች ዘርፎች በተለየ በማያቋርጥ ለውጥ ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል። በዚህም ምክንያት ከዘመን ዘመን የሚለዋወጥ ቁመናውን የሚወስኑ "ዕሴቶችን" ዜጎች/ተገልጋዮች ከሚፈልጉት ውጤት ጋር የሚጣጣሙ አድርጎ መላበስና ለየዘመኑ ጥያቄ ምላሽ ሰጪ የሆኑ አሰራሮችንም ቀርጾ መተግበርንም እንዲሁ ይጠይቃል።

በእርግጥም በማንኛውም የመንግስት አገልግሎት ዘርፍ የሚሰማራ የሰው ኃይል በብቃትና ችሎታው ተመልምሎና ተመርጦ ከተሰማራ፣ አገልጋይነት አስተሳሰብና እምነት በሕዝብ ውስጥ ከሰረጸ፣ ንቃተ ሕሊና ካደገና በአዲስ እውቀት ከበለጸገ የአገልግሎት ዘርፉ ችግር ይቀረፋል። ስርዓቱ በማይናወጥ ማዕዘን ላይ ከተሰራ ደግሞ 'መንግስት በተቀያየረ ቁጥር የሚቀያየር ሲቪል ሰርቫንት ይዘን እስከመቼ ነው የምንዘልቀው' የሚለው ጥያቄ ገቢራዊ ምላሽ ሊያገኝ ይችላል።

በአጠቃላይ አገልጋይነት ከራስ ፍላጎት ይልቅ የሌሎችን ፍላጎት በማስቀደም በዓለም ላይ ለውጥ ማምጣት ነው። ከመቀበል ይልቅ በመስጠት ላይ ያተኮረ የአኗኗር ዘይቤ ነው፤ እና በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችልም ባህሪ ነው።

ቤተሰብን፣ ማኅበረሰብን ወይም በአጠቃላይ ዓለምን በማገለግል የአገልጋይነት ጽንሰ ሃሳብን መቀበል በሌሎች ሕይወት ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣና ዘላቂ የሆነ የርህራሄና ከራስ ወዳድነት ነጻ የሆነ ትሩፋት ያስገኛል። ይህ ጥንካሬን፣ ድፍረትንና የኃላፊነት ስሜትን ይጠይቃል።

የተሻለ አገር ለመፍጠር የአገልጋይነት ባሕል አስፈላጊ ነው፤ ስለዚህ በመላው አገሪቱ በሚገኙ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ከፌዴራል እስከ ወረዳ ተቀጥረው የሚሠሩ የመንግሥት ሠራተኞች እና የሕዝብ አገልጋዮች በየተሠማሩበት የሥራ መስክ አገልግሎት በሚሠጡበት ወቅት በትህትና፣ በደግነትና በስራ ወዳድነትና በአገልጋይነት መንፈስ በማገልገል ለአገር እድገትና ብልፅግና የራስን ድርሻ መወጣት ይገባል።

አገልጋይነት በተገልጋይ እርካታ የሚገኝ ሐሴት ነው። ለሀገር ክብር ነው! ታላቅ ስብእናም ነው! ዝቅ ብለን አገልግለን፤ ታላቅ ሃገር ለመገንባት ኢትዮጵያን እናገልግል! አገልግሎት ሰጪነት ግን ከራስ እንደሚጀምር ልብ ይለዋል። አገልጋይነት ከራስ ሲጀምር ግልጋሎቱ ሌሎችም ይተርፋል!!

# ርዕሰ አንቀፅ

## 2017 ዓ.ም ለሰላማችን ተግተን የምንሠራበት ሊሆን ይገባል!

ባሳለፍነው ዓመት አልፎ አልፎ በሀገሪቱ የተስተዋሉ የጸጥታ ችግሮች አደብ ገዝተው ተማሪውም ወደ ትምህርት ቤት፣ መምህሩም ወደ ማስተማሩ ፣ ነጋዴው ወደ ንግዱ ፣ ገበሬውም ወደ እርሻው ሌላውም እንዲሁ ወደ ሙያው ፊቱን መልሶ የተረጋጋ ኑሮ መኖር አለበት። በ2016 ዓ.ም ያየነውንና የሰማነውን ችግር ለማስቀረት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት አለበት። ችግሮች ለምን ተፈጠሩ ላይባል ይችላል ነገር ግን የተፈጠሩ አለመግባባቶች እንዴት መፍትሄ ማግኘት አለባቸው ብሎ በሰከነ መልኩና በማስተዋል መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ችግሮችን ለመፍታት በሰለጠነ መልኩ መቀራረብ ፣መነጋገርና መግባባት ይገባል። ሰጥቶ መቀበል ለሁሉም ችግሮች መፍቻ ቁልፍ ነው። ሀገር የምታድገው ፣ ልማት እና ኢንቨስትመንት የሚስፋፋው ፣ ቱሪስቱ ወደ ሀገራችን የሚጎርፈው ፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እያበበ የሚሄደው በጋራ ስለሀገርና ሕዝብ በማሰብ፣ በመተባበርና ልዩነት አጥብቦ አንድነትን በማጠናከር ነው። ለዚህ ደግሞ ለሰላማችን አብዝተን መሥራት አለብን።

የውስጥ ችግሮቻችን የሰፉና ሀገር የተዳከመች በሚመስላቸው ወቅት የሀገራችንን ዕድገት የማይመኙ የውጪ ኃይሎች ሁሉ ክንዳቸውን ሊያሳዩን ይሞክራሉ። እኛው በከፈትነው መስኮት ውስጣችንን አጮልቀው በመመልከት ሊከፋፍሉን ያስባሉ። አንዳንዶች ታሪካዊ ጠላቶች በቀጥታ አንዳንዶች ደግሞ በእጅ አዙር ሊያጠቁን ያስባሉ፤ያቅዳሉ። ትብብርና ኅብረት ይፈጥራሉ። ይሄ ከዚህ በፊትም በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ታይቷል፤ አሁንም እየታየ ነው። ይህንን የውጪ ጠላት ሀሳብና ዕቅድ ማክሸፍ የምንችለው ታዲያ በራሳችን የውስጥ ኃይላችንንና አንድነታችንን ማጠንከር ስንችል ነው። ለሰላማች ዘብ መቆም ከሁሉም በፊት ቅድሚያ የምንሰጠው ሥራ መሆን አለበት። በአዲሱ ዓመት መጥፎ ሥራን በማስወገድና መልካሙን በማጠናከር የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ማስቀጠል ያስፈልጋል። ሰፊ ቁጥር ያለው ሥራ አጥ ዜጋ የሥራ ዕድል ባለቤት የሚሆነው በሁሉም አቅጣጫ በመላ ሀገሪቱ ተንቀሳቅሶና ያለ ስጋት ሰርቶ መኖር ሲችል ነው። ለዚህ ደግሞ የሰላም ዋጋው ከፍተኛ ነው።

ኢትዮጵያ ከ90 ከመቶ በላይ የአማኒያን ሀገር መሆኗ ይታወቃል። አብዛኛው ሕዝብ እምነት ያለው እምነቱንና ሃይማኖቱን የሚያከብር ነው ። ክርስቲያን ፣ ሙስሊም ዋቄፈታ ሳይባባል ተከባብሮና ተፋቅሮ የኖረና የሚኖር ሕዝብ ነው። ያለው ለሌለው በመስጠት፣ በመጠያየቅና በመረዳዳት የኖረ ሕዝብም ነው። በችግር ወቅት፣ በሀዘንና በደስታ ሰዓት ሁሉ አለሁ ብሉ ከጎን የሚቆም፤ተካፍሎ የሚበላ ላጣ የሚመጸውት ጭምርም ነው። በየትኛው የእምነት ተቋም መረዳዳት አንዱ የሃይማኖታዊ አስተምህሮ ነው። በጎ ሥራ መሥራት በጎ አድራጎት ደግሞ ከተደረገለት ሰው በላይ ደስታን የሚሰጠው በጎ አድራጎት ላደረገው ወገን ነው። የተቸገሩ ወገኖቻችንን አለንላችሁ ብሎ ከፊት መቆም በዓላትን በደስታ አሳልፉ ብሎ ከተረፈን ላይ ሳይሆን ካለን ላይ ማካፈል ለራሳችን ከምናገኘው ሀሴት በላይ የፈጣሪን ትዕዛዝ መፈጸም ስለሆነ እርካታውም ከፍ ያለ ይሆናል።

በበዓላት ወቅት መረዳዳቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ችግረኞች መረዳት ያለባቸው እንደ ችግራቸው ስፋትና ጥልቀት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መሆን አለበት። በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ ብዙዎች ተጎድተዋል። ያዘኑትን ማጽናናት የተፈናቀሉትን ደግሞ አለንላችሁ ማለት ይገባል። በአዲሱ ዓመት ከመጥፎ አስተሳሰቦች በመራቅ መልካም መልካሙን ማጠናከር ያስፈልጋል። ለሀገራችን ሰላም ተግተን መቆምም ይጠበቅብናል።

2017 ዓ.ም ሰቆቃ የማንሰማበት የሰላም፣ የፍቅር፣ የአብሮነት፣ የመከባበርና የመረዳዳት እንዲሁም የብልጽግና ዘመን እንዲሆንልን ሁላችንም ለሰላማችን አብዝተን ዘብ መቆም ይገባናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በኮሪደር ልማት የደመቀው አዲስ ዓመት

**ሰላማዊት ውቤ**

የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ከሌሎች ዓውድ ዓመቶች የተለየ ነው፡፡ እንደ ስሙ አዲስ ነገር የሚፈልግና በዚሁ መንፈስ የምንቀበለው ነው፡፡ ከአዲስ ልብስ ከአዲስ ጫማ ባሻገር መንፈሳችንና ልባችንም በአዲስ የሚታደስበት ነው፡፡ ዓይናችን በየዓመቱ አዲስ ነገርን ማየት ይሻል፡፡ ውጫዊ አካላችን ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ አስተሳሰባችን፤ ስብዕናችን፤ አካባቢያችን አዲስ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

ዘንድሮ መዲናችን አዲስ አበባ ይህን ዓይነቱን የነዋሪዋን ፍላጎት የማሟላት ጉዳይ ሰምሮላታል፡፡ አዲስ አበባ መሪዎቿ በዕቅድ ዘመናቸው ሲሉት እንደነበሩት በአዲስ እየፈካች ትገኛለች፤ በእርግጥም አዲስ አድርገዋታል፤ እያደረጓትም ይገኛሉ፡፡ ስሟን የሚመጥን የተለያዩ የልማት ሥራዎችን እያከናወኑ መገኘታቸው ምስክር ይሆናቸዋል፡፡ ከ28 ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ያለው የመንገድ ኮሪደር ልማት በዘንድሮ አዲስ ዓመት አዲስ አበባን አዲስ ካደረጓት በዋናነት ይጠቀሳል፡፡

ይህ የመንገድ ኮሪደር ልማት መዲናዋን በቃላት ከሚነገረው በላይ አስጊጧታል፡፡ በከተማዋ አራት አቅጣጫ ሌት ከቀን እየተከናወነ ያለና አብዛኛው ክንውኑ የተጠናቀቀም በመሆኑ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል፡፡ ዘና ፈታ እያለበትም ይገኛል፡፡ የመንገድ ኮሪደር ልማቱ በውስጡ ሌሎች የልማት ፕሮጀክቶች መያዙ ነዋሪዋ ዘና ለማለቱ ምቹ መደላድል ፈጥሮለታል፡፡

አብዛኛው ነዋሪ ከዋናው መንገድ ግራና ቀኝ በተገነባው ምቹ ስፍራ አረፍ ለማለት በቅቷል፡፡ ዘንድሮ በመዲናችን አብዛኞቹ አካባቢዎች አረፍ በማለት የአረንጓዴ ልማት ሽፋኗን 17 በመቶ ካደረሱት ተክሎች የሚመነጨውን ንፁህ አየር መማግ ተችሏል፡፡ ሥፍራዎቹ መንገደኛ ሲደክም ብቻ ሳይሆን አዛውንቶችም አረፍ የሚሉባቸው ሆነዋል፡፡ ለጥናትና ምርምርም ሆነ ለተለያዩ ተግባር የገቡ፤ እየኖሩ ያሉ የውጭ ሀገር ዜጎችም ጭምር አረፍ የሚሉባትና ቅኝትና አድናቆት የሚቸሯት ተመራጭ ሆናለች፡፡ ጥንድ፣ጥንድ ለሆኑ ወጣቶች የፍቅር ወሬ ያስኮመኩማሉ፡፡

በእነዚህ ስፍራዎች ያለው የእንጨት ወንበር ከቀድሞዎቹ ድንጋይ ወንበሮች ይልቅ ምቾት በመስጠት ያስቀምጣል፡፡ ቀድሞ ከአንዳንድ የመነፈሻ ቦታዎች በስተቀር በሁሉም መንገዶች ግራና ቀኝ ድንጋይ ወንበሮቹ ነበሩ እያልኩ አይደለም፡፡ ሲጀመር መንገዶቹ ለእግር መንገድም የማይበቁ በመሆኑ እግረኛው ከመኪና ጋር እየተጋፋና ለአደጋ እየተዳረገ የሚሄድባቸው መሆናቸውንም አልዘነጋሁም፡፡

በኮሪደር ልማቱ እንዲህ ዓይነቶቹ መንገዶች ተወግደዋል፡፡ ምቹና እግረኛው በሰው ብዛት ሳይጨናነቅና ሳይጋፋ እንደልቡ እየተራመደባቸው ባሉ ሰፊ የእግረኛ መንገዶች ተተክተዋል፡፡ በእነዚሁ ሥፍራዎች አቅራቢያ በተገነባው የሞተር አልባ ትራንስፖርት መንገድ አዋቂዎች ያለ እንከን ሳይከላቸውን ይጓዛሉ፡፡ ወላጆች ትምህርት ቤት በመዘጋቱ እረፍት ላይ ያሉ ልጆቻቸውን እሁድና ቅዳሜ ብቻ ሳይሆን ሰርክ ሣይክል ያለማምዳሉ፡፡

ከመንገድ ኮሪደር ልማቱ ፕሮጀክት ጋር ተያይዞ ዘንድሮ የእግር መሸጋገሪያ ድልድዮችም እየተገነቡ ነው፡ ፡ ራስ መኮንን ድልድይን ይዞ በተለያዩ ስፍራዎች የሚገኙ የወንዝ ተፋሰስም አካቷል ልማቱ፡፡ እነዚህ አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች በከተማችን የሚገነቡ የእግር መሸጋገሪያ ድልድዮችና ተፋሰሶች እንደቀድሞው ለኅብረተሰቡ ስጋት የሚሆኑ አይደሉም፡፡ በተለይ የእግር መሸጋገሪያ ድልድዮቹ እንደ ቀድሞው ውበት የሌላቸው ከመሆናቸው በዘለለ በመጥፎ ጠረን በመጠፍነግ አላሳልፍ የሚሉ አይደሉም፡፡

አራት ኪሎ የሚገኘውን ጨምሮ ሁሉም ደረጃቸውን የጠበቁ ናቸው፡፡ በግራ ቀኝ ያሉ መደበቂያዎች በመወገዳቸው ዘረፋና የትኛውንም ዓይነት ነውረኛ ተግባር ለመፈፀም አያመቹም፡፡ ከምንም በላይ ሁሉም ሲጠናቀቁ የመዲናዋን የመንገድ አማራጭ የሚያሰፉ ናቸው፡፡ ግንባታቸው የተከናወነበት ጥሬ ዕቃ ለከተማዋ ውበት ይለግሳል፡፡

**በአራቱም ማዕዘን ያለው የረጅሙ እግር መንገድ ውበት ታይቶ አይጠገብም። ደግሞ ምቹና ማራኪዎቹ መናፈሻዎችና ማረፊያዎች አሁን ላይ ክረምት ወለዱና ወቅታዊው ብርድ ባይኖር ቤታችሁ ግቡ ግቡ አያሰኙም**

ደረጃውን የጠበቀ ፓርኪንግ (የተሽከርካሪ ማቆሚያ) እንዲሁም ከትራንስፖርት በዘለለ ነዋሪው የሕዝብ የጋራ መገልገያ ሥፍራዎችም የ2017 ዓ.ም የመዲናችን አዲስ አበባ ስጦታዎች ናቸው፡፡ እነዚህም የተገነቡትና እየተገነቡ ያሉት በአራቱ አቅጣጫ እየተካሄደ ከሚገኘውና ከተጠናቀቀው ከመንገድ የኮሪደር ልማት ጋር ተያይዘው ነው፡፡

በልማት የሚሸፍኑት ሥፍራም ቀላል አይደለም፡፡ በጥቅሉ ከ28 ኪሎ ሜትር በላይ ይባል እንጂ ለመኪናም ሆነ ለእግርና ለማንኛውም እንቅስቃሴ አስቸጋሪ የነበሩ አካባቢዎችን ምቹ በማድረጉ ረገድ ትልቅ ሚና አለው፡፡

አንድ ባንድ እንያቸው ብንል ከመገናኛ ዲያስፖራ አደባባይ፣ ከአራት ኪሎ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ድረስ 6ነጥብ4 ኪሎ ሜትር በመሸፈን የመዲናችንን አዲስ ገጽታ በእጅጉ እየለወጡ ያሉ ናቸው፡፡ ከአራት ኪሎ በመስቀል አደባባይ እስከ ቦሌ ድልድይ ሰባት ኪሎ ሜትር ዘልቀው ውበትን አጎናጽፈዋታል፡፡

ከፒያሳ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ዙሪያ፤ በለገሀር ሜክሲኮ፤ በሣር ቤት በኩል እስከ ወሎ ሰፈር 10 ኪሎ ሜትር፤ ከቦሌ አየር መንገድ እስከ መገናኛ ዲያስፖራ አደባባይ 4ነጥብ9 ኪሎ ሜትር ውበት አጎናፅፈዋል፡፡ በተለይ ፒያሳ ዘንድሮ በእጅጉ ተለውጣ ምቹ ሆናለች፡፡ ሙሉ በሙሉ ውስጥ ለውስጥ የነበረው የጠለሸ ገጽታዋ ተለውጧል፡፡ ከበስተጀርባዋ ከትመው የነበሩት እነ ሠራተኛ ሰፈር፣ ዶሮ ማነቂያና ሌሎች የጠለሹ መንደሮችና ቤቶች ዘንድሮ በኮሪደር ልማት ውበት ተላብሰዋል፡፡

ዛሬ ላይ የደከሙና የፈራረሱ የጭቃ ቤቶች መገኛዋ አቧሬም አልፎላታል፡፡ እነዚያ በየጉራንጉሩ የተገጠገጡ እርጅና የተጫናቸው ቤቶች በፍጥነት በትልልቅ ፎቆች እየተተኩ ነው፡፡ ሪል ስቴትም ሞልቶባቸዋል፡፡ ከፒያሳ ሲመጣ በአራት ኪሎ ታጥፎ ቀበና የሚዘለቅበት መንገድም በየዳሩ የነበሩትን ግንባታዎች አስወግዶ አስፋልቱ ቅቤ መስሎ ተገንብቷል፡፡ ስፋቱም ፈረስ ያስጋልባል፡፡

በአራቱም ማዕዘን ያለው የረጅሙ እግር መንገድ ውበት ታይቶ አይጠገብም፡፡ ደግሞ ምቹና ማራኪዎቹ መናፈሻዎችና ማረፊያዎች አሁን ላይ ክረምት ወለዱና ወቅታዊው ብርድ ባይኖር ቤታችሁ ግቡ ግቡ አያሰኙም፡፡ ዘንድሮ በኢትዮጵያ አዲስ ዓመትን ነዋሪው እየተቀበለው ያለው እንደ ድሮው በየቤቱ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በእነዚህ ስፍራዎች ጭምር ዘና ፈታ በማለት ነው፡፡

በየአካባቢው ያሉትን የውሃ ፏፏቴዎች ከቦ ፎቶ በመነሳት፣ በማየትና አካባቢውን ጠቅላላ በማድነቅ፤ ነው የሚያሳልፈው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች በተገነቡ የጋራ መገልገያዎች ሻይ ቡና በማለትም አዲስ ዓመትን የተቀበለው ነዋሪ በርከት ነው፡፡ ይህ ወደፊት ነዋሪው በእነዚህ ስፍራዎች የልጆቹን ልደት፣ ሠርጉንና የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮቹን ሳይቀር የማይከውንበትና አካባቢውን እያደነቀ ዘና ፈታ የማይልበት እንደሌለ ያመላከተ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ መልካም አዲስ ዓመት!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# ዘወትር በምሥጋና...

መልካምሥራ አፈወርቅ

### የአዲስ ዓመት ዋዜማ ...

የአዲስ ዓመት ድባብ አካባቢውን ማወድ ይዟል። በርካቶች ለአውደ ዓመቱ ዝግጅት ሽብረብ እያሉ ነው። አንዳንዶች የመጪውን ዘመን ዕቅዳቸውን ያልማሉ። ሌሎች ደግሞ ባጠናቀቁት ዓመት የከወኑትን ስኬት እያስታወሱ፣ ዳግም ስለነገው እቅድ ይዘዋል።

ከዚህኛው መንደር ከአንደኛው ግቢ ደግሞ ውሎ በተለየ መልኩ ቀጥሏል። እንደ አበባ የፈኩ ሕጻናት ቀኑን በተለየ ሥሜት ተቀብለው እየፈነጠዙ ነው። የአብዛኞቹ ገጽታ በፈገግታ በርቷል። እርስ በርስ ፍቅርና ጨዋታን መጋራት ይዘዋል። ዛሬ በዚህ አጸድ ደስታ እየተመነዘረ ሳቅ ጨዋታ እየደራ ነው። ሁሉም ይህን ስሜት በእኩል መጋራት ይዘዋል።

ከዚህ እውነት ባሻገር ሌላው አይደበቄ ሀቅ በግልጽ እየታየ ነው። የነዚህ ዕንቦቃቅላ ወላጆች ደስታ ከፊታቸው ይነበባል። ሁሉም ስሜታቸው በአንድ መጋመዱ ግልጽ ነው። ዛሬም ሀሳባቸው በእኩል ተጣምሯል። ጨዋታ ወጋቸውን አመሳሳሎ፣ ችግር ሀዘናቸውን ያመሳሰለው ሚስጥር ደግሞ የጋራ አጀንዳቸው ከሆነ ቆይቷል። የልጆቻቸው ጤና፣ የፍሬዎቻቸው ሕልውና ጉዳይ።

በእነሱ ዘንድ ትውውቅና መግባባት ይሉት ጉዳይ መስፈርት ሆኖ አያውቅም። ስሜታቸው በአንድ ታስሮ ጨዋታቸው የጋራ ለመሆን አይዘገይም። የሁሉም እናቶች ትከሻ ስለልጆቻቸው ሰፊ እንደሆነ ጊዜያትን ዘልቋል። ወደፊትም ለእነሱ ከሆነ ድካም ይሉትን አያውቅም። እጆቻቸው ቢዝሉም ፈጽሞ አይሸነፉም።

### ልብ ለልብ ...

እናቶቹ በተገናኙ ቁጥር ስለ ልጆቻቸው አበክረው ያወጋሉ። ሁሌም የዛሬው ኑሯቸው፣ ያሳሥባቸዋል። የነገ ተስፋቸው ያሰጋቸዋል። የአብዛኞቹ እናቶች ስሜት ከሌሎቹ እናቶች ማንነት የተለየ ነው። እነሱ ‹‹ከልጆቻችን በፊት እኛን ያስቀድመን›› ብለው አያውቁም። ልጆቻቸው ከእነሱ አንዲት ደቂቃ ቀድመው ቢያልፉ /ቢሞቱ/ይመርጣሉ።

ሕጻናት ሲወለዱ ከአፈጣጠር ጋር ተያይዞ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ችግሮች ይኖራሉ። ከነዚህ መካከል የነርቭ ዘንግ ክፍተት /ስፓይና ቢፊዳ/ እንዲሁም ሀይድሮሴፋለስ ዋንኛነት የሚጠቀሱ ናቸው። የሕክምና ባለሙያዎች እንደሚሉት እነዚህ ችግሮች በእርግዝና ክትትል ግዜ የፎሊክ አሲድ ንጥረነገር ባለመውሰዳቸው የሚከሰቱ እክሎች ናቸው።

የነርቭ ዘንግ ከጀርባ የመሀለኛው ክፍል የላይኛውንና የታችኛውን ይዞ ከሀያ አንደኛው እስከ ሀያ ስምንተኛው የእርግዝና ቀናት ድረስ መዘጋት ያለበት የራስ ቅልና የሕብለሰረሰር ዘንግ ክፍተት ነው።

ሀይድሮ ሴፋለሰስ ደግሞ በጭንቅላት ወስጥ ከመጠን ያለፈ ፈሳሽ ሲያጋጥም ሲሆን በእርግዝና ግዜና ከወሊድ በኋላ በኢንፌክሽን ምክንያት ሊከሰት የሚችል ችግር ነው። የጭንቅላት መጠን በፍጥነት ማደግና መጨመር ሕመሙ ስለመከሰቱ ያመላክታል።

ይህ አይነቱ ሕመም የተከሰተባቸው ሕጻናት በወቅቱ የቀዶ ሕክምና ማግኘት ከቻሉ በጭንቅላታቸው ላይ ከመጠን በላይ የተከሰተውን ፈሳሽ ማስወገድ ይቻላል። የሕክምና ባለሙያዎች እንደሚሉትም በወቅቱ ሕክምና መደረጉ የነርቭ ሕዋሳቱ የከፋ ችግር ሳይደርስባቸው የሕጻናቱን ሕይወት ለመታደግ ያስችላል።

ወደመነሻችን እንመለስ። መግቢያችን ላይ ወዳነሳናቸው ወላጆችና ሕጻናት። እነዚህ ወገኖች ከእርግዝና ጋር ተያይዞ በሚከሰቱ የጭንቅላትና የነርቭ ዘንግ ክፍተት ሳቢያ ዋጋ የሚከፍሉ ቤተሰቦች ናቸው። አብዛኞቹ ወላጆች እናቶች ቢሆኑም ስለልጆቻቸው የመልካም አባት ተምሳሌት የሆኑ ጥቂት አባቶችም ተቀላቅለዋቸዋል።

ከእነዚህ ወላጆች ጋር የሚታዩ ልጆች ጭንቅላታቸው ላይ በሚከሰት ችግር ለተደጋጋሚ ቀዶ ሕክምና የወሰዱ፣ አልያም በመውሰድ ላይ የሚገኙ ናቸው። በተመሳሳይ የጀርባ ላይ ክፍተት ያለባቸው ሕጻናት በአብዛኛው ከወገባቸው በታች መንቀሳቀስ የማይችሉ ናቸውና የዕድሜ ልክ ዳይፐር ተጠቃሚ ሆነዋል።

ከነዚህ ሕጻናት መሀል ገሚሶቹ ከወላጆቻቸው ጋር በወጉ የሚግባቡ ናቸው። የተወሰኑት ደግሞ ሙሉ ለሙሉ የሌሎችን እገዛ የሚሹና የእይታም ሆነ የመግባባት ልማድ ታይቶባቸው የማያውቅ ሆነው ቀጥለዋል። ይህ እውነት ልጅ ወልዶ በጤና ለማሳደግ ለሚጓጓ ወላጅ ፈታኝ የሚባል ክፉ አጋጣሚ ነው።



ብዙ ግዜ በቤተሰቡ መሀል እንዲህ አይነት ልጆች በተወለዱ ግዜ የመከራ ዳፋው የሚወድቀው በእናቶች ትከሻ ብቻ ይሆናል። እንደውም አንዳንድ አባቶች የልጆቹን ችግር ባዩ ግዜ ትዳር ፈተው፣ ቤታቸውን በትነው ይርቃሉ። ብዙ ናቸው ባይባልም ጥቂት ልበ መልካም አባቶች ደግሞ የልጆቻቸውን ችግር ተቀብለው ሕመም ስቃያቸውን በእኩል ይጋራሉ።

**ሆፕ. ኤስ .ፒ. ኤች/ Hope œSPH/** የተባለው ግብረሰናይ ድርጅት በሀገራችን ብቸኛው በስፓይና ቢፊዳና ሀይድሮሴፋልስስ ችግር ላይ አተኩሮ የሚሰራ ተቋም ነው። ድርጅቱ በዘውዲቱና በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሎች ወላጆችን የማማከርና ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባራትን ይከውናል።

በችግሩ ተጠቂ የሆኑ ሕጻናት ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ የሕህክምና መሳሪያዎችን ከውጭ አገራት በማስመጣት የስልጠና መርሀግብሮችን ያመቻቻል። ከየክልሉ ለልጆቻቸው የሕክምና ክትትል የሚመጡና ተቀባይ ዘመድ ለሌላቸው ወገኖችም በቂ ማረፊያ በማዘጋጀት ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

የድርጅቱ መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ቤዛ በሻህ በዚህ ችግር ተጠቂ በሆነው ልጃቸው ምክንያት ድርጅቱን ከፍተው መሰል ወላጆችና ተጎጂ ልጆቻቸውን ለማሰባሰብ ምክንያታቸው ሆኗል።

እሳቸው አብዛኞቹ ወላጆች በተለይም እናቶች የሚደርስባቸውን ሕመምና ችግር ይጋሩታል። ልጃቸው ደግሞ ከሌሎች ሁሉ ይለያል። የመናገር፣ የመስማት፣ የማየትና የመንቀሳቀስ ችግሮች አሉበት። ሁልግዜ ግን ትንሹ ህዝቅኤል ብሩህ ፈገግታ ከፊቱ አይጠፋም።

እናት ቤዛ ሁኔታው ቢያሳዝናቸውም ፈጽሞ ተስፋ አልቆረጡም። የእሱ ተፈጥሯዊ አጋጣሚዎች ለበርካታ ወላጆችና ልጆቻቸው ምክንያት ሆኖ በከፈቱት ተቋም ብዙሀንን ማሰባሰብ ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ሰሞኑን አዲስ ዓመትን አስመልክቶ በድርጅቱ በነበረው መሰባሰብ የችግሩ ተጠቂ የሆኑ ሕጻናትና ወላጆቻው በእንግድነት ተገኝተው የአዲስ ዓመትን ዋዜማ አክብረዋል።

ከሕጻናት እንግዶቹ መካከል አብዛኞቹ፣ በዊልቸር የሚጠቀሙ፣ ጥቂት የማይባሉትም በእናቶቻቸው ትከሻ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ራሳቸውን ችለው የሚጓዙትም ቢሆኑ ከወላጆቻቸው የተለየ ትኩረትና ክትትል የሚርቁ አይደሉም። በግቢው ማረፊያ የሚስተናገዱ የሩቅ እንግዳ ወላጆችም ጨቅላ ልጆቻቸውን እንዳቀፉ በዝግጅቱ ታድመዋል።

ዕለቱን በነበረው የአዲስ ዓመት አቀባበል በርካቶቹ ከከተማው ራቅ ካለ ስፍራ የተገኙ ናቸው። ሁሉም በሚባል ግምት ግን ገጽታቸው ላይ ደስታ ይነበባል። የልጆቻቸው እርስ በርስ መገናኘትና የወላጆች ስሜትን መጋራት የተለየ ስሜት አሳድሯል።

አብዛኞች የቅርብ ዘመድ ያህል ተቀራርበው እያወጉ ነው። የውስጣቸውን ቋጠሮ ፈተው፣ ይወያያሉ፣ ልብ ለልብ. መናበባቸው ደግሞ የጋራ ሕመማቸውን አስታግሷል። ተመሳሳይ ቁስላቸውን ፈውሷል። ዝም ያሉት ያዳምጣሉ፣ የሚናገሩት ደግሞ የሌሎችን ስሜት ይጋራሉ። የግቢው ድንኳን መልከ ብዙ ፊቶች ይታዩበታል። ፈገግታ፣ ዝምታና ብሩህ ተስፋ።

በመድረኩ ላይ የወጡት ሕጻናት በተኮላተፈ አንደበት ኅብረዜማ ማሰማት ይዘዋል። ትንንሾቹ በልካቸው በተዘጋጁ ወንበሮቻቸው ይንቀሳቀሳሉ። በእህት ወንድሞቻቸው፣ በእኩያ ባልንጀሮቻቸው ታጅበዋል። ወንዶቹ ‹‹ሆያሆዬ ›› እያሉ ነው። ሴቶቹ ደግሞ አበባዬ ሆሽን ያዜማሉ። ዝብርቅርቁ ድምጻቸው አይረብሽም። የእነሱ ደስታ እጥፍ ሆኖ ስሜቱ ወደሌሎችም መጋባት ጀምሯል።

እንደ አዲስ ዓመት ልማድ የወረቀት አበባ ስለው ‹‹እንኳን አደረሳችሁ›› እያሉ ታዳሚውን ዘንድ የደረሱ ወንድ ሕጻናት ምርቃትና በረከትን አላጡም። ሁሉም ስለምኞታቸው የወጉን አድርሷቸዋል። የአዲሱ ዓመት ዋዜማ ንጹህ ልቦና ባለቸው ሕጻናት መልካም ምኞት መበሰሩን ቀጥሏል።

### የጥያቄው መልስ ...

ከዚህ ቆይታ በኋላ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ቤዛ በሻህ በድንገት አንድ ጥያቄ አቀረቡ። ጥያቄው በዝግጅቱ ለታደሙት ወላጆች በሙሉ የደረሰ ነበር። እንዲህ ይላል።

**‹‹እኛ ሁልግዜ የምንኖረው ለልጆታችን ነው። ሀሳባችንም ለእነሱ ብቻ ያተኩራል። በእናንተ እሳቤ ግን ምርጥና ውጤታማ ወላጅ ማለት ምን ማለት ነው?**

ይህ ጥያቄ በስፍራው ለታደሙት ወላጆች በሙሉ ከጥያቄ በላይ ነበር። ምክንያቱም በዚህ ሀሳብ ውስጥ ብዙ ታሪኮች አሉ። በርካታ አይገለፄ መከራዎች፣ ያልታበሱ ዕንባዎች በግልጽ ይታያሉ። በሁሉም ልቦና ውስጥ ለመመለስ፣ ለመናገር የሚከብዱ ውጣውረዶች ሊታወሱ ግድ ነው።

ለአፍታ ያህል ከበድ ያለ ዝምታ ሰፈነ። ዳሩ ብዙ አልቆየም። ተከታታይ እጆች መታየት ጀመሩ። ዕድሉ ውቢት ለተባለች እናት ተሰጠ። የመነጋገሪያውን ማይክ በእጇ እንደ ጨበጠች የውስጧን ሀሳብ ትዘረግፈው ያዘች።

**‹‹ከእግዜር ስለተሰጠን ሁሉ ምላሻችን ምስጋና ነው‹‹**

‹‹ልጄ ሰባተኛ ዓመቱን ሊይዝ ነው። በተሰራለት ተደጋጋሚ ቀዶ ሕክምና ግራና ቀኝ ‹‹ሼንት›› የተባለ ማገገሃ ገብቶለታል። ሰሞኑንም ተጨማሪ ቀዶ ሕክምና ላይ ተሰርቶለታል። ቀደም ሲል በእግሩ አይሄድም ነበር። አሁን ግን ሕክምናው ረድቶት መራመድ ጀምሮልኛል። እሱ ገና ትንሽ ልጅ ቢሆንም ሲከፋኝ፣ ሲጨንቀኝ ፊቴን አይቶ ውስጤን ይረዳል። ‹‹አይዞሽ እናቴ ለእኔ ነው ቁጭ ያልሽው፣ በእኔ ነው የከፋሽ›› ይለኛል። ይህኔ ላለቅስ የፈለኩትን ትቼ ፈገግታ አሳየዋለሁ። ደስ ይለዋል።

እኛ በውስጣችን የበዛ ሀዘንና ትካዜ ይዘናል። ሁሌም ግን ትዕግስት ሊኖረን ግድ ነው። በእኔ ዕምነት ይህ ችግር ለእኛ ለወላጆች ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው። ይህን ደግሞ አምነን በምስጋና ልንቀበለው ያስፈልጋል።

እንዲህ ስንሆን መልካም ወላጆች እንሆናለን፣ በልጆቻችን ተስፋ እናያለን። ጥንካሬን እንወርሳለን አሁን ላይ በየሆስፒታሉ ችግሩ በጨቅላ ሕጻናት እንደ አዲስ ሲከሰት እያየን ነው። እሱ ከፈለገ ደግሞ በአንዴ ታሪክ ሊቀይር ይችላል። ››

ቀደም ሲል የተነሳው ሀሳብ ጥያቄው ተደገመ።

**‹‹ምርጥና ውጤታማ ወላጅ ማለት ምን ማለት ነው ?**

አሁንም አንዲት እናት እጇን አወጣች ።

**‹‹ልጄ ከእግዜር የተሰጠኝ ፀጋ ነው‹‹**

‹‹ልጄ አስራ ሶስት ዓመቱ ነው። ዛሬም ድረስ ያለ አባት አሳድገዋለሁ። ብዙ ችግሮች ቢኖሩበትም በእናትነቴ እጅግ እኮራበታለሁ። እሱ ማለት ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ ጸጋ ነው። ለአንድም ቀን ፈጣሪን ‹‹እንዲህ አይነት ልጅ ለምን ሰጠኸኝ ስል አማርሬው አላውቅም። ሁሌም በምስጋና ስሙን እጠራዋለሁ። ልጄን ተሸክሜው እውላለሁ፣ ተሸክሜውም እሰራለሁ። በዚህ ደግሞ እጅግ ደስተኛ ነኝ። ከግዜ በኋላ ትንሽ አፉን ይይዘው ጀምሯል። እንዲያም ሆኖ ‹‹አይዞሽ እናቴ›› ሲል ያበረታኛል። ይህን ስሰማ ፈጣሪ በሰጠኝ ጸጋ አመሰግነዋለሁ።

**‹‹እናቴ ሆያ ሆዬ ብጨፍር ኖሮ ብሩ ይጠቅምሽ ነበር‹‹**

ማህሌት ሽቶ የሕጻን ያሬድ ብርሀኑ እናት ነች። እሷም ምርጥና ውጤታማ ወላጅ ማነው የሚለው ጥያቄ ይመለከታታልና የውስጧን ተንፍሳለች። ‹‹ልጄ ያሬድ የሀይድሮ ሴፋለስ ሕመም ተጠቂ ነው። ችግሩ የታወቀው ከተወለደ ከአንድ ዓመቱ በኋላ ነበር። መራመድ ሲያቅተው፣ ሲንቀጠቀጥ ሰዎች አግዘውኝ በሀኪሞች ችግሩ ተለየ።

አባቱ ትቶኝ የሄደው የስድስት ወር እርጉዝ እያለሁ ነው። የዛኔ ከጓደኞቼ ጋር በደባልነት ተከራይቼ እኖር ነበር። ልጄም የተወለደው በዚህ አስቸጋሪ ሕይወት ውስጥ ነው። ልጄን ለማሳደግ ብዙ ፈተናዎችን አልፌያለሁ። ለአስራ አንድ ግዚያት ቀዶ ሕክምና ተደርጎለታል።

ዘንድሮ እኩዮቹ ‹‹ሆያሆዬ›› ሲሉ አብሮ መጨፈር ፈልጎ ነበር። እኔ በየቀን ስራው ይገቼው ስለምዞር የልቡ መሙላት አልቻለም። እሱ ግን ሀሳቡ ጨዋታ አልነበረም። ‹‹እማዬ እኔ ብጨፍር እኮ የማመጣው ብር አንድ ነገር ይገዛልሽ ነበር አለኝ።›› በጣም ተሰማኝ። ስለእኔ ብዙ የሚያስብ ልጄ ነው። ችግሬ ተዘርዝሮ አያልቅም። ልጄ መማር ይፈልጋል። ይህን ለማድረግ ብዙ ይጎድለኛል። እኔ በእግዚአብሔር ተስፋ አልቆርጥም ሁሌም በምስጋና አስበዋለሁ።

**‹‹ፈጣሪን አላማርረውም››**

ከማህሌት በኋላ የመናገር ዕድል ያገኘችው እናት ንግግሯን የጀመረችው ፈጣሪን በማመስገን ነበር። ‹‹ልጄ በጣም ደስተኛ ነች። እኔም ደግሞ ፈጣሪ ትችያለሽ ብሎ ስለሰጠኝ አላማርረውም። እሷ በተወለደች ግዜ እኔም ታምሜ ነበር። በግዜው የነበሩ ሀኪሞች ግን ከእኔ ልጅ የባሰ ችግር ያለባቸው ልጆች ስለመኖራቸውን አሳዩኝ። ፈጥኜ ተጽናናሁ። ለእኔ መልካም ወላጅነት ማለት እንዲህ ነው።

መልካም ወላጅ ሁሌም የተሰጠውን አምኖ ይቀበላል፤ በሆነበት ሁሉ ፈጣሪውን ያመሰግናል››። ልጄን ለማስተማር በሞከርኩ ግዜ እንዲህች አይነት ልጅ አንቀበልም ብለው ያባረሩኝ መምህራን ነበሩ። ‹‹ከፈለግሽ ቤትሽ አድርጊያት፣ ከፈለግሽ ደግሞ ጣያት ያሉኝም አልጠፉም። ያንን ሁሉ አልፌ ግን በትግሌ ማስተማር ችያለሁ። ስለሁሉም ነገር ምስጋና እንጂ እግዜርን አላማርርም። ››

የአዲስ ዓመት መግባትን ምክንያት በማድረግ በድርጅቱ አጸድ በነበረው ዝግጅት በርካታ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ታድመዋል። ሁሉም ሕይወታችው ብዙ የሚናገር ማንነታቸው አስደናቂ ታሪኮችን የሚመሰክር ነው። ያሉበትና ያለፉበት የሕይወት ጎዳና ብዙ አሳይቷቸዋል፣ .ፈትኗቸዋል።

እነዚህ ድንቅ ወላጆች አሁንም በምሬት አይራመዱም። እንደ ዓምና ካቻምናው ዛሬን ኖረው ነገን ተስፋ ያደርጋሉ። በሆነባቸው ሁሉ ከምስጋና ፊት ምሬትን አያስቀድሙም። ዘወትር ፈጣሪያቸወን እያሠቡ ‹‹ተመስገን›› ይሉታል። አዎ! ሁሌም ‹‹ተመስገን። ››

# በ120 ወረዳዎች የሚተገበረው የገጠር መንገዶች ግንባታና ጥገና ፕሮግራም

**በኃይሉ አበራ**




ኢትዮጵያ በ2030 የአፍሪካ የልማት ተምሳሌት ለመሆን በምታደርገው ጉዞዋ በሰፋፊ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ውስጥ ትገኛለች። በተለይ በሀገሪቱ እድገትን ለማረጋገጥ ለሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ የምጣኔ ሀብት እና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ከእነዚህ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች መካከል የመንገድ መሰረተ ልማት ዘርፉ ጉልህ ድርሻ አለው።

በየጊዜው እያደገ የመጣውን ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ዕድገት፣ ዘላቂነትና ፍትሐዊነት፣ ለማረጋገጥ የእነዚህ መሰረተ ልማቶች ግንባታ ወሳኝ መሆኑ ይታመናል፡፡ ከ120 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያላት ኢትዮጲያ ከህዝብ ብዛቷ ጋር በተሰናሰለ መልኩ ተደራሽነት እና ፍላጎትን ታሳቢ ያደረገ የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ፣ ጥገና እና እንክብካቤ ስራ ማካሄድ እንዳለበት ይታመናል።

ይህንንም ቀጣይነት ባለው መልኩ ማስኬድ የሚያስችል የልማት ማዕቀፍ ተዘርግቶ ሲሰራበት መቆየቱን የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በቅርቡ አመላክቷል። ሚኒስቴሩ ‹‹የገጠር ትስስርና ተደራሽነት ለምግብ ዋስትና›› የተሰኘ ፕሮግራም ማስጀመሪያ መርሐ ግብርም አካሂዷል። በፕሮግራሙ አዲስ የገጠር መንገዶች ግንባታ፣ የመንገድ ጥገና፣ የተንጠልጣይ ድልድዮች ግንባታ እና የተሻጋሪ ድልድዮች ስራ ተግባራዊ እንደሚደረጉ ተጠቁሟል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሄለን ደበበ በመድረኩ ላይ እንዳብራሩት፤ ባለፉት ዓመታት በገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የአገሪቱን የመንገድ አውታር መጠን እና ተደራሽነት ትርጉም ባለው መልኩ ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል። ፕሮግራሙ በሀገሪቱ የገጠር ቀበሌዎችን በሙሉ በአቅራቢያቸው ከሚገኝ ደረጃውን ከጠበቀ ዋና መንገድ ለማገናኘት ታሰቦ የቀረበ ነው። በዚህ ፕሮግራም ብቻ 50 ሺህ ኪሎ ሜትር የተለያየ ደረጃ ያላቸው መንገዶች ተገንብተዋል፡፡

በፕሮግራሙ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የስራ እድል ፈጠራ እና ሌሎች ዘርፎችን ለማነቃቃት ለመስራት ታስቦ ሲሰራ መቆየቱን ሚኒስትሯ አስታውሰው፣ በፕሮግራሙ ሁሉንም የገጠር ቀበሌዎች በአቅራቢያቸው ከሚገኙ ዋና ዋና መንገዶች ጋር ደረጃውን በጠበቀ መንገድ ለማገናኘት የተቀመጠው ግብ በተሟላ መልኩ አለመሳካቱን አስታውቀዋል።

የመንገድ ተደራሽነት የገጠሩ ህዝብ ኑሮ እንዲቀየር እንዲሁም ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ያለው ተደራሽነት እንዲሻሻል በማድረግ በኩል መሰረት የጣለ እንደነበር ጠቅሰው፤ ይህም "የገጠር መንገድ ትስስር ለምግብ ዋስትና ድጋፍ ፕሮግራም" የተሰኘው አዲሱ ፕራግራምም በተለያዩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ባለቤትነት ሲከናወኑ የነበሩ የገጠር መንገድ ስራ ንዑስ ፕሮግራሞችን ወደ አንድ አገራዊና ወጥ የአሰራር ስርአት እንዲመጡ ለማድረግ እንደሚያስችል አመልክተዋል። ፕሮግራሙ የተቀረጸውም ነባሩን ፕሮግራም በመገምገም እና ለቀጣይ አስር ዓመት የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ በማካተት ነው ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ እንደተናገሩት፤ ለግንባታው የዓለም ባንክ እና የኢፌዴሪ መንግሥት ሚያዝያ 11 ቀን 2024 ባደረጉት ስምምነት መሠረት ከዓለም ባንክ በተገኘ 300 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ፤ እንዲሁም ከክልል መንግሥታት 107 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ በጀት ተመድቦ በድምሩ 407 ሚሊዮን ዶላር የፕሮጀክት ፈንድ ፀድቋል። በአጠቃላይም ከ2017 የበጀት ዓመት ጀምሮ ፕሮግራሙን ለአምስት ዓመታት በሁሉም ክልሎች እና በድሬዳዋ የከተማ አስተዳደር ተግባራዊ ለማድረግ የዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል።

የዚህ ፕሮግራም ዋና ዓላማም የገጠሩን ማህበረሰብ እርስ በርስ እና ከማእከላት ጋር በማስተሳሰር እና ተነጥለው ያሉ አካባቢዎችን በማገናኘት እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ የገጠሩን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል እና ለምግብ ገበያ እና ለተለያዩ አገልግሎቶች ያለውን ተደራሽነት ማሳደግ ነው።

ፕሮግራሙ ከያዛቸው ግቦች መካከል የገጠር ቀበሌ ማዕከላትን አቅራቢያቸው ከሚገኝ ዋና መንገድ ጋር ማገናኘት የግብርና ምርት እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን መንደሮች እና መዳረሻዎች ማገናኘት፣ በመልክአ ምድራዊ አቀማመጣቸው ምክንያት ተነጥለው ያሉ የገጠር አካባቢዎችን ተደራሽ ማድረግ እና በቆላማ አካባቢዎች ያሉ የመሻገሪያ ችግሮችን መፍታት የሚሉት ይገኙበታል። ፕሮግራሙ በ12ቱ ክልሎች እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሥር ባሉ ከ120 በላይ ወረዳዎች የሚተገበር መሆኑን አስታውቀዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ እንዳሉት፤ በፕሮግራሙ በዋናነትም የሰባት ሺህ 554 ኪ.ሜ የወረዳ መንገድ ግንባታ፣ የአስር ሺህ 71 ኪ.ሎ ሜትር የወረዳ መንገዶች ጥገና፣ የ373 ተንጠልጣይ የእግረኛ መሻገሪያ ድልድዮች (Trial Bridges) ግንባታ እና የ715 የቆላማ አካባቢ መሻገሪያ ድልድዮች (Special Structures) ግንባታ ይካሄዳል።

በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ የሚሆነው ፕሮጀክቱ ከ11 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን፣ የመንገድ ግንባታው በቀጣይ 5 ዓመታት የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ለ200 ሺህ ዜጎች በቀጥታ እንዲሁም ለ360 ሺህ ዜጎች ደግሞ በተዘዋዋሪ የሥራ እድል ይፈጥራል።

ፕሮግራሙ ከመንገድ ተደራሽነት ባሻገር በገጠሩ አካባቢ የሚካሄደውን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ፕሮግራምም የመንገድ ስራ ፕሮግራሙ አካል ሆኖ እንደሚተገበርም ተናግረዋል፡፡ የግብርና ግብይት ዲጂታል ሥርዓት ግንባታ እንደሚካሄድም ጠቅሰው፤ ሥራው በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲቲዩት ተግባራዊ እንደሚደረግም አመልክተዋል፡፡ ገዢዎችን ከገበሬዎችና ነጋዴዎች ጋር በቀጥታ ለማገናኘት የዲጂታል የግብርና ምርት ገበያ መድረክ የማዘጋጀት፣ የግብርና ምርት መከታተያ ሥርዓትን የመንደፍና የመዘርጋት፣ የኮንትራት ግብርና አስተዳደር ሥርዓትን የመንደፍና የመዘርጋት እና የመንግሥት-የግል ሽርክናዎች የዲጂታል ገበያ ሥርዓት ሙከራ ስራንም ማቀፉን አብራርተዋል፡፡

የሀገር ውስጥ ተቋራጮች ከፍተኛ ኢንቨስትመንትን በሚጠይቁ መንገዶች ግንባታ ላይ የመሳተፍ ድርሻቸው አሁንም አነስተኛ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታዋ ጠቅሰው፤ ይህንን አለመመጣጠን ለማስተካከል በመንገድ ልማት ዘርፉ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት ዘርፉን የሚቀላቀሉበት እና እያደጉ የሚሄዱበት ተመጋጋቢ ስራ መንደፍን እንደሚጠይቅም ጠቁመዋል።

አዲሱ "የገጠር ተደራሽነትና ትስስር ለምግብ ዋስትና ፕሮግራም" በዚህ ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት እምነት እንዳላቸው ጠቅሰው፣ ክልሎችና በፌዴራል ደረጃ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ፕሮግራሙን በቅንጅት እንዲመሩና እንዲተገብሩ አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ የትምጌታ አስራት እንዳብራሩት፤ የፕሮገራሙ 10 ዓመት እቅድ ሲዘጋጅ እነዚህም በዓለም አማካይ ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት አማካይ፣ ከአፍሪካ አማካይ፣ ከሰሃራ በታች ያሉ አገራት አማካይ እና አነስተኛ ገቢ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት አማካይ የሀገራችን የመንገድ አውታር ታይተዋል። በዚህ መሰረት ኢትዮጵያ ካላት አጠቃላይ የመሬት ስፋት፣ የህዝብ ብዛት እንዲሁም የመልማት አቅም አኳያ ሲታይ ያላት የመንገድ አውታር ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

በመንገድ ጥግግት በኩል በአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ስኳር ወሰጥ የዓለም አማካይ የመንገድ ጥግግት 944



አቶ የትምጌታ አስራት



አቶ ተስፋዬ ወልደሚካኤል

ሲሆን፣ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው አገራት አማካይ 1244 ኪሎ ሜትር ነው። የኢትዮጵያ ደግሞ ወደ 130 ኪሎ ሜትር አካባቢ ነው።

በቀጣይ አሥር ዓመት እቅድ ኢኮኖሚው በፍጥነት ማደግ እንዲችል ያለንን የመንገድ አውታር ለማሳደግ ብዙ መንገድ መገንባትና ደረጃን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ የ10 ዓመቱ እቅድ ሲዘጋጅ ከመንገድ ጋር የተያያዙ ሁለት ዋናዋና መገለጫዎች አሉት፡፡ አምራች የኢኮኖሚ ዘርፎች በፍጥነት ማደግ አለባቸው። ይህም የመንገድ መሰረተ ልማት እድገትን ይፈልጋል። ለሁሉም አካባቢዎች መሰረታዊ የሆነ የመንገድ ተደራሽነት ማቅረብ ያስፈልጋል።

የ10 ዓመቱ እቅድ ሁለቱንም ሚዛናዊ አድርጎ ይዟል። ኢኮኖሚው በፍጥነት ማደግ እንዲችል ትላልቅ መንገዶችን፣ የፍጥነት መንገዶችን፣ የጉዞ መንገዶችን መገንባት አንዱ የእቅዱ አካል ተደርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ መሰረታዊ የሚባሉ በተለይ በገጠሩ አካባቢ የሚኖረው ህብረተሰብ ለመንገድ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ያለውን ተደራሽነት ለማሻሻል የገጠር መንገዶችን በስፋት መገንባት በእቅዱ ተይዟል።

ከመንገድ አውታር ጋር ተያይዞ የ10 ዓመቱ እቅድ ሲዘጋጅ ወደ 144 ሺህ ኪሎ ሜትር አካባቢ መንገድ እንደነበረ አስታውሰው፣ ይህን አሀዝ በአስር ዓመቱ ወደ 245 ሺህ ኪሎ ሜትር ለማድረስ እንደ ሀገር ግብ መቀመጡን አስታውሰዋል።

ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚው እንዳብራሩት፤ በአምስት ዓመት ውስጥ 91 ሺህ ኪሎ ሜትር፣ በ10 ዓመት ውስጥ ደግሞ ከ245 ሺህ በላይ ኪሎ ሜትር መንገድ ሊኖር ይገባል። በመሆኑም መካከለኛ ገቢ መደገፍ የሚችል የመሰረተ ልማት ሊኖር የሚገባ ከሆነ ይሄንን ያህል መጠን መንገድ ያስፈልጋል የሚል በ10 ዓመቱ እቅድ ተቀምጧል።

በሀገሪቱ የመንገድ አቅርቦት ሥርዓት ያልተማከለ ነው። የመንገድ ግንባታዎች በፌዴራል ደረጃ፣ ፣ በክልል ደረጃ ፣ በከተማ መስተዳድር ወይም በማዘጋጃ ቤት ደረጃ ይካሄዳሉ። ሀገራዊ የመንገድ አውታር የሚባለውም የእነዚህ አራት የመንገድ ባለቤቶች የሚተዳደሩ መንገዶች ድምር ነው።

በ10 ዓመቱ ውስጥ በፌዴራል ደረጃ የመንገድ አውታር መጠን ከ28 ሺህ ወደ 38 ሺህ ኪሎ ሜትር መጨመር አለበት። ይህም ከቀደመው አሀዝ ወደ 10 ሺህ ኪሎ ሜትር ጭማሪ አለው።ይህም በአማካይ በዓመት ወደ አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ተጨማሪ መንገድ መስራትን ይጠይቃል።

አብዛኛው የመንገድ ስራ ያለው በክልል እና በወረዳ ደረጃ መሆኑን አመልክተዋል። በክልል ደረጃ በ10 ዓመት ውስጥ ከ35 ሺህ ወደ 63 ሺህ፤ በወረዳ ደረጃ ደግሞ ከ55 ወደ 108 ሺህ ኪሎሜትር እጥፍ ለማድረግ ይሰራል ሲሉም ጠቁመው፤ የአብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል ጥያቄ መመለስ የሚቻለው በክልል ደረጃ እና በወረዳ ደረጃ በሚሰሩ የመንገድ አውታር ስራዎች መሆኑን አስገንዝበዋል።

የክልል የገጠር መንገዶችን ግምገማ በመድረኩ ያቀረቡት የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ከፍተኛ አማካሪ አቶ ተስፋዬ ወልደሚካኤል እንዳብራሩት፤ ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ ከኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት፣ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን እና ከፋይናንስ ሚኒስቴር የተውጣጡ የግምገማ ቡድን አባላት በሀገሪቱ ሁሉም አቅጣጫዎች ላይ ተመሰርተው ጂኦግራፊያዊ ግምገማ አድርገዋል።

ግምገማው የተደረገው የዓለም ባንክ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያስገባውን 65 ሚሊዮን ዶላር የመጀመሪያ ዙር ድጋፍ ወደ ክልሎች ለማሰራጨት ታስቦ መሆኑን አስታውቀዋል። ክልሎች ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በክላስተር ላይ እንደሚታይ ተናግረዋል፡፡ በግንባታው ዙሪያም በመጀመሪያ በሁሉም ክልሎች ላይ በጋራ፣ በአንዳንዶቹ ትራንስፖርት እና መንገድ ቢሮ፣ አንዳንድ ቦታ በመንገድ ቢሮ፣ በሌሎች ዘንድ ደግሞ በመንገዶች ባለሥልጣን ክልላዊ ባለድርሻዎች እና ቢሮዎች ፋይናንስን የማማከር ስራ ተደርጓል ሲሉም አብራርተዋል።

ከአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲዎች እና ባለሥልጣኖች እንዲሁም ከግዥ /ፕሮኪዩርመንት/ አስተዳደር ኤጀንሲዎች እና ከክልል ፀረ ሙስና ተቋማትና በክልል ደረጃ ከሚገኙ የፕሮግራሙ ባለድርሻዎች ጋር ግምገማ ተደርጓል። ገንዘብ ከሄደ በኋላ በሚገባ ተሰርቶ ሪፖርት መደረገ ያለበት ስለመሆኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተደርገዋል።

የግምገማ ቡድኑ ከአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ሶማሌ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ፣ ሀረሪ አፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላና ትግራይ ክልሎች ርእሰ መስተዳድሮች እና ከፍተኛ ኃላፊዎች እንዲሁም ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከሚመለከተው ጋር መወያየቱን አስታውቀዋል።

# በተለወጠ ልብ የተለወጠ ሀገር እንፍጠር

ቴል ጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

አዲስ ዓመትን በአዲስ ልብ ካልተቀበልነው አሮጌ ነው። አዲስ ዓመት አዲስ የሚሆነው እኛ በአስተሳሰብ ስንልቅና አዲስ ስንሆን ብቻ ነው። የሰው ልጅ ታሪክ አለው..ታሪክ ደግሞ በጊዜና በዘመን ውስጥ ያልፋል። የእያንዳንዳችን ታሪክ ከውልደት የሚጀምር በሞት የሚጠናቀቅ የዘመን ሀቅ ነው። ይህ ተፈጥሮአዊ እውነት ደግሞ የሰውን ልጅ ማረፊያ አድርጎ በተቀመጠለት የስርዐት አውድ ውስጥ እየመጣ የሚሄድ ነው።

ጊዜ ሀጂውን እየሸኘ..መጪውን እየተቀበለ በማይዛነፍ ፍጹም እውነት ውስጥ ይጓዛል..የሰውን ልጅ ጉዳይ አድርጎ። ጊዜ ጌታ ነው..ጊዜ ፈራጅ ነው። ጊዜ መጽናናት መሻርም ሁሉንም ነገር ነው። በተፈጥሮ እውነት የጸና..በሚዛናዊነት ምህዋር ውስጥ ሳይንገዳገድ የቆመ መለኮታዊ ጽኑ ቃል እንዲህም ነው። የጊዜ ጌትነት ግን በራሱ የሚሆን ሳይሆን በሰው ልጅ የማሰብ አቅም የሚወሰን የአእምሮ ነጸብራቅ ነው። የእያንዳንዳችን ትላንት የእያንዳንዳችን ዛሬና ነገ፣ የእያንዳንዳችን ድሮና ዘንድሮ፣ አምናና ካቻምና በዚህ በጊዜና በሰው ልጅ የጋርዮሽ መስተጋብር የተቃኘ ነው።

የሰው ልጅ በጊዜ ውስጥ ባለታሪክ ነው። ጊዜ በሰው ልጅ ውስጥ ጉልበታም ነው። የጊዜና የሰው ልጅ ቁርኝት ታሪክን እየደገመ፣ ተፈጥሮን እያጣቀሰ የሚያዘግም ነው። ጊዜ የታሪክ መፈጠሪያ፣ የህልምና ምኞት ካዝና ነው። የምንፈልጋቸው ነገሮች በጊዜ ውስጥ አልፈው የእኛ የሚሆኑ ናቸው። ካለጊዜ ሰው፣ ካለሰው ጊዜ ምንም ናቸው። ጊዜና የሰው ልጅ እጅና ጓንት፣ መዳፍና አይበሉባ፣ መረብና አሳ ናቸው። ሁለት አካል አንድ ገጸ ሰብ፣ ሁለት ገላ አንድ አይነት መልክ። በተፈጥሮ እውቀትና ጥበብ ተሰናስለው የተዳሩ የዳበሩም ናቸው።

ለዚህም ነው አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር አዲስ አስተሳሰብና አዲስ ነፍስና ስጋ ፍለጋ የምንዋትተው። ለዚህ እኮ ነው አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር ከአምናው የተለየን ለመሆን በአዲስ እቅድና በአዲስ ምኞት የምንሳበው። ለዚህ እኮ ነው እድሜአችን የሚያሳስበን፣ ሞታችን የሚያስጨንቀን። ትልቁ የዘመን መለወጥ ፋይዳው በአስተሳሰቡ ለተቀየረና ተሀድሶን መሰረት ላደረገ አእምሮ ነው። ለለውጥ ካልተጠቀምንበት ጊዜ መጥቶ ከመሄድ ባለፈ ትርጉም የለውም። ትርጉም ያለው ሆኖ እንዲያልፍ የምናደርገው እኛ ነን።

አዲስ ዓመት እንደ ትርጉሙ አዲስ ነው። በውስጡ አንዳች ኃይልና ብርታት አለው። ለሰው ልጅ ሁሉ የሚሆን የመታደስ፣ የመበርታት መንፈስን በውስጡ ይዟል። ብዙዎቻችን ይሄን ኃይል እንፈልገዋለን። በዚህ ኃይል ውስጥ መኖር እንፈልጋለን። ለዚህም ዓመት ጠብቀን የምናቅድ፣ ዓመት ጠብቀን የምንጀምር፣ ዓመት ሲመጣ የምንበረታ ባጠቃላይ ለምንም ነገር አዲስ ዓመት የምንል ብዙዎች ነን።

ብዙዎቻችን ጋ የአዲስነት ስሜት የሚያድርብን አዲስ ዓመት ሲመጣና ሲቃረብ ነው። የመስራት የመለወጥ ፍላጎታችን የሚነሳሳው መስከረም ሊጠባ ጥቂት ሲቀረው ነው። ሕልሞቻችን የሚታወሱን የአበቦቹን ሽታ ተከትለን ነው። ከአሮጌነት የምንወጣው፣ ከድሮነት የምንሸሸው ጳጉሜን ተሻግረን አበባየ ሆይ ሲባል የሚመስለን እልፍ ነን። ሕይወታችን፣ መኖራችን ትርጉም ያሚያገኝ የሚመስለን በዚህ ጊዜ ነው። ለአዲስ ሕይወት የምንዘጋጀው ይሄን አዲስ ዘመን ታከን ነው። ሁሉ ነገራችንን ለአዲስ ዓመት አሳልፈን የሰጠን ነን።

ይሄ ስህተት ነው የሰው ልጅ የጊዜ ባሪያ መሆን የለበትም። ዛሬን ለለውጥና ለስኬት መጠቀም ይኖርበታል። የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር ከዛሬ በመጀመር፣ ከአሁን በማቀድ ማሳካት እንችላለን። ብዙዎቻችን ዛሬን አናውቀውም። የአሁኑን ኃይል አልተረዳነውም። የቆምንባት ቅጽበት የኃይል የለውጥ መጀመሪያ እንደሆነች ገና አልደረስንበትም። አዲስ ዓመት የምንም ነገር መጀመሪያ እንደሆነ አምነን የተቀበልን ነን። በአዲስ ዓመት ሰሞን ከሞት የምንነቃ፣ ካንቀላፋንበት የምንባንን ብዙ ነን።

በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ለውጥ የለም። በዚህ እምነት ውስጥ ስኬት የለም። ስኬት መነሻውም መድረሻውም

**ባልተለወጠ እምነት የተለወጠች ሀገር አትኖርም። ለውጥ ሁልጊዜም መነሻው አእምሮ ነው። በአእምሯችን ስንለወጥ ብቻ ነው ባለውም በሚመጣውም ዘመን ላይ ጀግና የምንሆነው**

አዲስ ዓመት ሳይሆን አዲስ አስተሳሰብ ነው። አዲስ አስተሳሰብ ደግሞ ዛሬን ከመጠቀም አሁን ከመኖር የሚጀምር ነው። አዲስ ዓመት ሲያልፍ ምኞታችን አብሮ የሚያልፍ ከሆነ፣ አዲስ ዓመት ሲመጣ ምኞታችን ከሞተበት የሚነቃ ከሆነ የአዲስ ዓመትን ትርጉም አልተረዳነውም ማለት ነው። ጊዜና ለውጥን አስታከው የተጻፉ ብዙ የስኬት መጽሀፎች አሉ። አንዳቸውም ለውጥ ከአዲስ ዘመን እንደሚጀምር አልጻፉም። የሁሉም የጋራ ሀሳብ ለውጥ ያለው ከዛሬና ከአሁን የሚል ነው።

ጥያቄ አንድ..አዲስ ዓመት ማለት ምን ማለት ነው? በአስተሳሰቡ ላልተቀየረ ማኅበረሰብ አዲስ ዓመት ምኑ ነው? ከመጠበቅና ተስፋ ከማድረግ ላልወጣ ሰውነት አዲስ ዓመት ዋጋው ስንት ነው? ፍቅርን ለማያውቅ ይቅርታን ላልተማረ ልብ ጊዜ ዘመን ምኑ ነው? ለማይሰሩ እጆች፣ ለማያስቡ ጭንቅላቶች መጠበቅ ፋይዳው ምንድ ነው? በብሄር፣ በጎሳ ለሚባላ ሀገርና ሕዝብ የዘመን መቀየር ፋይዳው ምንድነው? ከወንድሞቹ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖ ለሚኖር፣ ተነጋግሮ መግባባት፣ ተወያይቶ መስማማት ላቃተው ፖለቲካና ፖለቲከኛ፣ ትውልድና ዜጋ መሻገር ምንድነው? እኚህ ጥያቄዎች አሁን ላለነው እኛ መሰረታዊ ናቸው። የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ስናውቅና ስንረዳ ብቻ ነው የአዲስ ዓመትን ዋጋ ልንረዳው የምንችለው።

ያለፈውን ዓመት እንዲህ እንደ አሁኑ ለመነቃቃት ተጠቅመነው ነበር። አምናን እኮ በእልልታና በፌሽታ ተቀብለነው ነበር። ካቻምናን እኮ የደስታና የሰላም ዘመን ብለነው ነበር። ያለፈውን ዓመት ብዙ ልንሰራበት ብዙ ልናተርፍበት አውርተን ነበር። 2016 እኮ እንደ ሀገር፣ እንደግለሰብ ብዙ ያቀድንበት ብዙ ያሰብንበት ዘመን ነበር ግን እንደሀሳባችን አልተጠቀምንበትም። እንደምኞታችን አላዋልነውም። ምክንያቱም ከዘመን ጋር የተቀየረ አእምሮ ስለሌለን።

በተቃራኒው መጥፎና እድለ ቢስ እንደነበር አወራን። ምንም ያላተረፍኩበት ዓመት ነው ስንል ነቀፍነው። አያችሁ የዘመንን እውነት? ዘመን የሚዘወረው በሰው ልጅ አስተሳሰብ ነው። ያለፉት ዓመታቶች ጥሩ ያልነበሩት ዘመኑ ጥሩ ስላልነበር ሳይሆን እኛ ጥሩ ስላልነበርን ነው። እኛ ስላልተቀየርን ዘመኑም አልተቀየረም። የሰው ልጅ ልቡና አእምሮው፣ ሀሳቡና ምኞቱ ካልተቀየረ አዲስ ዓመት ምንም ነው። ሀሳባችንን ሳናድስ፣ ከድሮነት ሳንወጣ ሰኔና ሐምሌ ገመገም ላይ ቆመን 2016 ለኔ ጥሩ ጊዜ አልነበረም፣ ለሀገራችን መልካም አልነበረም ብንል ልክ አይደለንም።

ዘመን ለሰው ልጅ ሎሌ እንጂ ሰው ለዘመን ሎሌ አይደለም። ሁሉን ነገር ለአዲስ ዓመት ትተን መቀመጣችን የዘመን ጥገኞች መሆናችንን ከማሳየቱ ባለፈ እያንዳንዱን ቀን ዋጋ ለመስጠት የምናደርገው የበረታ እንቅስቃሴ እንደሌለም የሚያሳይ ነው። ዘመን በእኛ ስር ነው። አዲስ ዓመት አዲስ የሚሆነው በእኛ አዲስ ልብ ነው። ልቦቻችንን አሳድፈን፣ መንፈሳችንን አስነውረን፣ ፍቅርና ይቅርታን ሳንማር፣ በመነጋገር ሳንግባባ፣ በእርቅ አንድ ሳንሆን ብንቀበለው ያው ነው እንደ ድሮው..እኛም ከእርግማን አንወጣም።

ተስፋ ያደረግንው አዲሱ ዓመት ያሰብነውን እንደሚሰጠን ዋስትናችን ምንድ ነው? የሚመጣው አዲስ ዓመት የምንመኘውን እርቅ፣ የምንፈልገውን አንድነት፣ የራቀንን ሰላም እንደሚሰጠን መተማመኛችን ምንድ ነው? ምንም መተማመኛ የለንም። ልንተማመንበት የሚገባ አንድ ነገር ቢኖር ራሳችን ነን። ራሳችንን ለፍቅር፣ ለይቅርታ፣ ለመነጋገር ዝግጁ ካደረግን እንዳሰብነው አዲስ ዓመት አዲስ ይሆናል። ይሄ ባልሆነበት ሁኔታ አዲስ ዓመትን አዲስ ይሆናል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው የሚሆነው።

ታሪኮቻችን ውብ የሚሆኑት በእኛ ነው። ጊዜ እኛ ተኝተን የሚያነቃ ኃይል የለውም። ለምንፈልገው ሰላም፣ ለምንፈልገው አንድነት፣ ለምንፈልገው እድገት ዘመን አስተዋጽኦ የለውም። ለዚህ ምስክር የሚሆኑን ያለፉ በአዲስ ምኞት ተቀብለናቸው አዲስነትን ያልሰጡን ዘመኖች ናቸው። ተስፋዎቻችን ሀሳቦቻችን በኩል የሚያብቡ እንጂ በመስከረም ጥባት በኩል የሚታዩ አይደሉም። እንደዚህ አይነት መለማመዶች ለማንም አይጠቅሙም። ዘመን ያው እንደትላንቱ ነው። የተፈጥሮን እውነት ጠብቆ መጥቶ የሚሄድ ነው። አትምጣ ብንለውም፣ ና ብንለውም በእኛ ፍቃድ ስር አይደለም። መጥቶ መሄድ ተፈጥሮአዊ ግብሩ ነው።

ከዚህ እውነት በመነሳት አዲስ ዓመት ሲመጣም ሆነ ሲሄድ የተለየ ተፈጥሮ እንደሌለው መተማመን ላይ መድረስ እንችለለን። አዲስም ሆነ አሮጌ የሚሆነው በሰዎች ተጽዕኖ ነው። ቀን ሳንጠብቅ፣ ጊዜ ሳናሰላ፣ አዲስ ዓመት ሳንል የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር አሁን ላይ መፍጠር እንችላለን። ሰላም ከሆነ የምንሻው፣ አንድነት ከሆነ ፍላጎቶቻችን ሰላምና አንድነት በሚያመጡ ሀሳቦች ላይ በማተኮር የምንፈልገውን ማግኘት እንችላለን።

ባልተለወጠ እምነት የተለወጠች ሀገር አትኖርም። ለውጥ ሁልጊዜም መነሻው አእምሮ ነው። በአእምሯችን ስንለወጥ ብቻ ነው ባለውም በሚመጣውም ዘመን ላይ ጀግና የምንሆነው። ከጊዜ ባርነት መውጣት ይኖርብናል። ለምንም ነገር ነገን መጠበቃችን፣ ለምንም ነገር አዲስ ዓመትን መሻታችን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ነው የሚያመዝነው።

ሰላም ሊሰጡን የሚችሉ፣ ሕልምና ራዕዮቻችንን ልናሳካባቸው የሚችሉ ብዙ ቀናት፣ ብዙ ጊዜዎች አብረውን አሉ። ራሳችንን ማንቃት ከቻልን ወደትላንት ሳንሄድ፣ ወደነገም ሳናዘግም መለወጥ እንችላለን። ችግሩ ከአዲስ ዓመት አስተሳሰብ አልወጣንም። ችግሩ ከዛሬ ይልቅ ነገን ተስፋ የምናደርግ መሆናችን ነው። ከቻልን ጊዜ የእኛ ባሪያ እንዲሆን እንቆጣጠረው። ከቻልን እያንዳንዱን ቀናችንን የምንም ነገር አዲስ ዓመታችን አድርገን እንቀበለው።

በጊዜ ባርነት ውስጥ ልዕልና የለም። በመጠበቅ ውስጥ ንግስናና ክብር ምንም ናቸው። ሰው ከትጋት ሲጎድል፣ ከጥረት ሲላላ ለምንም ነገር ጊዜን መጠበቅ ይጀምራል። ጊዜን የመጠበቃችን ምክንያት ስንፍናና አጉል የኑሮ ዘይቤ መልመዳችን ነው። በእውቀትና በእቅድ መኖር ብንጀምር እያንዳንዷ ቀን አዲስ ዓመታችን ትሆን ነበር ወይም ደግሞ ከአዲስ ዓመት በበለጠ ምን ያክል ለለውጥና ለስኬት አስፈላጊ እንደሆነች እንረዳ ነበር። በትጋት ስንሞላ ለምንም ነገር ጊዜ እኛን መጠበቅ ይጀምራል። በትጋት ስንሞላ ምንም ነገር ከአሁን እንጀምራለን። ጊዜን መጠበቅና በጊዜ መጠበቅ ሁለት የተለያዩ እውነቶች ናቸው። ልክ ለምንም ነገር አዲስ ዓመትን እንደሚጠብቁት እና ለምንም ነገር ዛሬ የተሻለ ቀን ነው ብለው እንደሚያምኑት ሁለት ጉራማይሌ ነፍሶች አይነት።

ትጉ ነፍሶች የሚፈልጉትን ዘመን ዛሬ ላይ ይፈጥሩታል። ታካች ነፍሶች ደግሞ በመንቀፍ፣ በመሰልቸት፣ በስንፍና፣ በአይሆንልኝም፣ በማመንታት፣ በመወላወል፣ ቆይ ነገ በሚል እሳቤ በመጠበቅ ውስጥ ይቆማሉ። ብዙ ዛሬዎችን፣ ብዙ አሁኖችን፣ ብዙ ነገዎችን ዘለን አዲስ ዓመትን መጠበቃችን ስንፍናና ስልቹነት ምን ያክል ስር እንደሰደደብን አመላካች ነው። ብልህ ሰው በብሩህ ሀሳቡ በኩል ዛሬን አዲስ ዓመት ማድረግ ይችላል። ጠንካራ ሰው ወደ ነገ ሳይሄድ፣ ወደ አምና ሳይሳብ አሁንን ለለውጥና ለስኬት መጠቀም ይቻለዋል።

ለተጋ ልብ፣ ለበረታ አእምሮ ሁሌም ስኬት፣ ሁሌም አዲስ ዓመት አለ። ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት አዲስ ዓመት ለእኛ ብሎ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም። መጥቶ እንዲሄድ የተፈጥሮ ግዳጁን እየተወጣ ነው። እኛ ነን ከተፈጥሮ የራቅነው። እኛ ነን ማስተዋል የጎደለን..በጊዜ ሀቅ ውስጥ ቆመን እንኳን መማር አልቻልንም። ለመማር ዝግጁ ብንሆን ጊዜ የሚያስተምረን ብዙ ነበረው።

አምናን በጉጉት ጠብቀነው የምንፈልገውን ሰላምና አንድነት ካልሰጠን፣ 2015 ለነበሩብን ችግሮች መፍትሄ አድርገነው ቃሉን ከበላ ችግሩ ከጊዜው ሳይሆን ከእኛ እንደሆነ ልንረዳ ይገባል። አዲሱን 2017 በአምና ልብ ሳይሆን በታደሰና በተቀየረ ልብ ልንቀበለው ይገባል። ያኔ ያለጥርጥር የምንፈልገውን እናገኛለን..እንደምኞታችንም ዘመኑ አዲስ መሆን ይጀምራል።

የሚሰማ ጆሮ የሚያስተውል ልብ ቢኖረን ኖሮ የጊዜን ሹክሹክታ እናደምጠው ነበር። ጊዜ ህላዊ ኖሮት መናገር ቢችል ኖሮ ‹..እባካችሁ አትጠብቁኝ እኔ ለሰው ልጅ የሚሆን ምንም የለኝም፣ ለበረቱ እየመጣሁ የምሄድ፣ ለጠንካሮች ሚዛኔን የደፋሁ ነኝ› የሚለን ይመስለኛል። በዚህ አያበቃም ‹ከኔ ይልቅ ዛሬና ነገ የላቀ ዋጋ አላቸው።

አስራ ሁለት ወራትን አልፋችሁ፣ ሀምሳ ሁለት ሳምንታትን ትታችሁ፣ ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ቀናትን ሽራችሁ የምትጠብቁኝ ምናችሁ ሞኝ ነው? ሲል የሚያላግጥብን ይመስለኛል። መች በዚህ ያበቃና ‹ልቦቻችሁን ሳታድሱ፣ አመለካከታችሁን ሳትቀይሩ ጥሩ ነው መጥፎ ነው እያላችሁ አትሙኙኝ። እኔ ጥሩና መጥፎ የመሆን ስልጣን የለኝም። መጥቼ እንድሄድ የታዘዝኩ የተፈጥሮ መንገደኛ ነኝ እናም አትጠብቁኝ በአሁናችሁ ላይ በርትታችሁና ተልቃችሁ ቁሙ› ይለን ነበር።

ምኞታችን መልካም ጊዜ ከሆነ እጆቻችንን በስራ፣ ልቦቻችሁን በትጋት እንጥመድ። ምኞታችን ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ወንድማማችነት ከሆነ ደግሞ ለነዚህ የሚሆን የተግባቦት ሰውነትን መፍጠር ይኖርብናል። ካልሰራንበት፣ ካልበረታንበት አዲሱ ዓመትም እንደ አምናና ካቻምና ርባና ቢስ ሆኖ ነው የሚያልፈው። አዲስ ዓመት የዛሬ አብራክ ነው። ብዙ ዛሬዎች ተቆጥረው ነው የምንቦርቅበትን አዲስ ዓመት የሰጡን። ለምንድነው ዛሬአችንን አዲስ ዓመት አድርገን የማንቀበለው? ለምንድነው አዲስ ዓመት ሲመጣ የምናገኘውን ኃይልና ብርታት በቆምንባት ዛሬ ላይ የማንፈጥረው?

አንሳት ..አዲስ ዓመት የቀናት ጥርቅም ነው። አዲስ ዓመት የሳምንታት የወራት ሂደት ነው። ለመለወጥ ካልተጋን የሚሰጠን አንዳች ነገር የለውም። እኛ እስካልተለወጥን ድረስ የአዲስ ዓመት መምጣት ምንም ነው..ቤስቲ ቤስታ የለውም። ጊዜ በተለይም አዲስ ዘመን በእያንዳንዳችን ሕይወት ላይ ዋጋ የሚኖረው የአሁኑን ወይም ደግሞ የዛሬን ዋጋ ስናውቅ ብቻ ነው። አምና አዲስ ያልነው ዘንድሮ አሮጌ ብለን ሸኝተነዋል። ምንም አላተረፍንበትም። ስለዚህ ከዘመን ቁራኛነት ወጥተን ዛሬን አዲስ ዓመት እናድርግ። በተለወጠ ልብ በተለወጠ ሀሳብ የተለወጠ ሀገርና ሕዝብ እንፍጠር።

# ስፖርት





## በኦሊምፒክ ኮሚቴ ላይ የቀረበው ክስና የተሰጠው ምላሽ

**ቦጋለ አበበ**

የተለያዩ ብሔራዊ ፌዴሬሽኖችና አትሌቶች በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴና በአመራሮቹ ላይ ከቀናት በፊት በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ መመስረታቸው ይታወሳል። ፌዴሬሽኖቹንና አትሌቶቹን ወክለው ክሱን ያቀረቡት ጠበቆች ከትናንት በስቲያ በኃይሌ ግራንድ ሆቴል በቀረበው ክስ ዙሪያ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ይህንን ተከትሎም ኦሊምፒክ ኮሚቴ መግለጫ አውጥቷል።

ጠበቆቹ በሰጡት መግለጫ ከሳሾቹ የኢትዮጵያ ቴኒስ እና ቦክስ ፌዴሬሽኖች ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገ/ስላሴና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት አትሌት ገዛኸኝ አበራ መሆናቸውና እነሱን ወክለው ችሎት ላይ እንደሚቆሙ አስረድተዋል።

የኢትየጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እንደ ተቋም፣ በግል ፕሬዚዳንቱ ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ፣ ዋናና ምክትል ጸሐፊዎቹ አቶ ዳዊት አስፋውና አቶ ገዛኸኝ ወልዴ እንዲሁም አቃቤ ነዋይ ዶ/ር ኤደን አሸናፊ መከሰሳቸውን የገለጹት ጠበቆቹ፣ አራት ፌዴሬሽኖች ክሱን ለመቀላቀል ጠይቀው ጉዳዩን እያዩ መሆናቸውን ይፋ አድርገዋል። "አራት ፌዴሬሽኖች የዚህ ክስ አካል ለመሆን ጠይቀውናል እያጠናነው ነው፣ ከማን ጋር ነው የምንጋጨው ብለው የሰጉም አሉ፣ ማንም በህግ አንጻር እኩል ነው ብለን ነው የምናምነው፣ የምንጋጨውም ግለሰብ የለም፣ መንግሥት ጣልቃ ይገባል ብለንም አንሰጋም" ሲሉም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ኦዲት አልተደረገም የሚለውን ጉዳይ አፅንኦት የሰጡት ጠበቆች፣ ተቋሙ ወደ 1 ቢሊዮን ብር በካሽና በአይነት ያለው ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግ መጠየቃቸውን ጠቅሰው፤ ወደ 48 ሚሊዮን ብር ለአኖካ ስብሰባ ተብሎ መንግሥት ክፍያ መፈፀሙን፣ እንደ ኢትዮ ቴሌኮምና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከፍተኛ ክፍያ ፈጽመው ኦዲት እንዳልተደረገ፣ ከ400 ሺህ ዶላር በላይ የሆኑ ትጥቆች በየዓመቱ ከአዲዳስ ኩባንያ ቢላክም የት እንደገባ እንደማይታወቅ ገልፀዋል።

"ኦሊምፒክ በተካሄደ ቁጥር ወደ 600 ሺህ ዶላር የሚገመት የስፖርት ትጥቅ ድጋፍ ይደረጋል፤ ለመላው አፍሪካ ወደ 500 ሺህ ዶላር ድጋፍ ተደርጓል፤ ለኦሊምፒክ ውድድር ተሳትፎ 30 ሺህ ዶላር ለስልጠና ተብሎ ደግሞ ከ15-20 ሺህ ዶላር በየዓመቱ ይመጣል፤ 198 ሺህ ዶላር ወጣቶችን ለማትጋት ተብሎ ይሰጣል፤ እስካሁን ግን ምንም ኦዲት አልተደረገም፤ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴርም የሚጠበቅበት ኃላፊነቱን አልተወጣም። በዚህም አዝነናል። ዋናው ጥያቄያችን ከላይ የገለጽናቸው ገቢዎች የት ገቡ ወይም ለምን ወጪ ተደረጉ የሚለው ምላሽ ያስፈልገዋል፣ ችሎቱን የጠየቅነውም ይህንን ነው" ሲሉ አብራርተዋል።

ጠበቆቹ አቶ አያሌው ቢታኒ ፣ አቶ ኃይሉ ሞላና አቶ ጳውሎስ ተሰማ ለመደበኛ ችሎት አቀረብን ባሉት የክስ ማብራሪያ፣ "ግንቦት 5 እና ሰኔ 14/2016 የተደረጉት የኮሚቴው ህገወጥ ጉባኤና ውሳኔዎቹ ይሰረዙ፤ ተገቢ በሆነ አግባብ አጠቃላይ ወጪ ላይ ኦዲት ይደረግ፤ በፓሪስ ኦሊምፒክ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እንደተካሄደ የሚያሳይ ነገር ስላለ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በፈረንሳይ ኤምባሲ በኩል እነማን ሄዱ እነማን ተመለሱ የሚለው እንዲጣራ ጠይቀናል፤ ኦሊምፒክ ኮሚቴው በ64 ሚሊዮን ብር ወጪ የውሃ ማምረቻ ፋብሪካ ለማሰራት ማሽኖችን ከውጪ አስገብቷል። የገቡት ማሽኖች እውነት ለፋብሪካው ስራ የሚጠቅሙ ናቸው የሚለው ይጣራል" ሲሉም አጠቃላይ የክሱን ጭብጥ አስረድተዋል።

ስፖርቱን በበላይነት የሚመራው መንግሥታዊ ተቋም ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የሚጠበቅበትን ዳኝነት እንዲሰጥ በተደጋጋሚ ያቀረብነው ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ባለማግኘቱ ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት እንደ ወሰዱትም ጠበቆቹ አብራርተዋል። በዚህም ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ችሎቱ ፊት ቀርቦ ምላሽ እንደሚሰጥና ለደረሰው ጉዳትም ወጪን እንደሚሸፍን ገልፀዋል።

‹‹በግልና በኦሊምፒክ ኮሚቴ አመራሮች ላይ የተወሰነው የ11 የባንክ ሂሳብ ቁጥር እገዳ ጊዜያዊ ነው። እገዳው እስከ ችሎቱ ውሳኔ የሚሰጥበት ጊዜ ድረስ የጸና ነው" በማለትም ሂደቱን ገልጸዋል።

"ግለሰባዊ አጀንዳ የለንም፤ ይሰቀል ይገደል የምንለው ሰውም የለም፤ ከኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጋር የገጠምነው ክርክር ዋናው ዓላማ ስፖርቱን ለመታደግ ብቻ ያደረግነው መሆኑ ታሳቢ እንዲደረግ እንጠይቃለን" ሲልም ጀግናው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገ/ስላሴ ተናግሯል።

የጠበቆቹን መግለጫ ተከትሎ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ በሰጠው ባለ 6 አቋም የምላሽ መግለጫ "ከሳሾች በውሸት ቃለመሀላ ፍርድ ቤቱን ያሳሳቱ በመሆናቸው ራሳቸው በህግ የሚጠየቁበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም" ብሏል። ከዚህ ቀደም በኦሊምፒክ ኮሚቴ ውስጥ የስፖርት ትጥቆችን መርካቶ ድረስ ሄደው በመቸብቸብ በፈፀሙት ህገ ወጥ ተግባር በኮሚቴው የታገዱ አካላት ስልጣን በሌለው መደበኛ ፍርድ ቤት ከሳሽ ሆነው መቅረባቸውም እጅግ አሳፋሪ ነው" ሲል የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ገልጿል።

በተጨማሪም ጠበቆቹ ‹‹በውሸት ቃለመሀላ ያገኙትን እግድ ልክ ተከራክረው እንዳሸነፉ መግለጫ መስጠታቸው የቱን ያህል በኃላፊነት እና በተጠያቂነት ስሜት እንደማይሰሩ በግልፅ የሚያሳይ ነው። ሀገርን ለማስቀጣት የሚደረገው እንቅስቃሴ በአስቸኳይ ሊቆም ይገባል" ሲል ኮሚቴው አስጠንቅቋል።

የስፖርት ነክ ጉዳዮች በመደበኛ ፍርድ ቤት እንደማይታዩ እና መደበኛ ፍርድ ቤት ስልጣን እንደሌላቸው እየታወቀ ህግና ሥርዓትን ተከትሎ ጥያቄ ማንሳት ሲገባ የውሸት ቃለመሀላ በማቅረብ እና ተረኛ ችሎቱን በማሳሳት እግድ ያወጡበት መንገድ ከሳሽ ነን የሚሉት ግለሰቦች ተከራክረው ማሸነፍ የሚችሉበት የእውነተኛ የህግ መሰረት የሌላቸው መሆኑን ያሳያል ሲልም ኮሚቴው በመግለጫው ጠቁሟል።

---

MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ የሚታተም

## ጤና ሚኒስቴር በአዲስ ዓመት ዋዜማ

**ሰላማዊት ውቤ**

የጤና ሚኒስቴር የማህበረሰቡን የጤና አገልግሎት ፍላጎት ከማርካት ባሻገር በማህበራዊውና በሌሎች ጉዳዮች ከሕዝቡ ጎን መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲያስመሰክር ይታያል። አምስቱን የጳጉሜን ቀናት ከጤናው ጋር በተሳሰሩ መሪ ቃሎች ከሕብረተሰቡ ጋር አክብሯል። የ2017 አዲስ ዓመት መባቻንም በሆስፒታል ከተኙ ወላድ እናቶች ጋር ነው ያሳለፈው። ለዛሬ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአምስቱ የጳጉሜን ቀናት ያከናወናቸውን ተግባራት ቃኝተን ልናስቃኛችሁ ወድደናል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ‹‹የተሟላ ጤንነት ለሀገር ሉዓላዊነት!›› በሚል መሪ ሀሳብ ጳጉሜን 3 ቀን 2016 ዓ.ም አክብሯል። ይህን ቀን አመራሮች እና ሠራተኞች እንዲሁም የጤና ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት በጋር በመሆን ለጤና ጠቃሚ የሆኑ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግና የሉዓላዊነት ዋንኛው መገለጫ የሆነውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በማውለብለብ አክብረውታል።

በዚሁ ወቅት የጤና ሚኒስትሯ ዶ/ር መቅደስ ዳባ ‹‹ሉዓላዊነት የሚከበረው መጀመሪያ ራስን መጠበቅ ሲቻል ነው››ብለዋል። እለቱ የጤና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት አመራሮች እና ሠራተኞች ወደ ራሳቸው የሚመለከቱበት ስለመሆኑም አንስተዋል። ከራሳቸው ጀምረው ጤናቸውን ለመጠበቅ እንዲሁም ጤንነቱ በተሟላ መልኩ የተጠበቀ ህብረተሰብ እንዲኖር በትኩረት መስራት እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

በዚሁ መርሐ ግብር ላይ የተገኙት የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር አየለ ተሾመ የሀገር ሉዓላዊነት የሚከበረው በጤናማ ትውልድ ስለመሆኑ ተናግረዋል። ይሄን ዓይነቱን አምራች ትውልድን ማፍራት የጤናው ዘርፍ ድርሻ ስለመሆኑ አንስተዋል። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ በቀላሉ ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች መጠበቅ አስፈላጊ ስለመሆኑም አስረድተዋል።

የጤና ሚኒስቴር አመራር እና ሰራተኞች ይሄን የህብር ዕለት "ጤናማ ትውልድ ለአብሮነትና ለሀገር ግንባታ!" በሚል አብሮነትን በሚያጠናክር መሪ ሀሳብ ነው ያከበሩት። በአከባበር ሥነ- ሥርዓቱ ላይ የጤና ሚኒስትሯ ዶ/ር መቅደስ ዳባ የህብር ቀን ያለው ለሌለው የሚያካፍልበት ስለመሆኑ ተናግረዋል። ሀገራችንን በጤናው ዘርፍ ከፍ ያለ ደረጃ ለማድረስ ቃል የምንገባበት ነው ብለዋል። ሠራተኛው በሚሰራው ሥራ ውጤታማ እንዲሆን ጠንክሮና በትብብር መንፈስ መሥራት እንዳለበትም አሳስበዋል። የጤናው ዘርፍና የማህበረሰባችን የጤና አገልግሎት ፍላጎት መሻሻል የሚችለው ሁሉም በጤናው ዘርፍ የሚሰራ አመራርና ሠራተኛ በአብሮነትና በህብረት ጠንክሮ ስራውን ሲሰራ ስለመሆኑም አስረድተዋል።



ሚኒስትሯ በዓውደ ዓመት ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው በሥራ ላይ የሚገኙ የጤና ባለሙያዎችን ሲያበረታቱ

ሚኒስትሯ በ2017 ዓ.ም በዘርፉ የሚመዘገበው ውጤት ከባለፈው በጀት ዓመት በተሻለ ደረጃ ከፍ እንደሚልም ተስፋቸውን ገልጸዋል። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አመራሮች ባለሙያውን ከጎናቸው በማሰለፍ ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ማበረታታት፣ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል እንዲሁም ምቹ የሆነ የስራ አካባቢን መፍጠር እንደሚገባቸውም አሳስበዋል። መረዳዳትና አብሮነትን ባህል አድርጎ ማስቀጠል እንደሚገባም አንስተዋል። በመርሐ ግብሩ ላይ አነቃቂ ንግግር እና በኤች አይቪ ኤድስ ዙሪያ የመወያያ ጽሁፍ ቀርቦም ውይይት ተደርጎበታል።

የጤና ሚኒስቴር ይሄን የ2017 ዓ.ም አዲስ ዓመት ዋዜማ በተለየ ሁኔታ ነው አክብረውት የዋሉት። ..የነገ ቀን.. የተሰኘ ስያሜ ያለው እንደመሆኑ ሁሉ ለነገ ተስፋ የሚሆኑ ሕፃናትን



ዓውደ ዓመትን ምክንያት በማድረግ በጤና ሚኒስትሯ ስጦታ ከተደረገላቸው ወልደው በሆስፒታል ከተኙ እናቶች አንዷ

ወልደው በተለያዩ ሆስፒታሎች የተኙ እናቶችን በመጎብኘትና የተለያዩ ስጦታዎችን በመስጠት ጭምር አክብረውታል። ለአቅመ ደካሞች መኖሪያ የሚሆናቸውን ያስገነቡትን ቤትም አስረክበዋል። በአካባቢዎቹ ለሚገኙ አቅመ ደካሞች ማዕድ ማጋራትም አከናውነዋል።

የቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፤የጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ኤካ ኮተቤ ጠቅላላ ሆስፒታልም ጉብኝት ተደርጎባቸዋል። በነዚህ ሆስፒታሎች ወልደው የተኙ እናቶች፣ በተለያየ የጤና መታወክ ችግር ምክንያት በሆስፒታሎቹ ተኝተው ህክምናቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ ወገኖች በጤና ሚኒስትሯና በተለያዩ ኃላፊዎች ተጎብኝተዋል። ስጦታም ተበርክቶላቸዋል።

በሆስፒታሎቹ እየተደረገ ያለውን የፅዱ ተቋም ኢኒሼዬቲቭና የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች በጤና ሚኒስቴር አመራሮች ተጎብኝተዋል። አመራሮቹ በዕለቱ በኤካ ኮተቤ ጠቅላላ ሆስፒታል የተገነባውን የአቅመ ደካሞች መኖሪያ ቤትም አስረክበዋል። ዓመት በዓልን ምክንያት በማድረግም ለነዚሁ አቅመ ደካማ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጭምር የተለያዩ ስጦታዎችንም አበርክተዋል። በጤና ሚኒስቴር ዋና መስሪያ ቤትም በአካባቢው ላሉ አቅመ ደካሞችና በችግር ውስጥ ላሉ ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የመዓድ ማጋራት መርሐ ግብር እንዲከናወን አድርገዋል።

ዶክተር መቅደስ በተከናወኑ መርሐ ግብሮች ላይ መልዕክት አስተላልፈዋል። መደጋገፍ፣ አብሮ መቆም እና ለወገን ደራሽ መሆን ከሁሉም ዜጎች የሚጠበቅ ስለመሆኑ አንስተዋል። በጤናው ዘርፍ ያሉ አመራሮች እና ባለሙያዎች ህብረተሰቡን የበለጠ ለማገልገል በቁርጠኝነት መስራት እንደሚጠበቅባቸውም አሳስበዋል።

በዘንድሮው የክረምት በጎ ስራዎች እንደ ሀገር ከ3 ነጥብ 9 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎች ነፃ የጤና ምርመራና የህክምና አገልግሎት ያገኙ ስለመሆናቸውም አንስተዋል። ለስኬቱም በዘርፉ ተሰማርተው አገልግሎቱን የሰጡትን የጤና ባለሙያዎችን አመስግነዋል። በዘርፉ በባለፈው የበጀት ዓመት በርካታ ስራዎች የተሰሩ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በ2017 አዲስ ዓመትም የተጀመሩትን ስራዎች ለማስቀጠል እና የጤና አገልግሎቱን የሚያሻሽሉ አዳዲስ አሰራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰራ ስለመሆኑ ተናግረዋል። በየሆስፒታሎች ያሉት የጤና ባለሙያዎች ዓመት በዓልን ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ከህሙማን ጋር በማሳለፋቸው አመስግነዋል። 2017 ዓ.ም በጋራና በቅንጅት መልካም ስራዎች የሚከወንበት፣ በአብሮነትና በህብረት በጤናው ዘርፍ የላቀ ውጤት የሚመዘገብበት ዓመት እንዲሆን ተመኝተዋል።